# ማውጫ


## ፖለቲካ 3



«በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ቦርዱ በፊት ከሚያደርገው በተለየ ሁኔታ የሚዲያ ክትትል ያደርጋል»


- ወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ

## ኢኮኖሚ 31



ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለምን ጠላት አበዛብን?

## መዝናኛ 44



የመጽሔታችን የአእምሮ መጠቅ
የአልበርት አነስታይን 20 ምርጥ
እይታዎችና መልካቦታዎች

# ርዕሰ አንቀጽ

## ፓርቲዎች የዴሞክራሲ ባሕል የሚዳብርበትን መንገድ ቀያሽ ሊሆኑ ይገባል!

በኢትዮጵያ ተደጋጋሚ ምርጫዎች ተካሂደዋል። በየጊዜው አሸንፌያለሁ የሚለው ገዥው ፓርቲ ነበር። ተቃዋሚዎች ለምን የማሸነፍ እድል አላጋጠማቸውም ብለን ብንጠይቅ የሚሰጡን መልስ መንግሥት ሳጥን ገልብጦ ውጤታችን ስለቀማን ነው ይላሉ። ይህ እውነት እንዳለ ሆኖ ግን ተቃዋሚዎች የአገሪቱን ተጨባጭ ሆኔታ ተገንዝበው በጋራ መቆም ባይችሉም የየራሳቸውን ፕሮግራም ይዘው አንዱ ሌላውን ድርጅት ሳይተነኩስ በያሉበት ተቻችለው ሕዝቡን አሰባስበው ለምርጫ ማቅረብ አልቻሉም ነበር።

ዛሬ ማሰብ የሚገባው ካለፈው ስህተት እንዴት እንማር የሚለው እንጂ ያለፈ ታሪክ መውቀጥ አያስፈልግም። ይህች ዓለም በሥልጣኔ ወደፊት እየገሰገሰች ነው። ጊዜያችሁን ተጠቀሙብኝ እያለች ነው። በተለይ በውጪ ዓለም የሚኖሩ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችና ደጋፊዎች በአጠቃላይ ዳያስፖራው ከሰለጠነው ዓለም ብዙ ነገሮችን መቅሰም ይችላል። በአገራችን የተጀመረው ለውጥ ዳር ደርሶ ዴሞክራሲ መሰረት እንዴጥል ከተፈለገ ጥርት ያለና ግልጽ አገራዊ ራዕይ ያላቸውና የተለያየ አስተሳሰብ የሚያራምዱ ጠንካራ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዴሞክራሲያዊ አሰራር ቢያንስ በራሳቸው መካከል በመለማመድ መጠናከር አለባቸው።

ሁሉም ወይም አብዛኛው አገር ወዳድ ወገን ሁሉ አሁን የሚታየው ግዴለሽና ራስ ወዳድነት ተወግዶ በሀገሩ ጉዳይ ያገባኛል የሚል አስተሳሰብ እንዴኖረው በማድረግ በኩል የፓርቲዎች ዋነኛ የቤት ሥራ ሊሆን ይገባል። የጠንካራ ድርጅቶች ጥያቄ ምላሽ ካገኘና ችግሮቻችን ላይ በጥሞና መነጋገር፤ መግባባትና መተባበር ከተቻለ የምንፈልገውን ሁሉ ለውጥ ማምጣት እንችላለን። ለመፍትሄዎቹ መንግሥት ብቻ ሳይሆን ወደ ሕዝቦችም ማየት ይኖርብናል። የችግሮቻችን መፍትሄዎች በእያንዳንዳችን እጆች ላይ እንጂ በፖለቲከኞች እና በመንግሥት ባለስልጣኖች እጆች ላይ አይደሉም።

ስለ ሃገራችን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ፓርቲዎች ለምርጫ ውድድር ከመዘጋጀት ባሻገር ብዙ ሊጫወቷቸው የሚገቧቸው ሚናዎች አሏቸው። የአባሎቻቸውን የደጋፊዎቻቸውንና የጠቅላላውን ሕብረተሰብ ንቃተ ሕሊና ማዳበርና ለትግሉም ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል። ፖሊሲያቸውን በሚገባ በማዳረስና በማስረዳት ሕብረተሰቡን ማስተማር አለባቸው። ክርክርና ውይይት በማዘጋጀት፤ በአስፈላጊ ርእሶች ላይ በመነጋገርና ሕዝቡንም ተሳታፊ ማድረግ ሁኔታዎችን እያነሱ ችግሮችን በማንሳትና መፍትሔዎችን በመጠቆም የሃገሪቱን የወደፊት ራዕይ መጠቆም አለባቸው። ሁኔታዎችን በማስተካከል የዴሞክራሲ ባሕል የሚዳብርበትን መንገድ ቀያሽ ሊሆኑ ይገባል። ፓርቲዎች ስኬታማ መሆን የሚችሉት ለወጣቱና ለሴቶች አስፈላጊውን የአመራር ስልጠና ለመስጠት ማቀድና መተግበር ሲችሉ ነው። ወጣቱ ትውልድ ታላቅ የመነሳሳት ፍላጎት፤ ቅልጥፍና፤ ቆራጥነት፤ በዓላማው ላይ መራመድን ይቀይሳል። ያንንም ተግባራዊ ለማድረግ ፈጣንና ቆራጥ ያደርገዋል። ስለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ፓርቲዎች ከሚዲያውና ከሲቪል ማህበረሰቡ ጋር በመሆን ተቀናጅተው ወደ ሕዝቡ መድረስ አለባቸው።

ሙሽራ መጣ ቁጠማ ..... እንዴሉ ፓርቲዎች ምርጫ መጣ ሲባል ካልሆነ በስተቀር አስቀድመው ሲዘጋጁ አይስተዋሉም። አንድ የፖለቲካ ድርጅት መሪ ትግሉን እመራለሁ ከማለቱ በፊት ከራሱ ባሕሪ ጋር መጀመሪያ ሙግት መግጠም አለበት። ሙግቱ ትግሉን ለመምራት ብቃቱን፤ ጥንካሬውን፤ መስዋዕት ለመሆኑ ቁርጠኝነቱን፤ ከግል ዝና መጽዳቱን፤ እውነተኛ ለሕዝብና ዴሞክራሲ የቆመ ስለመሆኑ ከሕሊናው ጋር ሙግት መግጠም አለበት። በተጨማሪም የነደፈው ፕሮግራም ምን ያህል ለአገርና ለሕዝብ ይጠቅማል? ሕዝቡስ ፕሮግራሙን ተቀብሎ መሠረታዊ ለውጥ እስኪመጣ ድረስ ከፓርቲው ጋር ይወግናል ወይ? ወዘተ ሊሟሉ የሚገባቸውን ነገሮች አስቀድሞ ማጤን ያስፈልጋል። ነገር ግን በይሁን ይሁን የመሪነት ሥም በመያዝ ለምርጫ መቅረብ መሠረታዊ ለውጥ ሊያስገኝ አይችልም።

**በዚህ ዓምድ ስር የሚስተናገዱ ፅሁፎች የፀሐፊውን አመለካከት እንጂ የዝግጅት ክፍሉን አቋም አይወክሉም።**

ነፃ ሃሳብ

## ለውዲቷ አገራችን አንድነትና ሰላም እናስብ፤ እንጨነቅ

**ጊዜው ያምራል**

በኢትዮጵያ እስካሁን አምስት ጊዜ አገር አቀፍ ምርጫዎች ተካሂደዋል። ከ1997 ዓ.ም ምርጫ በስተቀር በኢትዮጵያ እስካሁን የተካሄዱ ምርጫዎች የይስሙላ መሆናቸውን አብዛኞዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ይገልፃሉ። ቀጣዩ ሀገራዊ ምርጫ ሰላማዊ፥ ፍትሐዊና ነፃ ምርጫ ሆኖ እንዴጠናቀቅ ከ1997 ዓ.ም ምርጫ ብዙ መማር ያስፈልጋል።

እንደ 97 ዓ.ም ነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማድረግ ለሚመረጠው መንግሥት የህዝብ ተቀባይነት ያለው ጠንካራና የተገራ መንግሥት ይፈጥራል፤ አገርን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማሻገር ይችላል። በአንፃሩ በምርጫ መሸነፍን የሚቀበል መንግሥት ባለመኖሩና ሥልጣን ላይ ያለው አካል የምርጫ ኮሮጆ ወደ መገልበጥ በመሄዱ ውጤቱ እንዴበላሽ፤ ህዝቡ በብሔር እንዴቆሳሰል፤ በማህበረሰቡ ውስጥ ጠንካራ መተማመን እንዳይኖር አድርጓል። በአገራችን ዜጎች ላይ መዓት አውርዷል፤ ለእሥር፣ ለግድያና ለስደት ዳርጓል። ይህ ደግሞ ዴሞክራሲያዊ ሽግግሩን ከባድ አድርጎታል። ከዚህ ምርጫ አገራችን ተምራ ኢ- ዴሞክራሲያዊ አካሄድን የማትቀበልና የማትሸከም መሆኑን ያስተማረ ሆኖም አልፏል።

ከራሳችን በላይ ስለተጎዱት ጭቁን ወገኖቻችንና ለዉዴቷ አገራችን አንድነትና ሰላም እናስብ፤ እንጨነቅ። ስለአሁኑም ሆነ ስለሚቀጥሉት ትዉልዶች ፅጣ ፈንታ ማሰብና መጨነቅ ይኖርብናል፤ ራስ ወዳዶችና አፍራሾች ሆነን ሰይጣንን ከምንመግብና ወገኖቻችንን ከምናጠፋ በፍቅርና በአንድነት ብንቆም ይበጃል። ለማንም ከማይጠቅሙ አጉል ትርክቶች ነፃ እንሁን። ለሆድ ቅድሚያ መስጠቱ ይቁም። ሕይወት አጭር መሆኗን አንዘንጋ።

ቅድመ አያቶቻችን፤ አያቶቻችን፤ አባቶቻችንና እናቶቻችን በህብረት ከዉጪ ወራሪዎችና ከዉስጥ ጨቋኞች ሲከላከሉልን ዉድ ሕይወታቸዉን ገብረዋል፤ ደማቸዉን አፍስሰዋል፤ አጥንታቸዉን ከስክሰዋል። አገር ወዳድ ዕድሜ ልኩን ለዉድ አገር ይቆማል፤ ስላሁኑና ስለሚቀጥሉት ትዉልዶች ደህንነት ይጨነቃል። የነቃና አገር ወዳድ ወጣት ዘርና ሃይማኖት አይለይም፤ የግል ጥቅም አያስቀድምም፤ በህብረት ይቆማል፤ ይፀልያል፤ ይታገላል፤ አስፈላጊዉን መስዋእትነትም አብሮ ይከፍላል። አገር እናት ናት። እንደ እናት ደግሞ የሚወደድ፤ የሚፈቀርና የሚከበር አይኖርምና ቅድሚያ እንስጣት።

ከፋፋይ ቡድኖችና ግለሰቦች የሚረጩትን መርዞች አዉቆ ማርከስ ያስፈልጋል። አገራችን ኢትዮጵያ ናት። ሰላም ካለ ሁላችንንም በደስታ ታኖራለች። ስለዚህ ስለዉድ አገራችን አንድነትና ሰላም ሁላችንም የሚቻለንን አስተዋጽኦ እናድርግ። ወገንን በዘርና በኃይማኖት በመከፋፈልና በማጫረስ የሚገኝ ጥቅም ባፍንጫ ቢወጣ ይሻላል። አያዛልቅምና፤ ሰይጣናዊ ተግባር ነዉና።


**በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እየታተመ የሚወጣ**

**ዋና አዘጋጅ፡-** ሳሙኤል ይትባረክ
**ፖ.ሳ.ቁ፡-** 30145
**ስልክ፡-** 011-1264207
**ከፍተኛ አዘጋጆች፡-** ማለደ ዋስይሁን
ስሜነህ ደስታ
**አዘጋጆች፡-** የትናየት ፈሩ
ሀብታሙ ስጦታው

www.ethpress.gov.et
zemenpress@gmail.com

**ማስታወቂያና ደንበኞች አገልግሎት**
ስልክ፡- 011 1 56 98 73
ፋክስ፡- 011 1 57 44 40
**ማከፋፈያ፡-**
ስልክ፡- 011 1 57 02 70

**ሾፌን ዲዛይን**
ትዕግስት ሰይፉ
**ሌይአውት ዲዛይን**
ብርሃኔ ደመቀ፣ ሸዋዬ
አለማየሁ፣ ሣራ ገ/ማርያም፣
ልኬ አባተ
**ፎቶግራፍ፡-**
ዳኜ አበራ፣
ሐዱሽ አብርሃ፣
እዮብ ተፈሪ

# «በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ቦርዱ በፊት ከሚያደርገው በተለየ ሁኔታ የሚዲያ ክትትል ያደርጋል»

**- ወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ**



የትናየት ፈሩ

**ወይዘሪት ቡርቱካን ሚደቅሳ ቀደም ሲል የፌዴራል ፍርድ ቤት ዳኛ በመሆን አገልግለዋል። በኋላም የተቃዋሚ ፓርቲ አባልና አመራር ሆነው በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ጉልህ ተሳትፎ ማድረግ ችለዋል። በ1997 ዓ.ም በተካሄደው ምርጫ ማግስት በተፈጠረ ውዝግብ ምክንያት በተደጋጋሚ ለእስር ተዳርገዋል። በመጨረሻም የዕድሜ ልክ እስራት ተፈርዶባቸው ነበር። ከእስር ከተለቀቁ በኋላ ወደ አሜሪካን በማቅናት ከሐርቫርድ ዩኒቨርሲቲ በሕዝብ አስተዳደር ሁለተኛ ዴግሪያቸውን ይዘዋል። በሀገረ አሜሪካ ለሰባት ዓመታት ቆይተው በኢትዮጵያ የተካሄደውን ለውጥ ተከትሎ በ2011 ዓ.ም ወደ ሀገራቸው ተመልሰው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን እንዲመሩ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተሹመው ቃለ መሐላ ፈጽመዋል። በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን በሰብሳቢነት እየመሩ ከሶስት ወር በኋላ የሚካሄደውን ምርጫ ለማስፈጸም እየሠሩ ይገኛሉ። ዘመን መጽሔት ከወይዘሪት ቡርቱካን ጋር ያደረገችው ቆይታ እንደሚከተለው ቀርቧል።**

**ምርጫ ቦርድ እንደተቋም ያለውን የራስን ሥራ በራስ የመወሰን ሁኔታ ሳየው በጣም ያስገርመኛል**

**ዘመን ፡- እርስዎ ከዚህ ቀደም የፌዴራል ፍርድ ቤት ዳኛ ሆነው አገልግለዋል። ከዚያም የተቃውሞ ጎራውን ተቀላቀለው ከፍተኛ ተጋድሎ በማድረግ ስምዎን መትከል የቻሉ ፖለቲከኛ ሆነዋል። አሁን ደግሞ አስቸጋሪ በሆነ ወቅት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን በሰብሳቢነት እየመሩ ነው። ከአንዱ ኃላፊነት ወደ ሌላኛው ያደረጉት ሽግግር ምን ይመስላል ? በተለይ አሁን ያሉበትን የኃላፊነት ቦታ እንዴት አገኙት ?**

**ወይዘሪት ብርቱካን፡-** ሽግግሩ በረጅም ጊዜ በብዙ ዓመታት መካከል የሆነም ቢሆን የራሱ ውጣ ውረዶችና አስገራሚነቶች አሉት። የቀደሙትን ነገሮች ትቼ አሁን በኃላፊነት ምርጫ ቦርድ ላይ በምሠራብት ጊዜ ቀደም ሲል የፖለቲካ ፓርቲ በተለይም ደግሞ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ የመራሁ ሰው በመሆኔ የችግር ምክንያት የነበሩትን ብዙ ነገሮች እንደገና የማየት፣ እንደገና መመሪያዎችና ደንቦች የማውጣትና የማስተካከል ዕድል ይሰጣልና ይሄ በጣም ደስ ይለኛል። ብዙ ስናማርርባቸው የነበሩ ዝርዝር ነገሮች በአደባባይ ሌሎች ዜጎች የማያውቋቸው ግን የሚፎካከሩ ፓርቲዎችና ፖለቲከኞች ብዙ ማነቆ ሆኑብን የሚሏቸውን ነገሮች እንደገና ለማየት ዕድል ስለሰጠኝ በጣም ደስ ይለኛል። ከዛ ውጪ አሁን

ደግም አዳዴስ ፈተናዎች ስላሉ አንዳንድ ጊዜ ያለውን ዕድል ለማጣጣምና ልዩነቱንም ለማየት ጊዜ ላይሰጥ ይችላል። በየቀኑ የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፍታት ላይ በየቀኑ የሚያጋጥሙ አዳዴስ ተግዳሮቶችን ደግሞ መቋቋም ላይ እናተኩራልን። አንዳንድ ጊዜ ቆም ብዬ በተለይ ተቋሙ ካለው ገለልተኝነት አኳያ ውሳኔዎችን ለመስጠት፣ የራሱን ሥራዎች ለመወሰን፣ ከበጀት አንስቶ ከሥራ እንቅስቃሴው፣ ከሚቀጥራቸው ሰዎች፣ ከሚወስናቸው ውሳኔዎች እነዚህን ሁሉ ለማድረግ እንደተቋም ያለውን የራስን ሥራ በራስ የመወሰን ሁኔታ ሳየው በጣም ያስገርመኛል፤ ጥሩ ነገር ላይ አለን ብዬ አስባለሁ። በእርግጥ በአንድ ምርጫ ብቻ ተቋሙ በሚያደርገው ሁኔታ ሁሉ ነገር ይፈታል ብዬ አላምንም። ብዙ ምርጫዎች ማድረግ ይኖርበታል። በእያንዳንዱ ምርጫ የሚገኘው ነገር ትምህርት እየተወሰደበት፣ ይበልጥ እየተጠናከረ፣ በየምርጫዎቹ ደግሞ ከአንዱ ምርጫ በሚቀጥለው ምርጫ ከህዝቡ የሚያገኘው እምነት እየጨመረ ሄዶ በጣም ጥሩ መደላደል ያለው ጠንካራና ተዓማኒ የሆነ ተቋም ይሆናል ብዬ እንዳይ ያደረገኛል አሁን ያለሁበት ቦታ። ያለኝን ኃላፊነት ከዚያ አኳያ ነው የምመለከተው።

**ዘመን፡- ዘንድሮ የሚካሄደውን ስድስተኛ ሀገራዊ ምርጫ ከዚህ ቀደም ከተካሄዱት ምርጫዎች ልዩ የሚያደርጉት ነገሮች አሉ?**

**ወይዘሪት ብርቱካን፡-** በጣም በብዙ መንገድ ነው የሚለየው። የማቋቋሚያ አዋጁ እንደገና ተሰንዶ በፖለቲካ ፓርቲዎች ተሳትፎ ተጽፏል። የሚመሩት ሰዎች አሳታፊ በሆነ ሁኔታ በሙያቸው፣ ባላቸው ተአማኒነት፣ በሥራ ልምዳቸው እና በትምህርታቸው ተመርጠዋል። ከመነሻው ስንነሳ የምርጫ ህጉ ላይ ብዙ ማሻሻያዎችን አድርገናል። አሁንም መሻሻል አለባቸው የሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች አሉ፤ ወደፊትም ይበልጥ እናሻሽላለን ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ከዛ ውጭ እያንዳንዱን አሠራር እንደገና ፈትሸን ግልጸኝነትን እና ዘመናዊነትን ጭምር ተላብሶ የተቋቋመበትን ዓላማ በደንብ በስኬታማነት መፈጸም የሚችል ተቋም እንዲሆን ሊያደርጉ የሚችሉ አሠራሮች በሰፊው በሁሉም እንቅስቃሴዎቻችን ውስጥ አቅደን እየፈጸምን ነው የምንገኘው ያንን ለመፈጸም የምናወጣውን ገንዘብ የምናሰማራውን የሰው ኃይል ብታወዳድር፣ ለምሳሌ በፊት ለምርጫ ቦርድ ለአንድ የምርጫ ሂደት የሚመደበው ገንዘብና አሁን የተመደበው ገንዘብ ከመንግስት ብቻ እንኳን ቢታይ የሰማይና የምድር ያህል ነው። ይሄ የእንቅስቃሴውን ስፋት እና አዳዴስ ነገሮች መዘጋጀታቸውን ያሳያል።

ለማወዳደር ያህል 2007 ዓ.ም. የተደረገው ምርጫ የፈጀውን ገንዘብና የአሁኑን ከመንግስት የተበጀተልንን ገንዘብ ስንወስድ ወደ ሶስት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር መድቧል፤ ተጨማሪም እየመደበልን ነው። በ2007 ዓ.ም የተመደበው ወደ ሰባት ሚሊዮን ገደማ ነበረ። ሁለቱን ስናወዳድረው የአምስት ስድስት እጥፍ የበጀት ልዩነት አለ። የሰው ኃይልንም በተመለከተ በዋና መስሪያ ቤትም በክልሎችም በየሙያ መስኩ በአቅማቸው በጣም የበቁ የሚባሉ ባለሙያዎችን ማሰማራት ችለናል። በራሳችን ደግሞ ያልቻልናቸውን ነገሮች በዓለም አቀፍ ደረጃ በምርጫ ልምድ ያላቸውን ኤክስፐርቶች እንዲያግዙን አድርገን ብዙ አዳዴስ ነገሮችን እየተገበርን ነው ያለነው።

በሁሉም ነገር ይህ የሚታይ ነው። መራጮችን በማስተማር፣ በእጩዎች ምዝገባ፣ የመራጮች ምዝገባን በተሳለጠ ሁኔታ በማድረግና መብታቸውን በማረጋገጥ እንዲሁም ወደ ፊት ስንሄድ ዋናው ድምጹ በአግባቡ መሰጠቱና እውነተኛ በሆነ ሁኔታ ድምጹ መቆጠሩ ስለሆነ የምርጫው ቁልፍ፣ እዛ ጋር ደግሞ ስንደርስ የምንጠቀምባቸውን መንገዶችና አሠራሮች ያኔ የምናያቸው ይሆናሉ። ከድምጽ መስጫው ወረቀት ጀምሮ በፍጹም ሌላ ሰው ሊያባዛውና ሊያጭበረብር በማይችልበት ሁኔታ ደረጃውን ጠብቆ ይታተማል። ከዚያ ድምጽ አሰጣጡንም እንደዛው በታዛቢዎች በሚታይበት ሁኔታ አስፈጻሚዎቹም ገለልተኝነታቸው ተረጋ ግጦ በቂ ስልጠና አግኝተው የሚያስፈጽሙበት ሁኔታ እንዲኖር እናደርጋለን። ሂደቱ በሙሉ ተአማኒነትን፣ ግልጸኝነትን እና እውነተኝነትን በሚያረጋግጥ ሁኔታ እንዲደራጅ እያደረግን ነው የምንገኘው።

**ዘመን፡- አንዳንዶች ቀጣዩን ምርጫ ለማካሄድ ያለው ጊዜ አጭር ነው የሚል አስተያየት ይሰጣሉ። ጊዜው አጥሯል ማለት ይቻላል?**

**ወይዘሪት ብርቱካን፡-** ካጠረም ማጠር ያለበት ለእኛ ለአስፈጻሚዎቹ ነው። ያው የህዝብ ቁጥር ጨምሯል ኢትዮጵያ ትልቅ ሀገር ነች። ምን ብንዘጋጅበት ሁለት ዓመትም፣ ሶስት ዓመትም ቢሰጠን ለምሳሌ በእያንዳንዱ የምርጫ ክልል ምን አይነት የድምጽ መስጫ ወረቀት እንደምናሳትም ቀድመን ልናውቅ አንችልም። ምክንያቱም እዛ ምርጫ ክልል ላይ ስንት ተወዳዳሪዎች እንደሚመጡ አናውቅም፤ ስንት ፓርቲዎች እንደሚመጡ አናውቅም፤ እንዲሁም ስንት መራጮች እንደሚመዘገቡ አናውቅም። አሁንም በግምት ነው እያቀድን የምንሄደው። ስለዚህ የመራጮችና የተወዳዳሪዎች ምዝገባ አድርገን ካጠናቀቅን በኋላ በአርባ ቀናት ውስጥ መቶ ሚሊዮን ገደማ የድምጽ መስጫ አሳትመን ማድረስ አለብን። ይሄን እንዴት እንደምናከናውን የራሳችንን ብቃት ያለው ዝግጅት እያደረግን ነው። ስለዚህ ከአስፈጻሚ አንጻር አጠረ ማለት ይቻላል።

ሁል ጊዜም ምርጫ አስፈጻሚ አስቀድሞ ተዘጋጅቶ አቅዶ ዕቅዱ ደግሞ ሳንካ ሲያጋጥመው እያሻሻለ በፍጥነት ነው የሚሄደው። ሁልጊዜም ቢሆን የትም ሀገር፣ ካናዳም ብትሄድ ምርጫ አስፈጻሚ ሂደቶችን ቶሎ ቶሎ በጣም በአጣብቂኝ ሁኔታ ነው የሚፈጽመው። ምክንያቱም ምርጫ ማለት በጣም ብዙ ሂደቶችንና ክንዋኔዎችን የያዘ ብዙ ሰዎችን የሚያሳትፍ ትልቅ ፕሮጀክት ነው። ግን ደግሞ በግልጽና በፍጥነት ተደርጎ ድምጹ ተሰጥቶ ተቆጥሮ ወዲያው መገለጽ አለበት። ከአስፈጻሚ አንጻር ለዓመታት የተራዘመ ነገር ሊሆን አይችልም።

ከተወዳዳሪዎች አንጻር ብናየው የምረጡኝ ቅስቀሳ ማድረግ የሚችሉበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። ከሶስት ወር በላይ አላቸው፤ ከዚያ አንጻር ጠበበ ወይም አጠረ የሚባል አይደለም የሚሆነው። ከመራጮች አንጻር ደግሞ ብናየው መራጮች ከዚህ ቀደም በነበሩት ምርጫዎች የሚመዘገቡት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ነው። አሁን በተሻለ ሁኔታ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ብዙ መራጮችን ለመመዝገብ የሚያስችል ብቃት አለን ብዬ አስባለሁኝ። ጊዜው አጥሯል የሚለው ነገር አንዳንዴ ከምን አንጻር? የሚለው መጠየቅ አለበት እያንዳንዱ ሂደትም በራሱ መታየት አለበት። የውድድሩን ሁኔታ ወይም ለፓርቲዎች የሚሰጠውን ዕድል በተመለከተ አጥሯል የሚባ አይደለም። ከዚህ ቀደም በተደረጉ ምርጫዎች ከነበረው የምረጡኝ ቅስቀሳ ጋር የአሁኑ ቢተያይ እንደውም የኛ ሳይረዝም አይቀርም ባይ ነኝ። ስለዚህ በውድድሩ ጥራት ላይ ችግር በሚፈጥር ሁኔታ ያጠረ ጊዜ አለ ብዬ አላምንም።

**ዘመን፡- ብዙዎች ከዚህ ቀደም የተካሄዱት ምርጫዎች ዴሞክራሲያዊ፣ ፍትሃዊ እና ተአማኒ እንዳይሆን ከፍተኛ ሚና የተጫወቱት ስገዢው ፓርቲ የወገኑ የምርጫ አስፈጻሚዎች ናቸው ይላሉ። ዘንድሮ የሚካሄደው ምርጫ ከዚህ ችግር እንዲላቀቅ የተደረገው ዝግጅት ምን ይመስላል?**

**ወይዘሪት ብርቱካን፡-** የወገንተኝነት ነገር ግማሹ አስፈጻሚዎች ከፈጸሟቸው ወገንተኛ ከሆኑ ተግባራት ተነስቶ ሌላው ተሳታፊ የሚደርስበት ድምዳሜ ነው። ግማሹ ደግሞ በእይታ የሚመጣ ድምዳሜ ነው። ይህን ደግሞ ሁላችንም የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ ሁኔታ የምናውቅ ከሁለቱም አንጻር የወገንተኝነት ጥያቄ በቀደሙት አስፈጻሚዎች ላይ ይነሳ እንደነበረ እናውቃለን። ስለዚህ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከዚያ አንጻር የሚያቀርቡትን ጥያቄ ታሳቢ በማድረግ ከዚህ ቀደም ምርጫ ሲያስፈጽሙ የነበሩ ሰዎች አሁን በአስፈጻሚነት አይሳተፉም። በተለይ ለተወዳዳሪዎቹ መተማመኛ ለመስጠትና ከበፊቱ ልምድ የተነሳ ከእይታ አንጻር የሚኖርባቸውን ጥርጣሬ ለመቀነስ ብለን ያደረግነው ነው። ይሄን ስንል ግን በጣም ቀላል ውሳኔ ነው ማለት አይቻልም። ምክንያቱም እነዚያ ምርጫ አስፈጻሚዎች ብዙ ጊዜ ምርጫ ስላስፈጸሙ ከምርጫ ወረቀቶችና ህግጋቶች ጋር የተወሰነ መላመድ አላቸው። እነዚህን ክህሎት ያላቸው የቀድሞ አስፈጻሚዎች በተወሰነ ደረጃ እንዲሻሻሉ የሚያደርግ ስልጠና ሰጥተን ብንጠቀምባቸው ከአፈጻጸም አኳያ የተሻለም ነገር ሊያመጡ ይችሉ ነበረ። ነገር ግን የምርጫ ሂደት በተለይ ተሳታፊዎቹ ከአመኔታ አንጻር የሚያቀርቧቸው እንዲህ አይነት መሰረታዊ ጥያቄዎች እንዲሁ ወደ ጎን ሊባሉ የሚችሉ አይደሉም ብለን እንደ ቦርድ ትልቅ ውሳኔ ነው የወሰንነው።

የነበሩትን አስፈጻሚዎች ትተን ሌሎች አዲስ አስፈጻሚዎች ገለልተኝነታቸውን፣ ስልጠና የመውሰድ ችሎታቸውን እና የማስፈጸም አቅማቸውን አይተን መልምለናቸዋል። ከዚህ አንጻር ብዙ ዝግጅት አድርገናል። ነገር ግን ይህን ማድረግ ቀላል ነገር አይደለም። ሀገሩ ላይ ወደ 673 ቦታዎች የእጩዎች ምዝገባ እናከናውናለን። በእነዚህ ቦታዎች በሙሉ ሰዎች መመልመል ነበረብን። ከመንግስት ሠራተኛ፣ ከሲቪክ ማህበራት፣ ከወጣቶችና ከጡረተኞችም ሳይቀር የምንመለምልበትን ዘርፍ በጣም በማስፋት ብዙ አይነት ክህሎት ያላቸውን ዜጎች ከየዘርፉ ከየህብረተሰብ ክፍሉ ለማምጣት ሞክረናል። ከዚያ ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ ፖለቲካ ፓርቲዎች በአስፈጻሚዎች ገለልተኝነት ላይ አስተያየት እንዲሰጡ አድርገናል። በምንፈልገው መጠን ፓርቲዎች እከሌ የዚህኛው ፓርቲ አባል ነው



ማረጋገጫ መስጠት ሀሰተኝነት ይሆናል። በእኛ በኩል የምንችለውን ጥረት አድርገን ከማጣሪያ መንገዳችን ያመለጡ ሁለትም ሶስትም ሊኖሩ ይችላሉ።

ነገር ግን እነርሱን ደግሞ የማረሚያ መንገዶች አሉን። አቤቱታ የምንቀበልበትና እርምጃ የምንወስድብት መንገድ አለ። ታዛቢዎችም በስፋት ስለሚሰማሩ አስፈጻሚዎቹ የሚፈጽሙት ማንኛውም አይነት ስህተት ቢኖር ይመለከቱታል። ከዚያም በላይ ደግሞ ለአስፈጻሚዎቻችን በጣም ሰፊ የሆነ ስልጠና ሰጥተናል። ከስልጠና አኳያ ቀደም ሲል በነበሩት ምርጫዎች አንዳንድ ሰዎች ስልጠናም ሳይወስዱ ያስፈጽሙ ነበር። ስልጠናው የተወሰኑ አስፈጻሚዎች ጋ ብቻ ደርሶ ወደ ታች ሳይወርድ ይቀራል። አሁን ሀገሩ ላይ 23 በሚደርሱ ማዕከላት ስልጠናዎች አዘጋጅተን በብዙ ዙሮች እያሰለጠንን ነው የምንገኘው። ወደ መራጮች ምዝገባ ደግሞ ስንሄድ ስልጠናው በጣም ወደታች እየወረደ ብዙ እንቅስቃሴን እያቀፈ ይመጣል። እነዚህን ሁሉ ነገሮች የገለጽኩልህ አስፈጻሚዎች የሚኖራቸውን ብቃትና ገለልተኝነት ለማረጋገጥ ምን ያህል ርቀት ተጉዘን እንደሠራን ለማሳየት ነው።

**ዘመን፡- የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያደር ጉቸው የምርጫ ቅስቀሳዎች ግጭት ቀስቃሽ ሊሆኑ ይችላሉ በሚል ከወዲሁ ስጋታቸውን እየገለጹ ያሉ ወገኖች አሉ። ቦርዱ ፓርቲዎች በቅስቀሳ ወቅት በተለያየ መንገድ ለህዝብ የሚያሰራጯቸው መልዕክቶች ላይ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ አስተዳደራዊ እርምጃ ለመውሰድ ምን ያህል ተዘጋጅቷል ?**

**ወይዘሪት ብርቱካን፡** - እንግዴህ አሁን የምርጫ ቅስቀሳ በሚደረግበት ወቅት ቦርዱ በፊት ከሚያደርገው በተለየ ሁኔታ ሰፊ የሆነ የሚዲያ ክትትል ያደርጋል። ለዚህ የሰለጡኑ ሠላሳ የሚሆኑ ባለሙያዎች ቀጥሮ፣ የሚያስፈልጉ የቴክኖሎጂ ቁሳቁሶች ገዝቶ፣ አደራጅቶ ይህንን የሚዲያ መከታተያ የሥራ ክፍል ሥራ አስጀምሯል። ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ ጊዜ ውስጥ የሚያደርገው የፖለቲካ ንግግር ወይም ቅስቀሳ የሚገዛበት የሥነ ምግባር ድንጋጌዎች አሉ። እኛም ይሄንን እናስፈጽማለን። ፓርቲዎችም የፈረሙት የቃል ኪዳን ሰነድ አለ። ይህንን የሚያስፈጽሙት ራሳቸው ናቸው። እኛም ተከታትለን ይሄንን እንሠራለን። ፓርቲዎች ደግሞ ያጠፉትን ጥፋት በራሳቸው አሰራር የሚያርሙበት አሠራር ጭምር እንዳለ እያሳየን እንሄዳለን።

ሚዲያዎችን ክትትል/ሞኒተር/ ማድረጋችን አሁን ይጨምራል፤ ከምርጫው የቅስቀሳ ሂደት ውጪ «ማን፣ ምን አለ?» የሚለውን፣ የፖለቲካ ንግግራቸውን በየቀኑ የምንከታተልበት አሠራር የለም፤ የእርሱም ማንዴት (የኃላፊነት ወሰን) የሉብንም። አንዴ የቅስቀሳው ዘመቻ ከተጀመረ ግን ሂደቱን የሚያበላሽ፣ በቀላሉ ፉክክሩን የሚያቃውስ፣ ወደ ግጭት የሚመራ፣ መራጮች

እከሌ በዛኛው ፓርቲ ታቅፏል የሚለውን በማስረጃ አስደግፈው ሊያመጡልን አልቻሉም። ይሄ በጣም ጥሩ ልምምድ ነው ብዬ አስባለሁኝ፤ ምክንያቱም ድሮ ማንኛውም ፓርቲ አስፈጻሚው ማን እንደሆነ የሚያውቀው የምርጫው ዕለት ምርጫ ጣቢያውን ሲከፍት ሲያየው ነበር።

እኛ የምርጫ አስፈጻሚዎቹን እከሌን ሊደግፍ ይችላል ከሚባል ህብረተሰብ ክፍል ብቻ ሳይሆን ከብዙ ቦታዎች ስለሆነ የመለመልናቸው አሁን እነዚህ አስፈጻሚዎች ማን ናቸው? ምናልባት ያደሉብን ይሆን? በሚል ስጋት የሚገባቸው ተቃዋሚዎቹ ብቻ ሳይሆኑ ገዢው ፓርቲም ጭምር ነው። ይሄ ደግሞ መጥፎ ነገር አይደለም፤ ሁሉም በዚህ ሂደት ላይ ቁጥጥር እንደሌላቸው ነው ለእኛ የሚያሳየን። በሂደቱ እዚህም እዚያም ጥፋት ሊያጠፉ የሚችሉ አስፈጻሚዎች አልተመለመሉም መቶ በመቶ ከዚያ የጸዱ ናቸው ብሎ

**አሁን እነዚህ አስፈጻሚዎች ማን ናቸው? ምናልባት ያደሉብን ይሆን? በሚል ስጋት የሚገባቸው ተቃዋሚዎቹ ብቻ ሳይሆኑ ገዢው ፓርቲም ጭምር ነው**

ምርጫቸውን የሚገልጹበትን ሁኔታ የሚያጨናግፍ ሁኔታ ሊፈጠር ስለሚችል ሕጉም የሚያየው በተለየ ሁኔታ ነው፤ እኛም የምናየው በተለየ ሁኔታ ነው። ስለዚህ ክትትላችንም እርምጃ አወሳሰዳችንም በዚያው ልክ ከፍ ይላል ማለት ነው። ጨዋታው ሲጀመር የጨዋታው ሕግ ምን እንደሆነ፣ ንግግሮች ሲተረጎሙ ምን፣ ምን ማለት እንደሆነ ተወዳዳሪዎች እንዲያውቁት ግንዛቤ እናስጨብጣለን። ሕጎቹን ደንቦቹን በማስተዋወቅ ብዙ እንሠራለን፤ ዋናው እሱ ነው ብዬም አምናለሁ።



**ዘመን፡- በቅርቡ ብልጽግና ፓርቲን ስመደ ገፍ በተካሄዱ ሰልፎች ላይ በተንጸባረቁ ጉዳዮች ዙሪያ መግለጫ ሰጥታችኋል። መግለጫውን የምርጫ ቦርድን ገለልተኛነት ያሳየ ነው ብለው ያወደሱት አካላት የመኖራቸውን ያህል፣ ለዘብ ያለ ለስላሳ «የፍቅር ቁጣ» ሲሉ የሚገልጹት ወገኖችም አሉ። እነዚህ ወገኖች ሌሎች ፓርቲዎችም በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት መሰል ጥፋቶችን ቢፈጽሙ እውነተኛ የዴሞክራሲ ልምምድን «ሀ» ብለን መጀመራችን ነው በሚል ምርጫ ቦርድ ታጋሽ ይሆናል የሚል አስተያየት ይሰጣሉ። ስጋቶቹ እውን የሚሆኑ ከሆነ ምርጫ ቦርድ ሆደ ሰፊ ይሆናል ?**

**ወይዘሪት ብርቱካን፡-** በነገራችን ላይ እኛ ሕግ እንደሚያስፈጽም፣ በገለልተኝነት እንደሚሠራ ተቋም በዋናነት የሚመሩን በሕጉ ላይ የተቀመጡ ደንቦችና እንድናስተገብራቸው የተቀመጡ የአሠ ራር ሁኔታዎች ናቸው። የሚመሩን የሕዝብ አስተያየቶች አይደሉም። ምክንያቱም የሚሰጡ ውሳኔዎችን አንዱ ‹ገራገር› አድርጎ ሊያስብ ይችላል፣ ሌላው ደግሞ ‹በየት ሀገር ነው አንድን ሥልጣን የያዘ ወይም ገዢ የሆነን ኃይል ምርጫ ቦርድ የሚያርመው?› ሊል ይችላል። ነጥቡ ግን እርሱ አይደለም። የሰዎች አስተያየት እንደሚቆሙበት ሁኔታ፣ እንደሚያዩበት መነጽር ይለያያል። ስለዚህ ወደዚያ ገብቼ እንደዚህ ነው መታየት ያለበት ወደሚለው መሄድ አልፈልግም፤ ግን ገዢውም ሆነ ተቃዋሚዎች ማክበር ያለባቸውን የንግግር ስታንዳርዶች/ ሕጎች ማክበራቸውን ለማረጋገጥ የእኛ የሆነውን ኃላፊነት እንወጣለን።

አንዳንድ ነገሮች ወንጀል ነክ ሲሆኑ ደግሞ ምርጫ ቦርድ የሚያደርገው ነገር አይኖርም። ወደ ሕግ አስፈጻሚዎችም የሚሄድ ነገር አለ። ምርጫ ቦርድ የራሱን ገለልተኝነት የሚያረጋግጠው የራሱን ማንዴት በማወቅ፣ እርሱን የተመለከተ ነገር በማድረግና ከዚያ መስመር ደግሞ ባለመውጣት ነው። ምክንያቱም ሌሎች ተቋማት ደግሞ አሉ፤ የእነሱን ኃላፊነት መጋፋት አያስፈልግም። በራሳችን ማንዴት ላይ ብቻ እንሠራለን። ገና ወደ ውድድሩ ለመግባት ስንደራደር እንዲህ ዓይነቱ ነገር መታየት አልነበረበትም በሚል ቦርዱ አይቷል፤ በዚያም መሰረት መስጠት የነበረበትን ማስገንዘቢያ ሰጥቷል። በእርግጥ ያ፣ የድጋፍ ሰልፍ በሚካሄድብት ጊዜ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ጊዜ ውስጥም አልገባንም ነበረ።

**ዘመን፡- የምርጫ ቦርድን ገለልተኛነት ገና ከወዲሁ ጥያቄ ውስጥ የሚከቱ ፖለቲከኞች እየተደመጡ ነው። ለምሳሌ ኢንጂነር ይልቃል ጌትነት በቅርቡ ከአሃዱ ቴሌቪዥን ጋር ባደረጉት ቆይታ ፓርቲያቸው የተሰረዘው በመንግስት ትዕዛዝ መሆኑን ጠቅሰው ምርጫ ቦርድ በገዢው ፓርቲ እንደሚዘወር ገልጸዋል። ቦርዱ ከፖለቲከኞች ለሚሰነዘሩ እንዲህ ላሉ ስሙን ለሚያጎድፉ የአደባባይ ንግግሮች ምን አይነት ምላሽ ይሰጣል ?**

**ወይዘሪት ብርቱካን :-** የንግግር ነጻነት ለሁሉም ማለት ለፖለቲካ አመራር፣ ለሌሎች አደረጃጀቶች እንዲሁም ለዜጎች ሁሉ የተሰጠ መብት ነው። ግን እኛ እንደ ምርጫ ቦርድ ለእያንዳንዱ ክስ ምላሽ አንሰጥም። ምክንያቱም ብዙ ንግግር ባለ ቁጥር ብዙ ክሶች ሊኖሩ ይችላሉ። እንደ እኛ ዓይነት የንግግር ነጻነትን ተለማማጅ ለሆነ ማኅበረሰብ ደግሞ ብዙ ንግግር ሲመጣ፣ ብዙ የሚነገር ነገር ሲኖር፣ ብዙ ሃሳብ መስጠት ሲኖር ‹ያንን አይቼ በሞትኩ› ለምንል ሰዎች ጭምር እንኳን ‹እንዴ! ይሄ ነው እንዴ ለካ!› ሊያስብል የሚችልም ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም የንግግሩ መጨረሻ ይዘቱ ሲመዘን ትክክለኛነቱ፣ እውነተኛነቱ ብዙ ነገሮች ሲታዩ አሉታዊ ነገሮች ሊጎሉ ይችላሉ። ቢሆንም ግን የምንማረው በዚሁ መንገድ ነው። መጀመሪያ ብዙ መናገር፣ ከዚያ ደግሞ ትክክለኛ ነገር



መናገር የሚለውን በየጊዜው እያጠራነው የምንመጣ ይመስለኛል።

ለቦርዱም የምርጫ ሂደት፣ ለንግግር ነጻነትም ትልቅ አስተዋጽኦ ማድረግ ያለባቸው የሚዲያ ሰዎች ናቸው ብዬ አስባለሁ። የፖለቲካ ፓርቲዎችም ለምን እንደዚያ እንዳሉ፣ ክሶቻቸውን በማስረጃ እንዲያስደግፉ የማጣራት ኃላፊነት የሚዲያዎች ነው። እኛም ደግሞ እንደ ቦርድ ይሄንን ውሳኔ ስንሰጥ ‹በዚህ፣ በዚህ መንገድ ነው› ብለን ስንል የምርጫ ቦርድ ያለው ነገር ትክክለኛ መሆኑን አንዱን ደንብ ከሌላው ደንብ አጣቅሶ መርምሮ እውነተኛውን ነገር ለሕዝብ የሚያቀርብ ሚዲያ ሊኖረን ይገባል። ምክንያቱም ብዙ ጊዜ የሚያጋጥመኝ ነው፤ ‹የተባለው ልክ ነው?› እንባላለን፤ ግን ክሱን በሚያቀርቡ ጊዜ ክስ አቅራቢዎቹን ለምን እንደዚህ አላችሁ ወይም በመንግሥት ትእዛዝ ነው ሲባል መንግሥት በምን መልኩ ነው ትእዛዙን የሰጠው? ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል። መንግሥት ሲባል ገዢውን ፓርቲ የሚመለከተው ነው። ‹እውነት ገዢው ፓርቲ አሁን እንደ ተፎካካሪ የሚያያቸውን ፓርቲዎች እንደቀድሞው ለማጥፋት እየሰራ ነው ወይ?› ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል። ያን ማድረግ የፈለገበት ውሳኔ ነው ከተባለ ደግሞ የማጣራቱን ሂደት አልፈው በምርጫው ለመወዳደር እጩዎቻቸውን ያስመዘገቡት ፓርቲዎች ወደዚያ አይነት እርምጃ/ድምዳሜ የሚወሰዱ ናቸው ወይ ተብሎም መጠየቅ አለበት። እንደሚመስለኝ የቀሩት ፓርቲዎች ገዢውን ፓርቲ መፎካከር የማይችሉና ተቀናቃኝ ለመሆን አቅም የሌላቸው ናቸው የሚባሉ አይደሉም።

እኔ ስለፖሊሲያቸው ወይም ስላማራጫቸው በዚህም በዚያም ያሉትን መተቸት ሥራዬ አይደለም። ነገር ግን በአደባባይ የምናውቀው ነገር ነው። ምርጫ ተደርጎ ሁሉም ነገር እስከሚጠል ድረስ የትኛው ፓርቲ ምን ያህል የሕዝብ ድጋፍ አለው የሚለውን በእርግጠኝነት ለመናገር አይቻልም። ከላይ ባነሳነው የድጋፍ ሰልፍ ላይ በአንዳንድ በገዥው ፓርቲ ደጋፊዎች እንደጠላት የተቆጠሩ ፓርቲዎች የምርጫ ቦርድ ማጣሪያን አልፈው በህጋዊነት እንዲወዳደሩ እውቅና አግኝተዋል። ገዥው ፓርቲ አዝዞ ከሆነ፤ ወይም ገዥው ፓርቲ ለማጥፋት ፈልጎ በእኛ ሊጠቀም ትዕዛዝ አስተላልፎ ከሆነና እኛም ያንን ትዕዛዝ ተቀብለን እሺ ብለን ካስፈጸምን ዛሬ የማናያቸው በጣም በርካታ ፓርቲዎች መኖር ነበረባቸው።

የኢንጅነር ይልቃል ፓርቲ ኢ.ሀ.ን ነው። የእሳቸው ፓርቲ በዚህኛው ሳይሆን ቀደም ሲል በነበረው የመጀመሪያ ማጣሪያ በተሰጠው ጊዜ ምንም አይነት የድጋፍ ፊርማ ማቅረብ አቅቷቸው ፓርቲያቸው ከሂደቱ የወጣው ግልጽ በሆነ ሁኔታ ነው። እንኳን በእኛ ደረጃ የተቀመጠን ፖሊሲ የሚያስተረጉም ቀርቶ ማንንም ሰው አምጥተህ መመሪያውን አሳይተህ የእሳቸውን ፓርቲ ያልፋል ወይ? ብትለው አያልፍም ይልሃል። ምክንያቱም ሀገራዊ ፓርቲ አሥር ሺህ የድጋፍ ፊርማ ማምጣት አለበት። ይህ ግልጽና ግልጽ ነገር ነው። የእሳቸው ፓርቲ አስር ሺህ አላመጣም፤ አለቀ። የእኛ መከሰስ ምንም ችግር የለውም። የሥራው አንድ አካል ነው እንላለን። ክሶቹ ግን መጣራትና በማስረጃ መመዘን አለባቸው፤ ሰነዶች መታየት አለባቸው። በሚዲያዎች ጥሩ ጥሩ ጥያቄዎች ከተጠየቁ በየትኛውም ወገን የሚቀርቡ ክሶች እነዚያን ጥያቄዎች ማለፍ አይችሉም። እኔ እንደማስበው ጥሩ ጠያቂ መሆን፣ መማር አለብን። ጋዜጠኞች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች የሚዲያ ተጠቃሚዎችም /ዜጎች/ ጥሩ ጥያቄ መጠየቅ አለባቸው ብዬ አስባለሁ።

**ዘመን፡- በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋ ሚያ አዋጅ 1133/2011 መሠረት ለቦርዱ ከተሰጡት ስልጣኖች አንዱ ለምርጫ ታዛቢዎች ፈቃድ መስጠት እና መቆጣጠር ነው። ለድስተኛውን ሀገራዊ ምርጫ ለመ ታዘብ በመንግስት ግብዣ የቀረበላቸው አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ምርጫ ታዛቢዎች የትኞቹ ናቸው? የሀገር ውስጥና የውጭ የምርጫ ታዛቢዎች ላይ ቁጥጥር የሚካሄደውስ በምን መንገድ ነው?**

**ወይዘሪት ብርቱካን፡-** ለውጭ ታዛቢ እና ለሀገር ውስጥ ታዛቢ ፈቃድ የሚሰጥበት ምክንያት የተለያየ ነው። የሀገር ውስጥ ታዛቢ ምርጫን የሚታዘበው በመሠረታዊነት ምርጫን መከታተልና እውነተኝነት ማረጋገጥ የዜጎች መብት ስለሆነ ነው። ሁሉም ዜጎች መታዘብና መቆጣጠር ስለማይችሉ የዜጎችን መብቶች ሊያራምዱ ወይም ሊያስጠብቁ የሚቋቋሙ የሲቪል ማህበራት ያንን ሚና ይጫወታሉ። ስለዚህ በሕጉ በተቀመጡ ሁኔታዎች ገለልተኝነቱንና አቅሙን ማስረዳት የቻለ ማንኛውም ሀገር በቀል የሲቪል ማህበር ታዛቢዎችን መልምሎ ሊያሠማራ ይችላል። እኛ ደግሞ ያንን አይተን ፍቃድ እንሰጣለን፤ ይሄ አንዱ ነገር ነው። የሚመሠረትበት መነሻ ምክንያት በጣም ጠንካራ ነው። ከዜጎች መብት ጋር የሚያያዝ ነው። የሉዐላዊነትም መገለጫ ነው፤ የሀገር ውስጥ ትዝብት ዜጎች ደሃም ሆኑ ሀብታም፣ እከሌ ከእከሌ ሳይባል ያላቸውን መብት የሚገልጹበት ነው።

የውጭ ሀገር ታዛቢ ማለት ደግሞ የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ አካል እንደመሆናችን «አሠራራችን እንዴት እንደሆነ እዩልን» ተብሎ በእንግድነት /በግብዣ ጥሪ ተደርጎ/ የሚቀርብ ነው። በሀገራት መካከል የሚደረግ ግንኙነትን የሚመለከት ነው። ሕጉ ራሱ ምርጫ ቦርድ በቀጥታ የሚያስተዳድረው (የሚቆጣጠረው) ሳይሆን በውጭ ጉዳይ በኩል የሀገራችን መንግስት የሚፈቅደው ነው። በዚህ ሁኔታ ሲጋበዝ፣ የውጭ ታዛቢው የሚያሰማራቸውን ሰዎች እያንዳዳቸውን በምርጫ ቦርድ በኩል ገለልተኛነታቸውንና የመታዘብ ብቃታቸውን አይተን መታወቂያ እንሰጣለን። የውጭ ሀገር ታዛቢ መጥቶ ከእኛ ቀጥታ ፈቃድ ሊጠይቅ አይችልም፤ ምክንያቱም ሉዐላዊ ሀገር ነው። በዓለም አቀፍ መድረክ የተወከለ መንግስት አለ። የተጋበዘ

የውጭ ታዛቢ የሚያሟላቸውን መስፈርቶች፣ የሚጠበቅበትን ግዴታዎች፣ የሚኖረውን መብቶች የሚገልጽ በዓለም አቀፍ የሚታወቅ ስታንደርድ አለ። ያንን የማስፈጸምና ያንን በተከተለ ሁኔታ ትዝብታቸውን እንዲያደርጉ፣ ሃሳባቸውን እንዲገልጹ የማድረግ ኃላፊነት ወደ እኛ ይመጣል። በሁለቱም ዙሪያ ጥሩ ነገር አለ ብለን እናስባለን።

የአሜሪካ መንግስት ታዛቢ እንዲልክ ግብዣ ቀርቦለታል፤ የአፍሪካ ህብረትም በቻርተሩ መሠረት ይታዘባል። የኢትዮጵያ መንግስት የአፍሪካ ህብረትን መጋበዝ ግዴታው ነው። ሌሎችም ዓለም አቀፍ ማህበራት፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ምርጫ ላይ የሚሠሩ ሊጋበዙ ይችላሉ ብለን እናምናለን። ‹ለዚያ የሚያስፈልገን የሕግ አሰራር፣ የምንሰጠውን የድጋፍ አይነት ምንድነው የሚለውን በተመለከተ ልናደርገው የምንችለው ዝግጅት ምንድን ነው?› ብለን በዚያ ላይ እየሠራን ነው።

የሀገር ውስጥ ታዛቢዎችን በተመለከተ ጥሪውን አቅርበን፣ መመሪያውን አስተዋውቀን፣ በጣም በርካታ ማህበራት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ታዛቢዎችን ለማሰማራት ጥያቄ አቅርበውልናል። ከሁለት መቶ በላይ ሀገር በቀል ማህበራትን ደግሞ ሕጉ ላይ በተቀመጠው መስፈርት መዝነን ፈቃድ እንሰጣለን። ለእኔ በግሌ በጣም ደስ ከሚሉኝ ነገሮችና ለምርጫ ሂደቱ ጥሩ ነገር ነው ብዬ ከምኮራባቸው ነገሮች የሲቪል ማህበራት ተሳትፎ ነው። በ1997 ዓ.ም. ይህን ተግባር ሊፈጽሙ የሞከሩ ሀገር በቀል የሲቪል ማህበራት ታግደው ነበር። የታገዱት አለአግባብ ነው ‹ወገንተኞች ናችሁ፣ የፖለቲካ ዝንባሌ አላችሁ› ተብለው ነበር። አሁን ግን የሚጠበቅባቸው ለሁሉም ማህበራት ክፍት ሆኖ በሕግ የተቀመጠውን ነገር ማሟላት ብቻ ነው። በጣም ሰፊ የሆነ የሀገር ውስጥ ታዛቢዎች ድርሻ ይኖራል ብዬ አምናለሁኝ። እሱ ደግሞ ሂደታችንን በየቦታው የሚመለከት ዐይን እንዲኖር ያደርግልናል።

**ዘመን፡- የፖለቲካ ፓርቲዎች ለቦርዱ ሲያቀርቧቸው የነበሩ ችግሮች በተገቢው መንገድ እየተፈቱ መጥተዋል ብለው ያምናሉ? በተለይ ደግሞ በነጻነት ከመንቀሳቀስ ጋር ተያያዘው የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ምን ያህል ርቀት ሄዳችኋል ?**

**ወይዘሪት ብርቱካን፡-** እኛ በራሳችን በጣም አስቻይ የሆኑ ነገሮችን ለመፍጠር፣ የበለጠ አዳማጭ ቦርድ ለመሆን፣ የበለጠ ተገኝ ለመሆን ማድረግ የምንችላቸውን እያደረግን ነው። ቅሬታዎችን የምንሰማ፣ በሂደት ደግሞ ያሉንን ውሳኔዎች ከየፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር የምንማከር እንድንሆን፣ ለሁሉም ፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ቅርብ ለመሆን በጣም ብዙ ሥራዎች ሠርተናል።

አንዳንዶቹ ቅሬታዎች በጣም ብዙ ነገሮችን የሚዳስሱ ይሆናሉ። ለምሳሌ ይሄንን ያህል ሺህ ሰው ታስሮብኛል ብለው ቅሬታ የሚያቀርቡ ፓርቲዎች አሉ። በፍርድ ቤት የተያዘ ይሆናል፣ እያንዳንዱን ክስ ይዞ ለምን ተያዘ ለማለት በጣም ያስቸግራል። ያም ቢሆን ግን አላግባብ የታሰረ፣ አቃቤ ሕግ ክስ የመሠረተበትና ፖሊስ ያጣራበት ሊኖር ይችላል፤ በእርግጠኝነት ይኖራል። ገዥው ፓርቲ እና ቅሬታ አቅራቢ ፓርቲዎቹ ተነጋግረው መፍትሄ እንዲያበጁ፤ አብረው ደግሞ እንዲያጣሩ ብዙ ሞክረናል። ሂደቱ በፈለግነው ፍጥነትና

**ፖለቲካው ብዙ ጊዜ የመጠቃቃት ምክንያት፣ አንዱ አንዱን የማጥፋት፣ የመታሰር የመፈታት እና ሕይወትን የማጣት ሆኖ ለብዙ ዓመታት ስለቆየ ገና አንድ ነገር ሲሆን ፍጹም ጥርጣሬ ውስጥ መግባት ስለሚኖር ትንሽ ነገር ወደ ትልቅ የፖለቲካ ችግርነት ሲሄድ ይችሳል፤**

ጥራት ባይሄድም በእኛ በኩል ግን መሞከር ያለብንን ሁሉ ሞክረናል።

አንዳንዶቹ ላይ እውነት ለመናገር ውጤት አይተናል። ለምሳሌ ቤንሻጉል ጉሙዝ ክልልን ብንውሰድ በጣም በርካታ አቤቱታ ከሚቀርብባቸው ክልሎች አንዱ ስለሆነ የሶስትዮሽ መድረክ አዘጋጅተን የፓርቲዎች ቅሬታ ስንሰማ ቆይተናል። ከዚያም ከክልሉ መንግስት ፕሬዚዳንት ጀምሮ ቅሬታዎቹን አቅርበንላቸዋል። እዛ አካባቢ የሚለየው ነገር አንዳንድ ጊዜ የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ዋና ዋና መሪዎች ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ይታሰራሉ። ለምሳሌ “ቦሮ” የሚባለውን ፓርቲ ብንውሰድ ሊቀመንበሩም ምክትሉም ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ታስረው የቆዩባቸው ጊዜያት አሉ። ከአንደኛው ክስ ነጻ ሲሆኑ፣ ወደ ሌላ ክስ ሲሄዱ ያየንበት ሁኔታም አለ። ይሄን በመንተራስ በጣም ብዙ ግፊት ስናደርግ ቆይተን በመጨረሻ የፓርቲውን አቤቱታ ወደ ፌዴራል አቃቤ ሕግ መርተነዋል። የፌዴራል አቃቤ ሕግ ጉዳዩን አይቶ የቦሮ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ላይ የተመሰረተው ክሱ እንዲቋረጥ ትዕዛዝ ሰጥቷል። መሰል ተጨማሪ ጉዳዮች አሉ ስለተባለ ገዥውና ተቃዋሚ ፓርቲዎቹ ቡድን አቋቁመው ወደ ክልሉ ልከው ሊያጣሩ ተስማምተዋል። የምርጫ ቦርድ ተወካይ ማለትም የእኔ ምክትል በቦታው ላይ ከቡድኑ ጋር በመሄድ ሁኔታውን እንዲከታተሉ ወስነናል።

ሌሎች ፓርቲዎችን በተመለከተ እንዴሁ እዚ ህም፣ እዚያም በተለይ ጽህፈት ቤት በመክፈት እና እንቅስቃሴ ከማድረግ ጋር በተያያዘ ያሉ ችግሮችን ለማቃለል ሞክረናል። አሁን ደግሞ የምረጡኝ ቅስቀሳዎች ሲጀምሩ አቤቱታዎቹ ሊጨምሩ ይችላሉ። እኛም ደግሞ በራሳችንና ከሌሎች የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር የበለጠ ምላሽ መስጠት የምንችልባቸው ሁኔታ መኖር አለባቸው። ምክንያቱም የምርጫ ውድድር በጣም በፍጥነት የሚሄድ ነገር ነው። አንድ ፓርቲ እዚህ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ተከለከልኩኝ፣ እዚያ ደግሞ ስቴዴዮም ተከለከልኩኝ እያለ ሶስት ወር ሊቆይ አይችልም። ውሳኔው የሚዘገይ ከሆነ ለነገሩ ምላሽ የሚሰጠው ምርጫው ካለፈ በኋላ ይሆናል። ስለዚህ የፓርቲዎች የጋራ መድረክን ጨምሮ ምላሽ የምንሰጥባቸውን የአሠራርና የትብብር ማዕቀፎች በደንብ ማቋቋም አለብን።

በእኛ በኩል ችግር ፈቺ ለመሆን ዝግጁዎች ነን። ፓርቲዎችም ችግር ፈቺ ለመሆን ዝግጅት ማድረግ አለባቸው። ብዙ ዝርዝር ውስጥ መግባት ባልፈልግም አንዳንድ ጊዜ ተቃራኒውን አያለሁ። ግማሹ ካለፍንበት መንገድ የመጣ ነው። ፖለቲካው ብዙ ጊዜ የመጠቃቃት ምክንያት፣ አንዱ አንዱን የማጥፋት፣ የመታሰር የመፈታት እና ሕይወትን የማጣት ሆኖ ለብዙ ዓመታት ስለቆየ ገና አንድ ነገር ሲሆን ፍጹም ጥርጣሬ ውስጥ መግባት ስለሚኖር ትንሽ ነገር ወደ ትልቅ የፖለቲካ ችግርነት ሊሄድ ይችላል። በሁሉም በኩል ችግር ፈቺዎችና መፍትሄ ሰጪዎች መሆን ይኖርብናል። የዚህ ሂደት ስኬት ደግሞ በሁላችንም አስተዋጽኦ የሚሆን ነገር እንደሆነ መርሳት አያስፈልግም እላለሁ።

**ዘመን፡- ከፍተኛ የስራ ጫና ባለበት ወቅት የተጣበበ ጊዜዎን አብቃቅተው ከመጽሔታችን ጋር ቆይታ ስለአደረጉ እናመሰግናለን።**

**ወ/ሪት ብርቱካን፡-** እኔም አመሰግናለው

በድርጅቱ ውስጥ የነበሩ እስከ ኮሉኔልነት ማዕረግ የነበራቸው ታስረው ብዙ ስቃይ ያዩ ወዳጆች ነበሩኝ። ሄዶ፣ ሄዶ ተሳትሞ በራሱ ጊዜ እንደሚጠፋ ይነግሩኝ ነበር፤



# «የስብሃት ቤተሰብ ከሱር ኮንስትራክሽን ብቻ በዓመት 100 ሚሊዮን ዶላር ከአገር ያስወጣ ነበር!»

- ጋዜጠኛ አርአያ ተስፋማርያም

የትናየት ፈሩ

አቶ አርአያ ተስፋማርያም ጋዜጠኛ ነው። ከ1990ዎቹ መጀመሪያ አንስቶ ሪፖርተርን ጨምሮ በተለያዩ ጋዜጦች ላይ ሰርቷል። ወደ ሙያው የተሳበበትን ሁኔታ ሲገልጽ «በሰማንያዎቹ አጋማሽ ይወጡ ከነበሩ ጋዜጦች ቁጥር አንድ ምርጫዬ "ጦማር' ጋዜጣ ነበረች:: "የአራዳ ሹክሹክታ' የምትለው ቅልብጭ ያለችና አጭጭር መረጃ የምታስኮመኩመው አምድ አትረሴ ናት:: ወደ ጋዜጠኝነት እንዳዘነብል ያደረገችኝ "ጦማር' ጋዜጣ ናት። በተለይ ሳላውቀው ወደ ሙያው የሳበኝ የማከብረው፣ የማደንቀው፣ ልዩ ቦታ የምሰጠው ጋዜጠኛ በፍቃዱ ሞረዳ ነው» ይላል። ጋዜጠኛ አርአያ በይበልጥ የሚታወቀው ከ1994 ዓ.ም አንስቶ በኢትዮጵ ጋዜጣ ላይ «ከህወሓት መንደር የቃረምኩት» በሚል አምድ ስር ያወጣቸው በነበሩት ጽሑፎቹ ነው። ዘመን መጽሔት ከዚህ አንጋፋ ጋዜጠኛ ጋር ያደረገችው ቆይታ እንደሚከተለው ቀርቧል።

« አምስት ፌዴራል ፖሊሶች ከኋላ መጥተው አናቴን መቱኝ። ከፊት ያሉት ተቀበሉኝ። ሶስት ጥርሴ ረገፈ። ከዚያ ድልድይ ውስጥ ተወረወርኩ። የፈለጉት ጅብ እንዲበላኝ ነበር»



**ዘመን፡- አንተ ትታወቅ የነበረው «ኢትዮጵ» ጋዜጣ ላይ «ከህወሓት መንደር የቃረምኩት» በሚል አምድ ስትጽፋቸው በነበሩ ጽሑፎች ነው። አምዱን ለመጀመር መነሻህ ምን ነበር?**

**አቶ አርአያ፡-** አምዱን ለመጀመር ያነሳሱኝ በህወሓት ታጋዮች ላይ ይፈጸሙ የነበሩት ግፍና በደሎች ናቸው። ህወሓት ሥልጣን ላይ ከወጣ በኋላ 1984 ዓ.ም ግምገማ በሚል 36 ሺ ታጋዮችን አባረረ። የዚያን ጊዜ ተማሪ ሆኜ እነዚህን መረጃዎች እሰበስብ ነበር። የህወሓት ክፍፍልን ተከትሎ እሰራበት ከነበረው ከሪፖርተር ጋዜጣ ከለቀቅኩ በኋላ 1994 ዓ.ም መስከረም ሁለት ኢትዮጵ ጋዜጣ ላይ መጻፍ ጀመርኩኝ። በተከታታይ በየሳምንቱ ጽሑፎችን ሳወጣ ነበር። እንደነገርኩህ መነሻዎቹ 36 ሺዎቹ ታጋዮች ናቸው። 1 ሺህ 500 የሚሆኑ ታጋዮች በሆለታ እስር ቤት ውስጥ እንዶድ የተባለ መርዝ ጠጥተው ሞተዋል። በታጠቅ ሁለት ሺህ በሳንባ ተላላፊ አልቀዋል። 14 ሺህ ጎዳና ያድሩ ነበረ። የእነዚህን ታሪክ ከጨረስኩ በኋላ በህወሓት፣ በደህንነት፣ በመከላከያ እና በተለያዩ ተቋማት ይፈጸሙ የነበሩ የወንጀል ድርጊቶችንና ሙስናዎችን ወደ ማጋለጥ ገባሁ። መረጃዎችን አገኝ የነበረው መከላከያ፣ ደህንነት፣ የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ውስጥ እና ሲቪል ሰርቪስ ውስጥ ካሉ ሰዎች ነበር።

**ዘመን፡- በ «ኢትዮጵ» ላይ በምታወጣቸው ጽሑፎች ካጋለጥካቸው በህወሓት የተፈጸሙ ሴራዎች፣ ግድያዎች እና ዘረፋዎች መካከል ይበልጥ ዋጋ የሰጠኸው የትኛውን ነው?**

**አቶ አርአያ፡-** ብዙ ናቸው በተለይ ግን የታጋዮቹን ስቃይና መከራ ማጋለጤ ደስ ይለኛል፤ ምክንያቱም በድርጅቱ ስም ነበር። ሁለተኛ በድርጅቱ ውስጥ የነበሩ እስከ ኮሎኔልነት ማዕረግ የነበራቸው ታስረው ብዙ ስቃይ ያዩ ወዳጆች ነበሩኝ። ይሄ ፓርቲ (ህወሓት) ሄዶ፣ ሄዶ ተላትሞ በራሱ ጊዜ እንደሚጠፋ ይነግሩኝ ነበር። 'ዘንዶ የተራበን ዘንዶ ሲውጠው በጣም ተጠንቅቆ ነው፤ ምክንያቱም ያኛውም ሊበላው ስለሚችል እርምጃ የሚወስድበት ቶሎ ነው። ልክ እንደ ዘንዶዎች ይዋዋጣሉ' ይሉኝ ነበር። ሀጎስ ገብረሕይወትም በዘፈኖቹ 'እንደ ትናንቱ ነገም እንፋረዳቸው' እና 'በጠዋቱ እረፉ ብለን ነበር' እያለ ከ18 ዓመታት በፊት ያቀነቀናቸው ሀሳቦች በሙሉ ተፈጽመዋል። ይህ ሲሆን በማየቴ በጣም ተደስቻለሁ። ሀጎስ ይህን ሳያይ መሞቱ ግን በጣም ያሳዝነኛል።

**ዘመን፡- ህወሓት የሚፈጽማቸውን ግፎች ጋዜጣ ላይ በመጻፍህ ምን ዓይነት ችግሮች ደርሰውብሃል?**

**አቶ አርአያ፡-** በ1995 ዓ.ም ከፖሊስ መረጃዎች ደርሰውኝ የቴሌ ኮሚዩኒኬሽንን መረጃ ማጋለጥ ተያያዝኩኝ። ያንን ይፈጽሙ የነበሩት በሕይወት የሌለው ኢያሱ በርሄ እና አዜብ መስፍን ናቸው። ኢያሱም ራሱ አምኗል። 38 ሰዎች ነበሩ፤ ከዚያ በኋላ እኔን ማሳደድ ተጀመረ። ቢተው በላይ የሚባል የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልም ታስሮ ነበር። ሚስቱ ዝማም ትባላለች፤ ባሏን አሳሰራ የደህንነት ሹም ከነበረው ከወልደሥላሴ ጋር ትፈጽማቸው የነበሩ ነውረኛ ድርጊቶች ነበሩ። እሷ ናት የጠቆመችኝ። 'ኢየሩሳሌም አርአያ ይባል እንጂ ወንድ ነው፤ የሚኖረው ቤላ ነው፤ ቤቱን ግን አላውቅም' አለቻቸው። ኃይሌ የሚባል ሰው ስድስት ወር ሙሉ አስጨነቀኝ። 'መረጃዎችን ማነው የሚሰጥህ? ገንዘብ እንስጥህ፤ 400 ሺህ ብር ከዚያ በኋላ ከአገር እንድትወጣ እናደርግሃለን' የሚሉ መደራደሪያዎች ነበሯቸው፤ እኔ ግን አልተቀበልኩም። አብረዋቸው የታገሉ ታጋዮች ላይ ያንን ሁሉ ግፍ እስር ቤት ውስጥ የፈጸሙ ለእኔ መረጃ የሚሰጡኝን ሰዎች ሲያገኙ ምን ሊያደርጓቸው እንደሚችሉ አስብ። በገባሁበት፣ በወጣሁበት ጎንበስ እያሉ ሽጉጥ ያሳዩኛል። እኔ ግን እንደዚያም ሆኖ እነሱ ከሚጠረጥሩት ውጪ በተለያየ መንገድ መረጃዎቹን አገኝ ነበር።

ስድስት ወር በጣም አስጨነቀኝ ከዚያ በኋላ ይሄ እንደማይሆን ስነግረው መስከረም ሁለት ቀን ትግራይ ልማት ቢሮ ተጠራሁ። የዚያን ጊዜ የትግራይ ልማት ቢሮ ዳይሬክተሩ ተስፋጽጌ አበራ ይባላል። አባቴና የእሱ አባት ወንድማማቾች ናቸው፤ የአጎቴ ልጅ ማለት ነው። እንግሊዝ አገር ነበር። 1994 ዓ.ም አምጥተው ዳይሬክተር አደረጉት። ከእነሱጋ ሲሰርቅ ሲመዘብር የኖረ ነው። ያው ከወልደሥላሴ ጋር አገናኙኝና ሁለት ሰዓት ሙሉ አስፈራራኝ። እስከ አንድ ሚሊዮን ብር እንደሚሰጡኝና ከአገር ልወጣ እንደምችል ነገረኝ። አንዴ 'የአድዋ ሰው ነህ' ይለኛል፤ አንዴ ደግሞ በቤተሰብ ሊያግባባኝ ሞከረ። ከዚያም 'ፕሮፌሰር መስፍን እና ክፍሌ ሙላት አያድኑህም' አለኝ። ክፍሌ ሙላት በወቅቱ የኢትዮጵያ ነፃው ፕሬስ ፕሬዚዳንት ነበር። ነፍሳቸውን ይማርና ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ደግሞ የኢሰመጉ ፕሬዚዳንት ነበሩ። ይሄን ካለ በኋላ ‹‹ብንገልህስ!›› አለኝ። ‹እንግዴህ እኔ ከጀርባዬ መሣሪያ የለም፤ ያለው እስክርቢቶ ነው፤ አሁኑኑ ልታደርገው ትችላለህ፤ 36 ሺህ ታጋዮች እኮ! ለቤተ መንግሥት አብቅተዋችሁ መጨረሻ ላይ ሜዳ ላይ ጥላችኋቸዋል፤ ግማሾቹን እስር ቤት› ስለው ‹‹ምናገባህ!›› ብሎ ጮኸብኝ። ‹አይ! እኔ ያገባኛል፤እንደ ሰው ሳስበው እንደዚያ ተሰቃይተው ሲሞቱ ዝም ማለት አልችልም› አልኩት። ‹‹እንዳንተ እሹሩሩ ያልነው የለም፤ ለማንኛውም 15 ቀን ጊዜ ሰጥተንሃል›› አለኝ። ‹በ15 ዓመትም ሀሳቤን አልቀይርም› አልኩት።

1996 ዓ.ም መስከረም 20 ቀን ረቡዕ ማታ ወደ ቤቴ ስገባ ቤላ ቀበሌ 18 አቦ ድልድዩ ጋር ያደፈጡ ፌዴራል ፖሊሶች ነበሩ። አምስቱ ከኋላ መጥተው አናቴን ፈነከቱኝ ከፊት ያሉት ተቀበሉኝ። ሦስት ጥርሴ ረገፈ። ከዚያ ድልድይ ውስጥ ተወረወርኩ። የፈለጉት ጅብ እንዲበላኝ ነበር፤ ምክንያቱም በአካባቢው ማታ ማታ መንጋ ሆኖ ነበር የሚሄደው። ደሜ ይፈስ ነበር፤ ታፋዬ ተሰነጠቀ፤ መቆም አልቻልኩም። ከዚያ ባትሪ አብርተው አዩኝ። ሞቷል ሲሉ በሰመመን ስማኋቸው። መጨረሻ ላይ በማንም ሳይሆን በእግዚአብሔር ጥረት ደሜ እየፈሰሰ፣ በዚያ ቆሻሻ የሚጣልበት ዳገት መሬት ለመሬት እየተንፏቀቁ፣ ሄጄ ሰው ቤት ደረስኩ። ከዚያ በኋላ መብራት ሳይ ምን እንደሆንኩኝ አላስታውስም። በእነርሱ እርዳታ ተሰፍቼ፤ ሁሉ አካሌ ሕክምና እየተደረገለት፤ በኋላ ምኒልክ ሆስፒታል ራሴን አገኘሁት። በማግስቱ አስወጡት ተባለ። ለአዘጋጁ ሲሳይ አጌና ደውለው 'ኢየሩሳሌም አርአያን ፈልገን ነበር' ሲሉት ለሥራ ወጥቷል ሲላቸው ምኒልክ ሆስፒታል ሄደህ ሬሳውን ውሰድ' አሉት። ይሄንንም በጋዜጣ ላይ ጽፎት ነበር።

ያው እንግዴህ ስድስት ወር የአልጋ ቁራኛ ሆንኩ። ሀኪም ቆመህ ትሄዳለህ ያለኝ በሁለት ዓመት ነበር። ታፋዬ ላይ መሰንጠቅ ስለነበረ ስድስት ወር በጀርባዬ ብቻ ተኛሁ። ይህን ያህል ጊዜ ሳትገላበጥ በጣም ይከብዳል፤ ሆኖም በሁለት ዓመት ይወስዳል የተባለው በስድስት ወር ቆሜ ሄድኩኝ። ነገር ግን አሁን እነሱ ባደረሱብኝ ጉዳት ነርቭ ያመኛል።



የእነ ወልደሥላሴ ጭካኔ ከዚህ በላይ ነበር። እኔ የተረፍኩት በእግዚአብሔር ተአምር ነው፤ ዳግም ነው የተወለድኩት።

**ዘመን፡- ከዚያ በኋላስ ጋዜጣ ላይ በመጻፉ ቀጥለህ ነበር? ከአገርስ የወጣኸው እንዴት ነው?**

**አቶ አርኣያ፡-** አዎ! የ1997ን ምርጫ ተከትሎ ጋዜጣው እስከተዘጋ እስከ ጥቅምት 1998 ዓ.ም ድረስ እጽፍ ነበር። ከዚያ በኋላም የተባለው ‘ቀጥቅጣችሁ ጣሉት’ ነበር። እኔ ግን ወደ ሐረር ሄጄ ተደበቅኩኝ። ከዚያ በኋላ ልጄ ታመመች። ኢየሩሳሌም የምትባል ታዳጊ ልጅ አለችኝ። ‘የውጭ ሕክምና ያስፈልጋታል፤ ካልታከመች ፓራላይዝድ ትሆናለች’ ተባለ። ብዙ ጥረት ካደረግኩ በኋላ በዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ እገዛ 10 ሺ ዶላር ድጋፍ ተገኝቶ፤ ወደ ሕንድ ሄድን። ሁለት ጊዜ ቀዶ ጥገና አድርጋ በዚያ ከቆየን በኋላ ወደ አሜሪካን ሄድን። ዶክተር ነጋሶ በጣም ባለውለታዬ ናቸው፤ በጣም ጥሩ ሰው ናቸው። ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም ሰው እንደዚህ ነበሩ። ባለፈው ዓመት ልናመሰግናቸው ወደዚህ አገር ስንመጣ በስልክ ተገናኝተን ‘ወደ አያቶቼ አገር ደርሼ እመጣለሁ’ ብለው ሄዱ፤ ያው ሬሳቸው መጣና ሳናገኛቸው፣ ሳናመሰግናቸው ቀረን። እኔ ብወልዳትም ኢየሩስን ሕይወት የዘሩባት እሳቸው ናቸው፤ ከአገር አወጣጣችን እንደዚህ ነው።

**ዘመን፡- ህወሓት ሲነሳ የማፈኛ ፣ ማሰቃያ እና መግደያ ቦታዎች አብረው ይነሳሉ። አንተም እነዚህን ቦታዎች ታነሳቸዋለህ። እንደ ምርመራ ጋዜጠኛ አንተ የደረስክባቸው መሰል ቦታዎች የት አካባቢ ይገኛሉ? በእነዚህ ቦታዎች ግፍ የሚፈጸመውስ በእነማን ላይ ነበር?**

**አቶ አርአያ፡-** በጣም ብዙ ናቸው። ዝዋይ ለምሳሌ ካምፕ አለ፤ የወታደር ካምፕ ነው የሚባለው፤ ግን ወደ ሦስት፣ አራት ጉድጓዶች አሉ። እዚያ ውስጥ የራሳቸው ታጋዮች አብዛኞቹ ደግሞ የኦሮሞ ተወላጆች የሆኑ ኦነግ ተብለው ገብተው ታስረዋል። ለመጸዳዳት የሚወጡት ጠዋት ብቻ ነው። ቀኑን ሙሉ አይወጡም። ስለዚህ ይንጋ ይምሽ አያውቁም። ወደ ሰላሳ የሚደርሱ ወጣቶች ናቸው። ምርጫ 97ን ተከትሎ ቅንጅት ናችሁ ተብለው ከአየር ኃይል ተወስደው እዚያ የታሰሩ ሁለት ልጆች አውቃለሁ፤ አንዱ አሁን ካናዳ ነው። እዚያ ገብተው ጠዋት ሲነሱ ‘እንደምን አደራችሁ’ ሲሏቸው ‘እኛ እንደዚህ ዓይነት ነገር ሰምተን አናውቅም፤ ይምሽ ይንጋ ሳናውቅ እንደምን አደራችሁ አትበሉን’ ብለው በድንጋይ ሊፈነክቷቸው ነበር። ሰዎቹ ገርጥተው ነጭ ሆነዋል። ሌላው እዚህ ማዕከላዊም ግፍ ይፈጸም ነበር።

ካዛንችስ የነበረው ማሰቃያ ቦታው ደግሞ ነዳጅ ማደያ የነበረ የደህንነት ግቢ ነው። በካዛንችስ ሱፐር ማርኬት በኩል ነበር፤ አሁን ሕንፃዎች ተሰርተውበታል። በእሱ በኩል ስትወርድ በስተቀኝ በኩል የሚገኝ ነው። የሚገርምህ ይህን ማሰቃያ እዚያው እየሰሩ ያሉ ደህንነቶችም አያውቁትም። ማደያ የነበረውን አፍርሰው፣ በቆርቆሮ ከልለውት ነው፤ በዚያ በብሎኬት የተሰራ ጉድጓድ ነገር አለ። እዚያ ውስጥ ያስገባሉ፤ ብዙዎቹ የኦሮሞ ተወላጆች ናቸው፤ አንድ ጊዜ በ1995 ወይም 96 ዓ.ም ይመስለኛል ሙቀት ስለነበር እነ ወልደሥላሴ ደህንነቶቹን ግቢው ውስጥ ያለ ትልቅ ዛፍ ስር ሰበሰቧቸው። ደህንነቶቹ ያ፤ የታጠረ ቦታ ምን እንደሆነ አያውቁም። አንድ አሞራ ዝቅ ይልና ስጋ መስሎት ያነሳው ነገር በደም የተለወሰ ፋሻ ሲሆንበት የተሰበሰቡት ደህንነቶች ላይ ጣለው፣ በዚህ ጊዜ ደህንነቶቹ ደነገጡ።

ሌላው ደህንነት ቢሮ ውስጥም የእነ ጌታቸው አሰፋ ማሰቃያ ነበረ። እነ ረታ፣ ኢሳያስ እና ተክላይ ፀሐዬ የሚባሉሰው የሚደበድቡት ካረው ገብተው ነው። አሁን ተክላይ ፀሐዬ ዜሪካን ነው። የሚያደርጉትን ልንገርህ፤ ሽሮ ሜዳ ማታ፣ ማታ የወረዳ 11 ፖሊስ ለጥበቃ ወደዚያ እንዳያልፍ ተደርጎ ወስደው ድምጽ በሌለውና ባለው መሣሪያ ይገድላሉ። ብዙ ጊዜ በዚያ ጥፍርና ጸጉር ደም ይገኛል። የወረዳው ፖሊስ አዛዦች ምንም ማድረግ አይችሉም። በጣም ብዙ ሰው ተገድሏል።

ብዙ የማሰቃያ እስር ቤቶች ነበሩ። ማዕከላዊም አንደኛው ነው። በጣም የሚዘገንኑ ድርጊቶች ይፈጸሙባቸው ነበር። የአእምሮ በሽተኛ የሆኑ ሴቶች እንኳን በአስር ወንዶች ይደፈሩ ነበር። አንድ በሕይወት የሚኖር ጀነራልን ጨምሮ የህወሓት መኮንኖች የነበሩ ወንዶች እንዲደፈሩ ተደርጓል። ትግራይ ውስጥ ያለው በጣም ብዙ እስር ቤት ነው። ሰዎቹ አሁን ወጥተው ይሆናል። ባዶ ስድስት የሚባለው ወደ መሬት የሚቆፈር ነው። አሁን እነ ስብሃት የተያዙበት ቦታ ባዶ ስድስት ነው። እነሱ እዚያ ቦታ ላይ ብዙ ሰው ገድለዋል። የኢሃፓ፣ የኢዴዩ ፊውዳል ምናምን እያሉ በጣም ብዙ ሰው ያሰቃዩበት ነበር። እነዚህ ቦታዎች የራሳቸውን ታጋዮች የገደሉባቸውም ነበሩ። የምትቀበርበትን ጉድጓድ ‘አልቆፍርም’ ስትል ሌሎች ቆፍረውልህ አንተ እጅና እግርህ ታስሮ ከእነ ሕይወትህ የምትቀበርባቸው ቦታዎች ነበሩ። እነስብሃት እዚያ ቦታ ላይ ከእነ ሕይወታቸው የቀበሯቸው ብዙ ናቸው፤ እንግዴህ ስብሃትን የጠራው ደም ነው ማለት ነው።

**ዘመን፡- ህወሓት የራሱን ሰዎች ደብዛ የሚያጠፋው እና እንዴወገዱ የሚያደርገው በምን ዓይነት መንገድ ነበር?**

**አቶ አርአያ፡-** በተለያየ መንገድ ነው፤ ለምሳሌ ትግሉ ሃዋዜን የገደሉት ከእስር ቤት አመለጠ ብለው ነው። ኢጋዚን የመቱት ሆነ ብለው ከኋላ ነው፤ ግን ‘ከኢዴዩ ጋር ሲዋጋ ምናምን’ ይሉሃል። ስሁልንም የገደሉት እንዴሁ ሆነ ብለው ነው። ቤተሰቡን ሳይቀር ማጥፋት ስለፈለጉ ወንድሙን ለስለላ ብለው ልከውት ወደ ደርግ እየተመላለሰ መረጃ ይሰጣቸው

ነበር። ከዚያ እነ መለስ ለደርግ ሊሰልላችሁ መጣ ብለው መረጃ እንዲደርሳቸው አደረጉ፤ ከዚያ ይሄ ሰውዬ ታስሮ ተሰቃይቶ ተገደለ ማለት ነው። እንደዚህ ዓይነት ነገሮች ነበር የሚፈጸሙት። ሁለተኛ በመርዝ ይድሉሃል፤ ምን ዓይነት መርዝ እንደሆነና ከየት እንደሚያመጡት አላውቅም። ለምሳሌ ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል የሚባል አለ አይደል? ዋልታ ማለት የክንፈ ወንድም ነው፤ ዮሐንስ ይባላል። ዮሐንስንም የገደሉት ሆነ ብለው ነው፤ ድርጅቱ እንደዚህ ነው። እነ ኢያሱ በርሄ ብዙ ሰው ሲያጠፉ ከርመው ራሱ ኢያሱ በርሄም መጨረሻ ላይ በመርዝ ነው የተገደለው።

ስዬ አብርሃም በወቅቱ ሆነ ተብሎ ነው ከጨዋታ ውጪ እንዲሆን የተደረገው። ግን ያው ስዬ አብርሃ የአቋም ሰው አይደለም። እንደምታውቀው በመከላከያ ሰራዊታችን ላይ ጦርነት እንዲከፈት ካደረጉትና ስብሃት ጣት ከቀሰረባቸው አንዱ እሱ ነው። ዛሬም እንግዴህ ቦስተን ሸሽቶ ሄዶ የራሱን ሦስት ልጆች እዚያ በተቀማጠለ ሕይወት በሰረቀው ገንዘብ እያኖረ፣ ውድ ትምህርት ቤት እያስተማረ የድሃውን የትግራይን ልጅ እንዴህ እንዲያልቅ ያደረገ ነው፤ ነገ ጠዋት በጦር ወንጀለኝነት የሚፈለግ አንድ ወንጀለኛ ነው። የትም አይደርስም እንጂ አሁንም ቅስቀሳ ላይ ነው። አሜሪካን አገር ግሪን ካርድም ምንም ስትሞላ የምትፈርመው ወንጀል አልፈጸምኩም፤ ሰው አላስገደልኩምና ትዕዛዝ አልሰጠሁም ብለህ ነው። የዛሬ ሁለት ዓመት የቀይ ሽብር ወንጀለኛን ይዘው ለፍርድ አቅርበዋል። መንግሥት የቀይ ሽብር ወንጀለኞችን ታሪክ እየወሰደ እዚያ በአቃቢ ሕግ በኩል ለፍርድ ያቀርባቸው ነበር። አሁንም ልክ እንደዛ እነስዬ አብርሃም በሕግ መጠየቅ አለባቸው። ትግራይ

**ዘመን፡- የህወሓት ከፍተኛ አመራሮች ቤተ ሰቦች የዝርፊያ ሰንሰለትና አኗኗር ከትግራይ ሕዝብ ኑሮ ጋር ሲነጻጸር ምን መልክ አለው ?**

**አቶ አርአያ፡-** እየሁልህ ጥቂት የህወሓት አመራሮች አልፎላቸዋል። አንደኛው እንግዴህ ጥገት ላም የሚባለው ትእምት-ትግራይ እግሪ ምትካል/ ነው። የስብሃት ዘርማንዘር ከነቤተሰቡ ጠቅላላ ትእምት ሀብት ሆኖለታል። ከሱር ኮንስትራክሽን ብቻ በፓኪስታን ዜጎች በኩል ወደ ሲቲ ባንክ በዓመት 100 ሚሊዮን ዶላር ከአገር ያስወጣ ነበር። እነዚያ ፓኪስታኖች የመጡት ኮንሰልታንት ተብለው ነው። ምንም ሥራ የላቸውም ግን ለእነሱ ይከፈላል በሚል በዶላር 100 ሚሊዮን ይወጣ ነበር። ቀጥሎ ትእምትን የያዘችው አዜብ መስፍን ነች። አንድ ነገር ልንገርህ! ልጇ ሥራ ሰርታ አታውቅም፤ ነገር ግን የአምስትና ስምንት ሚሊዮን ብር መኪና ትነዳለች፤ በጣም ትልቅ ትምህርት ቤት ትማራለች። ከየት ነው ያመጣችው? የትእምት ገንዘብ ነው፤ የትግራይ ሕዝብ። ኢፈርት አሁን 30 ዓመት ሆነው! እስካሁን አንድም ኦዴት አያውቀውም። እነሱ አማካሪ ብለው የሚጠሯቸው አንዳንድ ድርጅቶች አሉ። ይሄንን በዚህ፣ በዚህ ጥቅም ብትሰራ ብለው ምክር ይሰጡሃል እንጂ ኦዴት አያደርጉም። አዜብ ስትጠየቅ የቻይና እና የኮሪያ ኦዴተሮችን አስመጥተን ኦዴት አስደርገናል፤ እጇ ላይ ወረቀት አለ ብላለች። የዚህ አገር ኦዴተር ጠፍቶ

ብርሃነ ጋኖ ማለት በዘፈን 98 በመቶ የሚሆነውን ታጋይ በርሃ የወሰደ ነው። ሱዳን ላይ ተቸግሮ፣ ደሃ ሆኖ፣ በመኪና አደጋ ነው የሞተው። እሱን ጨምሮ አምስት ልጆታቸውን ያጡት የብርሃነ ጋኖ እናት መቀሌ አደባባይ ቁጬ ብለው ይለምናሉ። አሁንም በሕይወት አሉ፤

ነው ከዚያ የሚያመጡት? ኦዴት አያውቀውም። እዚያ ውስጥ ያሉ ሁሉም ተጠቅመውበት የቪላ ቤት ባለቤት ሆነዋል። ነገር ግን ብርሃነ ጋኖ ማለት በዘፈን 98 በመቶ የሚሆነውን ታጋይ በርሃ የወሰደ ነው። ሱዳን ላይ ተቸግሮ፣ ደሃ ሆኖ፣ በመኪና አደጋ ነው የሞተው። እሱን ጨምሮ አምስት ልጆቻቸውን ያጡት የብርሃነ ጋኖ እናት መቀሌ አደባባይ ቁጭ ብለው ይለምናሉ። አሁንም በሕይወት አሉ፤ ባለፈው ዓመት እንዴያውም በፌስ ቡክ ታሪካቸውን አንስቼ ከአሜሪካና ከተለያየ አካባቢ ሰዎች ረድተዋቸዋል። የብርሃነ እናት ዓይነት ታሪክ ያላቸው በጣም ብዙ ናቸው። የትግራይን ሕዝብ የያዙት በሴፍቲኔት ነው። ከበላና ከጠጣ ሌላ ጥያቄ ሊያመጣ ነው፤ ስለዚህ አፍነው ነው የያዙት።

**ዘመን፡- በትግራይ የተካሄደውን ሕግ የማስከበር ዘመቻ የእስካሁን ሂደት እንዴት አገኘኸው?**

**አቶ አርአያ፡-** መጀመሪያ እነዚህ ሰዎች በጥጋብ፣ በስካር፣ በእብሪት ተነሳስተው ነው ይሄንን ወንጀል በመከላከያ ሰራዊታችን ላይ የፈጸሙት። እነሱ እንግዴህ በጎሬላ ውጊያ ዘመን ነው የሚያስቡት ያ፤ ደግሞ አያስኬድም አሁን ዓለም ሰልጥኗል። መንግሥትም በተደጋጋሚ በጣም በትዕግስት አልፏቸዋል። በትጥቅ ጊዜ እንደነበረው ሕዝቡም ያግዘናል ብለው በሽሬና በተለያዩ ቦታዎች መሣሪያ ሲያድሉ ነበር። እነሱ መሣሪያ የሚዋጋ ነው የሚመስላቸው፤ ሰዉ ግን ጀርባውን ነው የሰጠው። እነሱ በዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥ የተወገዱት ያለምክንያት አይደለም፤ ትግራይ ውስጥ 40 ሺ ሰው ገድለዋል፤ ይሄ አረጋዊ በርሔም ያመነው ነው። ፊውዳል እያሉ የጨፈጨፏቸው 40 ሺ የትግራይ ተወላጆችን ማለቴ ነው። ስለዚህ የእነዚህ ሰዎች ደም፣ የተሰዉት እምባ እና ጎዳና የሚለምኑት ተበዳዮች ግፍ ተደራረበና ሰው ጀርባውን ሰጣቸው። ስለዚህ መከላከያ መቀሌ የገባው ሰተት ብሎ ነው። ከዚህ ቀደም በሚዴያዎች ላይ እንደ ሳዳምሁሴንና ጋዳፊ ተጎትተው ከዋሻ ውስጥ ይወጣሉ ብዬ ነበር፤ ያው እንግዴህ እነ ስብሃት እንደዛ ወጡ። እና ሕግ የማስከበሩ ዘመቻ በአጭር ጊዜ መጠናቀቁ በጣም ጥሩ ነው።

**ዘመን፡- ሕግ የማስከበር ዘመቻው በትግራይ ሕዝብ ላይ ያነጣጠረ ነው የሚሉ ወገኖች አሉ። ያሉት መረጃዎች እንዴህ ዓይነት ድምዳሜ ላይ የሚያደርሱ ናቸው?**

**አቶ አርአያ፡-** እነዚህ ሰዎች ለትግራይ ሕዝብ ተቆርቁረው አይደለም፤ እኔ እንደዚያ ቢሆን ኖሮ ከማጋለጥ እውነትን ከመያዝ ወደ ኋላ አልልም። አንድ ነገር ሲነሳ ምክንያት ይኖረዋል፤ እሳት ዝም ብሎ ሊፈጠር አይችልም ወይ በክብሪት ነው ወይ በሲጋራ ነው ወይ ደግሞ በአንዳች ነገር ነው። እንዴህ የሚሉትን ሰዎች ‘ይሄንን ትንኮሳ በመከላከያ ሰራዊቱ ላይ የፈጸመው ማን ነው?’ ብትላቸው የሚመልሱት መልስ የላቸውም። እዚያ የነበረው መከላከያ ሰራዊት እኮ! አግብቶ ተዋልዶ መንገድ እየሰራ፣ ክሊኒክ እየገነባና እህል እያጨደ 21 ዓመት ከሕዝብ ጋር የኖረ ነው። ዛሬ የታሰሩት እነ አባይ ወልዱ እና የስብሃት



**እነዚህ ሰዎች እኮ! የለኮሱት እርችት አይደለም ወይም ነገሩ ሰርግ አይደለም። መከላከያ ሰራዊት ላይ እርድ ሲፈጽሙ ተከታዩ ነገር ምን እንደሚሆን ግልጽ ነው። ስለዚህ ጥፋቶች አይደርሱም ማለት አይደለም፤ ይደርሳሉ። ለዚህ ሁሉ ግን መንስኤዎቹ እነ ስብሃት ናቸው፤**

እህት ቅዱሳን ነጋ ይሄን ይመሰክሩ ነበር። ይሄን የሚያወሩ ሰዎች ሀቁን ለመደፍጠጥ እየሞከሩ ነው። እውነታው በመከላከያ ሰራዊታችን ላይ የተወሰደው እርምጃ ነው።

**ዘመን፡- ህወሓት የተከተለው ይዞ የመሞት ፖለቲካ ያስከተለው ሰብአዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ እንዲሁም የመሰረተ ልማት ውድመት በምን ደረጃ የሚገለጽ ነው?**

**አቶ አርአያ፡-** ልክ የመከላከያ ሰራዊት ሕግ ለማስከበር አጸፋዊ እርምጃ ጀምሮ በቀላሉ ከተሞችን መቆጣጠር ሲጀምር መጀመሪያ አሮጌውን ብር ለመቀየር በአንቶኖቭ የገባውን ገንዘብ ወሰዱ። ባንኮችም በጠቅላላ እንዲዘረፉ ተደረገ፤ ሲስተማቸውንም አበላሹት። ያ፤ ገንዘብ ተከማችቶ ‘ማን ነው የማይከዳን?’ ሲባል የስብሃት እህት ተመርጣ ቅዱሳን ነጋ ቤት ተቀመጠ። ከዚያ በኋላ አዴግራት ፋብሪካ የነበረውን መድኃኒት እንዳለ ወስደው ፋብሪካውን አወደሙት። ከተከዜ የነበረውን መብራት ጠቅላላ አቋረጡት። ኢንተርኔት እንዳይሰራ አደረጉ። በኋላም መቀሌ የሚገኘውን ድምጸ ወያኔ ቴሌቪዥን ጣቢያ ሙሉ ለሙሉ አወደሙት። ቀጥሎም መረጃ የሚያቀብሉ ተቃዋሚዎች እና ብልጽግና ብለው የእነ አብርሃ ደስታን አሁን የመቀሌ ከንቲባ የሆነውን የእነ አትክልትን ስም ዝርዝር አውጥተው መግደል ሊጀምሩ ነበረ ፤ የገደሏቸውም አሉ። ከዚያ በኋላ ነው እንግዴህ የሚጭኑትን ጭነው በተለያየ አቅጣጫ ያመለጡት። ሞንጀሪኖ እና ደብረጽዮን በሬዴዮ ያደረጉትን የተጠለፈ ንግግር ሰምቼ ነበር። እሷ ‘በቃ ከእንግዴህ አብይ እግር ስር ወድቀንም ቢሆንም እርቅና ሰላም እንፍጠር’ ትላለች፣ እሱ ደግሞ ‘እርቅና ሰላም የምንፈጥርበት ጊዜ አሁን ዘግይቷል፤ ስለዚህ በየአቅጣጫው ሕይወታችንን ማዳን ነው ያለብን’ ይላል። የሄዱት በጣም ብዙ መሰረተ ልማት አውድመው ነው።

ዛሬ ግን ጣትን ወደ ሌላ ይቀስራሉ፤ እውነታው ግን ይሄ ነው፤ ያረጋገጥኩትም ነገር ነው። ‘የኤርትራ ወታደር ገባ’ ይላሉ። የአንድን አገር መከላከያ ሰራዊት ካረድክ በኋላ ማን ሊጠብቅልህ ነው ድንበሩን? ሌላም ኃይል ሱዳንም ግብጽም ሊገባ ይችላል እኮ! ምክንያቱም መጀመሪያ መከ ላከያው ላይ እርምጃ ወሰዱ። እነሱ ያደረሱት ከፍተኛ ውድመት ነው።

አሁን ትግራይ ውስጥ ረሃብ አለ። መንግሥት በከፍተኛ ሁኔታ በቶሎ ደርሷል። ሰዎች በረሃብ አልሞቱም። ይሄ ጥሩ ነገር ነው። ትግራይን መልሶ ለመገንባት በጣም ብዙ ገንዘብ ያስፈልጋል። መንግሥት ይሄን እንደሚያደርግ አልጠራጠርም። ብዙ ባለሀብቶች በዚህ ጉዳይ ላይ ለምን ዝም እንዳሉ ግን ሊገባኝ አልቻልም። ያንን ሁሉ ሚሊዮን ብር ሲረጩ የነበሩ ሰዎች የትግራይ ልማት ሲባል ዝም ማለታቸው ይገርማል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሁለት መቶ ሺህ ብር ከመደመር መጽሐፍ ሽያጭ ፤ የአንድ ወር ደመወዛቸውን እና በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ስም ሦስት የውሃ ቦቴ መኪኖችን ሰጥተዋል። ይሄ ጥሩ ነገር ነው። ሌሎቹም ቢቀጥሉበት መልካም ነው። አንዳንድ ክልሎችም እያደረጉት ያለው ድጋፍ ጥሩ ነው፤ ግን ከፍተኛ ሀብት ማሰባሰብን የሚጠይቅ ነው።


**ዘመን፡- ሕግ የማስከበር ዘመቻው ለትግራይ ምን ዓይነት መልካም ዕድል ይዞ መጥቷል ማለት ይቻላል?**

**አቶ አርአያ፡-** ትግራይ ከእንግዴህ በኋላ በአንድ ህወሓት እየተጠመዘዘ፣ መቶ በመቶ ምረጥ እየተባለ የሚገደድበትና ስንዴ የሚከለከልበት ዘመን አብቅቷል። ካንሰር የነበረው የነስብሃት የሴራ መንገድ ተበጥሶ ተጥሏል። ስለዚህ የትግራይ ሕዝብ ነፃነቱን አግኝቷል።

**ዘመን፡- መከላከያ ሚኒስቴር የህወሓት ከፍተኛ አመራሮች ያሉበትን ለጠቆመ በሚሊዮን የሚቆጠር ብር እንደሚሸልም ማሳወቁ ይታወሳል። አንተ ደግሞ አራት ከፍተኛ የህወሓት አመራሮች ያሉበትን ቦታ ጠቁመህ እንዲያዙ አድርገሃል። ቃል የተገባውን የገንዘብ ሽልማት አግኝተሃል?**

**አቶ አርአያ፡-** አላገኘሁም፤ ባገኝም ለሕዝቡ ስንዴ የምገዛበት ነው። በትክክል ገልጸኸዋል፤ አራት ባለሥልጣናት ተንቤን ውስጥ ተደብቀው ነበር። ከአንድ ሰው ጋር ሆነን የተደበቁበትን ቦታ ለመከላከያ የመረጃ ክፍል ኃላፊዎች ጠቁመን እንዲያዙ አድርገናል። ነገር ግን የገንዘብ ሽልማት የተባለው አልተሰጠንም። እኔ እንደገለጽኩልህ ቢሰጠንም የማውለው ለሕዝቡ ነው።

**ዘመን፡- ህወሓት ወታደራዊ ሽንፈት መከናነቡን ተከትሎ በውጭ አገራት የሚ ገኙ ደጋፊዎቹ የትግራይ ሕዝብ አድማ እንዲመታና ራሱን ከኢትዮጵያዊ እህትና ወንድሞቹ እንዲነጥል እያቀረቡ ያሉትን ጥሪ እንዴት ታየዋለህ?**



**አቶ አርአያ፡-** እነሱ እንግዴህ በጣም ከፍተኛ የሀብት ትስስር የነበራቸውና ብዙ ጥቅም የቀረባቸው ናቸው። በደንብ አውቃቸዋለሁ። ዝም ብሎ ስም ማጥፋትና እንደ እነሱ ፍረጃ አልገባሁም። ከኤምባሲ ውስጥ ያገኘሁት ደብዳቤ ነበር። አሁን የተለያየ ጥሪ የሚያስተላልፉት ሚዲያዎች በወር እስከ ሰባት ሺህ ዶላር ድረስ ይወስዱ ነበር። ምን እንደሚሰሩ ግን አይታወቅም። በአንድ ወቅት የተከሰተውን ልንገርህ፤ የባለሥልጣናት ልጆች በሰባት ሺህ ዶላር አንድ ዕቃ በካሽ ይገዛሉ፤ እዚያ እንዴህ ዓይነት ባህል ስለሌለ የገቡበት እስቶር/የዕቃ ማከማቻ/ ሰዎች 911 ደውለው ነበር። እነሱ እንዴህ ናቸው። የችግሩ ሰለባ ግን የሆነው የትግራይ ሕዝብ ነው። የእነ ስብሃት ዕድሜ እንዴቀጥል ስንት ትውልድ መሞት አለበት? እዚህ ያሉት ሚዲያዎች ግን መጫወት የሚገባቸውን ሚና እየተጫወቱ አይደለም። ትግራይ ቲቪም እያስተላለፈ ያለው አንጻራዊ ነገር ነው። በተደጋጋሚ በየሚዲያዎቹ ብናገርም እርማት ሊደረግበት አልቻለም። እየሠሩ ያሉት የካድሬ ሥራ ነው። በፊትም ጋዜጠኞች ሳይሆኑ ካድሬ ነበሩ። የተሓድሶ ሥልጠና ተሰጥቷቸው የገቡ ቢሆኑም እየሠሩ አይደለም። የችግሩ ሰለባ ሕዝብ እዚህ ስላለ እነዚያ ውጭ ያሉትን ከምንም አልቆጥራቸውም።

**ዘመን፡- በትግራይ የሆነው ነገር ነው እየተነገረ ያለው? አንዳንድ ወገኖች «የተነገረው ጥቂቱ ነው፤ የከፋው ነገር ገና አልተገለጸም» ሲሉ ይደመጣሉ ፤ ሌሎች ደግሞ «ስፖለቲካ ፍጆታ ሲባል መረጃዎች ተጋነው እየቀረቡ ነው» ሲሉ ይከሳሉ። አንተ ባለህ መረጃ እውነታው የቱ ነው ?**

**አቶ አርአያ፡-** በቅርቡ ቢቢሲ በትግርኛ ያወጣው ዘገባ ነበረ። ቢቢሲ ማለት ደንበኛ ድምጸ ወያኔ ማለት ነው። ኅዳር ሦስት ቀን ‹አብይ አዴ ተንቤን ከአያቷ ጋር የምትኖር አንድ ወጣት ሴት አንድ የመከላከያ ሰራዊት አባል ሄዶ አያቷን ይችን ልጃገረድ አብራው እንድትተኛ ሲጠይቀው፣ እምቢ ብሎት ሲታገሉ ወደ ውጪ አውጥቶ ገደለው› ብሎ የተቆረጠ እጅም በምስል አስደግፎ ዘግቧል። የዚህ ሁሉ ድራማ ማብቂያውና ምላሹ ምን መሰለህ!? ኅዳር ሦስት ቀን መከላከያ አብይ አዴ አልገባም። ጦርነቱ የተለኮሰው ጥቅምት 24 ነው። ኅዳር ሦስት ቀን አልገባም። እነ ቢቢሲ እያቀረቡ ያሉት እንዴህ ጽንፍ የያዘ፣ ሕዝብን የሚያነሳሳ፣ በጣም የተንሸዋረረ ዘገባ ነው። ሚዲያው ላይ አልተሰራም የምልህ ይሄንን ነው።

ሁለተኛ ደግሞ ጦርነት ሲፈጠር ብዙ ነገሮች መከተላቸው ግድ ነው። ሰዎች ይሞታሉ፤ ይፈናቀላሉ፤ እነዚህ ሰዎች እኮ! የለኮሱት እርችት አይደለም ወይም ነገሩ ሰርግ አይደለም። መከላከያ ሰራዊት ላይ እርድ ሲፈጽሙ ተከታዩ ነገር ምን እንደሚሆን ግልጽ ነው። ስለዚህ ጥፋቶች አይደርሱም ማለት አይደለም፤ ይደርሳሉ። ለዚህ ሁሉ ግን መንስኤዎቹ እነ ስብሃት ናቸው።

**ዘመን፡- የዓለም የጤና ድርጅትን እየመሩ ያሉት ዶክተር ቴድሮስ አድሃኖም እያደረጉ ስላሉት እንቅስቃሴ፣ በተለይም በወቅታዊው የኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ እያንጸባረቁ ስላለው አቋም ምን ትላለህ?**

**አቶ አርአያ፡-**እርቀ ሰላም ይውረድ ማለቱ እንዳለ ሆኖ፤ ግን እነዛን ሰዎች/የህወሓትም አመራሮችን/ ያውቃቸዋል ለምን ‹ተዉ! ይሄ ነገር አያዋጣም።› አይላቸውም ነበር። ልጆቹ ራሳው በፌስቡክ እየጻፉ ያሉት ነገር መታዘብ ይቻላል። ‹ተነስ! ታጠቅ!› እያሉ በመንግሥት ላይ እየቀሰቀሱ ነው። ፈረንሳይ ውስጥ በተንደላቀቀ ኑሮ እየኖሩ በፌስቡካቸው እየጻፉ ያሉት ነገር ግን የትግራይ ወጣት እንዴነሳሳ ነው። ልጆቹንም ‹ተዉ! ማን እንዴሞት ነው ይሄን ቅስቀሳ የምታደርጉት?› አይልም። በየቀኑ እየተፉ ያሉት ከባድ መርዝ ነው። ይሄ መንገድ እንደማያዋጣ መንገር ነበረበት። ይሄ ነገር ከተከሰተ በኋላ ግን መጮኹ ምንም ተቀባይነት የለውም።

**ዘመን፡- በቅርቡ በውጭ አገር በሚገኘው «ትግራይ ሚዲያ ሀውስ» በተባለ የቴሌቪዥን ጣቢያ በኩል የአቶ ጌታቸው ረዳ ነው በተባለ ድምጽ «ጦርነቱ አላለቀም። በየቀኑ እየተዋጋን ነው፤ መቶ ሺ ሰራዊት ደምስሰናል» የሚል መልዕክት ተላልፏል። መረጃውን እንዴት አገኘኸው?**

**አቶ አርአያ፡-** ውሸታቸውና ፕሮፓጋዳንቸው የተለመደ ነው። በዚህ የተካኑ ናቸው። ስለጌታቸው እህቱም ተናግራለች፤ ‹ጌታቸው ጥይት ተኩሶም አያውቅም› ብላ በደንብ አድርጋ ነግራዋለች። ‹አሁን እያወራን ከፊት ለፊቴ መአት ወጣት ያልቃል› ይላል፣ የሚሰማው ግን የንፋስ ድምጽ ነው። አንድም የጥይት ድምጽ አይሰማም። ሁለተኛ መቶ ሺህ ከገደለ ታዴያ እነሱ ዋሻ ለዋሻ ምን ያደርጋሉ? እንደ በፊታቸው አፍነው እረግጠው እየገዙ ሥልጣን ላይ መሆን ነበረባቸው። ከተሞቻችን ላይ ጉዳት እንዳይደርስ አጸፋዊ መልስ የምንሰጠው በጥንቃቄ ነው ይላሉ። ያደረጉት ግን መብራት እንዴቋረጥ አድርገው ትግራይ በጭለማ እንድትዋጥ ነው። ሕዝቡ ደግሞ አንቅሮ እንደተፋቸው ሁሉ አሳልፎ ሊሰጣቸው ይገባል። እነሱ የፈለጉትን ቢሉ አይድነቅህ።

**ዘመን፡- መጽሐፍ ለማሳተም ዝግጅትህን አጠናቀሃል። መቼ ለንባብ ይበቃል?**

**አቶ አርአያ፡-** በዚህ አንድ ወር ውስጥ መጽሐፌን አወጣለሁ። ከዚያ በኋላም የሚቀጠል መጽሐፍ ነው። ሁለት ሦስት ተከታታይ መጽሐፍቶችን ለማውጣት ዝግጅት ላይ እገኛለሁ።

**ዘመን፡- ስነበረን ቆይታ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።**

**አቶ አርአያ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# በጁንታው መቃብር ላይ የሚገነባው ዴሞክራሲ

ሀብታሙ ስጦታው

## የትናንቱ ገመናችን

በአገራችን ኢትዮጵያ በርካታ መንግስታት ተፈራርቀዋል። ይሁን እንጂ በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ረገድ ያልተሳካላት እንደሆነች አለም የሚያውቀው ሀቅ ነው። በእነዚህ መንግስታት በኩል የነበረው ልምድ እና ቅብብሎሽ የሚያመለክተው መገዳደል፣ ደም መፋሰስ እና አንዱ የመንግስት ስርዓት በሌላው ላይ ቂም እና ቁርሾ በመያዝ ለቀጣይ ትውልድ የሚተርፍ አጥፊና አገር አውዳሚ እርሾ ማቆየት ነው። በመሆኑም አዴስ የሚመሰረት መንግስትም ቢሆን በዚህ ባህል ጉዞውን «ሀ» ይላል። ይህ አካሄድ ደግሞ መቆሚያ ሊበጅለት ካልቻለ ቀጣዩ ትውልድም ቂምና ቁርሾ እየወረሰ በተለመደው አዙሪት ውስጥ እንዴዳክር ያስገድደዋል።

አገሪቱ ረጅም ታሪክ ያላት ናት እየተባለ ሲነገር የመቆየቱን ያህል ዴሞክራሲያዊ ሆኖ ለትውልድ የሚተርፍ የሰለጠነ የፖለቲካ ባህል በመገንባት ታሪኳ እጅጉን አልሆነላትም። ሁኔታው ከአለመታደል ባለፈ  አሳዛኝ ያደርገዋል። አሁን ያለው ትውልድ ማንኛውንም ዋጋ ከፍሎ አዙሪቱን መቀየር አለበት የሚለው መሰረታዊ ሀሳብ ሁሉንም ያስማማ ጉዳይ ሆኗል። የዛሬው ትውልድ «ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ያስፈልጋታል፤ ለመጪው ትውልድ የሚተርፍ የሰለጠነ ፖለቲካ ስርዓት ይገባታል» ብሎ በቁርጠኝነት የሚያደርገው ወቅታዊ ተጋድሎው ለስልጣን ሽሚያ ሳይሆን ለሰለጠነ የፖለቲካ ባህል እና ለዘላቂ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ሊውል ይገባል፤ ያስፈልጋልም።

የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታና የሰለጠነ የፖለቲካ ባህልን በሚመለከት ያለፉት ዘመናት ታሪካችን የትውልድን ህይወት ከመንጠቅ በተጨማሪ የተደረገው ሽግግር ዴሞክራሲያዊነት የናፈቀው ከፊወዳል ወደ ከፋ አምባገነናዊ ስርዓት የዘለቀ ነበር። 1983ዓ.ም መንበረ ስልጣኑን የተቆጣጠረው ህወሓት መራሹ መንግስት የአገሪቱን ዴሞክራሲ በሕገመንግስት ቋጥሮ ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ ህዝቡ ዴሞክራሲ ቅንጦት እስኪመስለው ድረስ በግፍ መግደል እና የሴራ ጨዋታ መለያው ሆኖ ብዙ ዋጋ አስከፈለ።

ያለፉት 27 አመታት ብዙ መልኮች ቢኖሩትም ድምሩ ግን ዜሮ ነው። ይህ የዜሮ ድምር የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ዴሞክራሲያዊ እንደነበር ብዙ ቢነገርለትም መጨረሻው ሀገር ማፍረስ ሆኖ አገሪቱን ለሌላ የቤት ስራ ዳርጓት አለፈ። በእነዚህ ዓመታት የህወሓት/የጁንታው/ አመራሮች ስለዴሞክራሲ በመገናኛ ብዙሀን «በመልካም ግንባታ ላይ ነን» ሲሉ ነግረውናል፤ በሕገ መንግስቱም አስፍረዋል፤ በመረጧቸው ‹ምሁራን› የተለያዩ ጥናት መሰል ወረቀቶችንም ከትበዋል። የተሰራው ውሸት ጠገብ ትርክት ዴሞክራሲን ከመገንባት ይልቅ ብሄር ብሔረሰቦችን ሆድና ጀርባ ለማድረግ አቅሙ የበረታ ነው። ይህም በጣም በሚያሳዝን መልኩ ለአገር ቀጣይነት ፈተና ሆኖ ቅርቃር ውስጥ ከቷታል። ይህ እውነት ከህዝቡ የተሰወረ አይደለም።

ህወሓት /ጁንታው/ መሩ መንግስት ምን ያህል ኢ-ዴሞክራሲያዊ ነበር? የሚለው ጥያቄ መልክና ዓይነቱ ሲበዛ የኢትዮጵያ ህዝብ ብዙ ይናገርለታል። ስርዓቱ በህይወት እያለ ዴሞክራሲያዊ ነው እየተባለ ብዙ የተወራለት ቢሆንም እውነተኛ መልኩ ግን አምባገነናዊ ሆኖ በመዝለቁ ህዝቡ አምርሮ ታግሎታል፤ ድልም ነስቷል። በተለይ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶቹ ጫፍ የደረሱ በመሆናቸው አሁን ለተገኘው የለውጥ አየር ህዝቡ ያደረገው ተጋድሎ ትልቅ ዋጋ ከፍሎበታል።

ዛሬ ትግሉን ዳር በማድረስ የጁንታው ግብዓተ መሬት በተፈፀመ ማግስት ላይ በመሆናችን በቀጣይ የሚገነባው ዴሞክራሲ ምን መልክ ሊኖረው ይገባል? የሚለው አሁን ላለው ትውልድ የለመደውን አዙሪት



ፕሮፌሰር ውሂብእዜር ፈረደ

ለመቀልበስ መልካም እድል ፈጥሯል። አገሪቱን ከመንታ መንገድ ላይ ያወጣው የህዝብ ትግል አዲስ ለውጥ ጎዳና ላይ አድርሷታል። በመሆኑም አሁን ያለው ትውልድ ከመጠፋፋት ሴራ ወጥቶ፤ ከቂም በቀል ርቆ ዜጎች በሀሳብ የበላይነት ብቻ መንግስት የሚገነቡበት እንዴሆን በጁንታው መቃብር ላይ እውነተኛ ዴሞክራሲን የመገንባቱን የቤት ስራ ለማረጋገጥ ዜጎችን ማነጋገሩ ትክክል እንደሆነም ምሁራን ይመክራሉ።

## የተዋጣለት ዴሞክራሲ እንዴት ያለ ነው?

ዓለም በአንድ አገር ውስጥ ያለውን የዴሞክራሲ ስርዓት ደረጃ ለመለካት ያስቀመጠው የዴሞክራሲ ስርዓት /Index/ መለኪያ አለ። ይህ መለኪያ አንድ አገር የተዋጣለት ዴሞክራሲን ገንብታለች አልገነባችም? የሚለውን በሚገባ በመለካት ይታወቃል። በመሆኑም መለኪያውን በሚመለከት በተለያየ ወቅት የተለያዩ የዴሞክራሲ ስርዓት ነጥቦች ተቀምጠዋል፤ ጥቅም ላይም ውለዋል። ሆኖም ግን ዛሬ ያሉትን የተለያዩ ነጥቦችን በሶስት ሰፋፊ ክፍሎች እንዴጠቃለሉ መደረጉን የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ።

በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ ትምህርት ክፍል ተባባሪ ፕሮፌሰር ውሂብእዜር ፈረደ የዴሞክራሲ መለኪያዎች በሶስት ይከፈላሉ የሚለውን ሀሳብ በመደገፍ ይናገራሉ። ዶክተሩ እንደሚያስረዱት ቀዳሚው ነጥብ በአገሪቱ ብዝሀነት/diversity/ እንዴት ተስተናግዷል/ ይስተናገዳል? የሚለው ነው። ሁለተኛው የሲቪል ዜጎች ነፃነት /civil liberty/ ያለበት ሁኔታ ምን መልክ ይዟል? ሶስተኛው የፖለቲካ ባህል /political culture/ መሆናቸውን ያስረዳሉ። እነዚህ ክፍሎች የየራሳቸው ሰፋፊ ዝርዝር ነጥቦች እንዳሏቸውም በመጠቆም።

በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ፍልስፍና ረዳት ፕሮፌሰር ሲሳይ አስምሬ በበኩላቸው እንደሚገልፁት፤ አንድ አገር የተዋጣለት ዴሞክራሲ ገንብታለች ሲባል መሰረታዊ ከሆኑ ጉዳዮች ውስጥ አገሪቱ ህዝቦቿን የስልጣን ባለቤት አድርጋለች ወይ? ብለህ ስትጠይቅ የምታገኘው መልስ ይናገራል ሲሉ ይሞግታሉ። በዚህም ህዝብ የመረጠውን ይሾማል፤ ያወርዳል የሚለውን መርህ ያስገነዝባል። ሁለተኛ ጉዳይ አገሪቱ የህግ የበላይነት የተረጋገጠባቸው ሊሆን ግድ ነው ባይ ናቸው። ሁሉም ዜጋ፤ የመንግስት ባለስልጣንም ሆነ ተቋማት በህግ ፊት እኩል የሚጠየቁባቸው መኖሩ የአገሪቱ መገለጫ ወይም መለያ ነው። በሶስተኛነት ፍትህ እና እኩልነት የተረጋገጠባቸው ሲሆኑ በተለይ ዜጎች በአገራቸው ፍትህ ማግኘት መቻላቸው ያለብሔር፣ ሃይማኖት እና አመለካከት ልዩነት ተግባራዊ መሆን አለበት።

አገሪቱ እነዚህን ጉዳዮች አሟልተው ሲገኙ የተዋጣ ዴሞክራሲን እየገነቡ ነው ብሎ በድፍረት መናገር ያስችላል። ከዚሁ በተጨማሪ ፍትሃዊና ነፃ ምርጫ በተሟላ ሁኔታ እያካሄዱ የዘለቁና የቻሉ፣ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር፣ የሃሳብ፣ የአመለካከት ወይም የሃይማኖት ብዝሀነት ስፍኖባቸው ሂደቱን በሚገባ አሟልተው የተገኙ አገራት የተሳካ ዴሞክራሲ ገንብተዋል ማለት ይቻላል ሲሉ ረዳት ፕሮፌሰሩ ሃሳባቸውን ያቀርባሉ።

ዴሞክራሲያዊ ባህል ከዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ ለዴሞክራሲ መሰረት ከሆኑ ነገሮች አንዱ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብን መመስረት ነው። «ዴሞክራሲ አለ ልንል የምንችለው ማህበረሰብ እንደ ማህበረሰብ ዴሞክራሲያዊ ሲሆን ነው፤» በማህበረሰቡ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ባህል ሳይኖር ዴሞክራሲያዊ መንግስት ሊኖር አይችልም ይላሉ። በመሆኑም ተጨባጭ በሆኑ መለኪያዎች ስናያቸው ዴሞክራሲን እየገነቡ ነው የምንላቸው አገራት እነዚህን መርሆች አሟልተው የተገኙ ናቸው ሲሉ ይከራከራሉ።

## «ሙት ዴሞክራሲያዊነት»

ከላይ ከተቀመጡት የተለያዩ መስፈርቶች አኳያ በኢትዮጵያ በተለይ ባለፉት 27 ዓመታት ዴሞክራሲያዊ መብቶች በአግባቡ ተይዘዋል? ወይስ ተረግጠዋል? ህዝቡስ የራሱን መንግስት መሰረተ ወይስ ተጭኖበት ነበር? መሰረታዊ የሚባሉ የህዝቡ ሀሳብን በነፃነት መግለፅ፣ የመደራጀት መብት ፣የህግ የበላይነት፣ የእምነት ነፃነት እና የመሳሰሉት ነገሮች በመለኪያዎቹ ልክ የአገሪቱን ዴሞክራሲ መመዘን ግድ ይላል።

ፕሮፌሰር ውሂብእዜር እንደሚገልፁት ኢት ዮጵያ በተለይ ባለፉት 27 ዓመታት ውስጥ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ተጀምሮ ነበር ወይ ብሎ ለሚጠይቅ ምላሹ ዜሮ ለመሆኑ አሁን የደረስንበት ደረጃ ብቻውን አስረጂ ነው። ስርዓቱ በሶስት መሰረታዊ ምክንያቶች ከዴሞክራሲ ጋር ተጣልቶ ኖሯል፤ ሲሉ አስረጂ በማቅረብ ይሞግታሉ።

ዶክተሩ የጁንታው ቡድን ወደ ስልጣን የመጣበት መንገድ በምርጫ ሳይሆን በጦርነት በመሆኑ ዴሞክራሲ ላለመኖሩ ቀዳሚ አስረጂ አድርገው አቅርበዋል። ህወሓት ከላይ ከተጠቀሱት ሶስት ክፍሎች በተለይ ከሲቪል ነፃነቶች ጋር በቀጥታ የሚጣረሰው ባልተሟላ ሁኔታ የሚከተለው የማርክሲስት ሌኒኒስት ፍልስፍና በአገሪቱ ዴሞክራሲ አለመጀመሩ ሁለተኛው ገፊ ምክንያት ነው ሲሉ ያብራራሉ። ይህ ፍልስፍናው ሰብዓዊ መብትን ለማክበር አይፈቅድለትም፤ ይህ ደግሞ በቀጥታ ከሲቪል ነፃነቶች ጋር አጋጭቶት ዓመታትን ተሻግሯል። የሃይማኖት ነፃነትና የመደራጀት መብት ከወረቀት ላይ ወርዶ መሬት ያልነካ ለመሆኑ ብዙ እማኝ እና አስረጂ ማቅረብ እንደሚቻል አፅንኦት ሰጥተው ተናግረዋል።

ሶስተኛው ምክንያት ይህን ፍልስፍና ይመሩ የነበሩ ቡድኖች ይዘውት የመጡት ማህበራዊ ጉድለቶች ነው ይላሉ፤ ፕሮፌሰር ውሂብእግዜር። ቡድኑ የነበረው የስነልቦና ጉድለት ራሱን የበታች አድርጎ የሚወስድ በመሆኑ «አዋጣለሁ፤ ከስልጣን እገለላለሁ፤ አሁን ያለኝን ጥቅሞች አጣለሁ፤» የሚል ነው፤ ይህ ደግሞ የዴሞክራሲ ስርዓት ባህሪም ባለመሆኑ በአገሪቱ ዴሞክራሲ ተጀምሮ ነበር ማለት አይቻልም ሲሉ ይከራከራሉ።

በኢትዮጵያ ትልቁ ጥያቄ የዴሞክራሲ ስርዓት ሲሆን ይህ ግን በተለያዩ ጉዳዮች እየተሸፈነ እና እየታፈነ መምጣቱ ችግሩን አከፍቶታል። ይህም በአገሪቱ ዴሞክራሲን የማዋለድ ጥያቄ አስቀርቶታል፤ አጨናግፎታልም። በዚህ ድምር ምክንያቶች ዜጎች ዴሞክራሲን የቅንጦት እስኪመስል ድረስ ምኞት ሆኖ ቀርቷል ሲሉ ያስገነዝባሉ።

ረዳት ፕሮፌሰር ሲሳይ በበኩላቸው የጁንታው ቡድን ከዱር ጀምሮ የመጣበትን ስርዓት ስንመለከት ይከተለው የነበረው ፍልስፍና፣ በተግባር የሚናገሩትን ደምሮ ለሚያስተውለው ዴሞክራሲያዊ ስብዕና የላቸውም ሲሉ በዶክተር ውሂብእግዜር ሃሳብ ይስማማሉ። በግለሰብ ደረጃም ቢሆን አንዳቸውም የዴሞክራሲን ‹ሀሁ› የሚያውቁ አይደሉም ባይ ናቸው። ዴሞክራሲን የማያውቅ ዴሞክራሲን ያመጣል ብሎ ማሰብ አይቻልም። መጀመሪያውኑ ፓርቲውንና ራሳቸው የሚመሩበትን ሞራል ስታይ የዴሞክራሲ መንፈስ የላቸውም። ከጅምሩ የዴሞክራሲ ፅንሰ ሀሳብ የሌላቸው በመሆኑ ዴሞክራሲን ያመጣሉ ብሎ የጠበቀ በጣም ውስን ሰው ነበር ሲሉ ያስታውሳሉ። አለመታደል ሆኖ እንጂ መሪዎች ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ቀናኢ መሆን ነበረባቸው። ቡድኑን በቁንጮነት ከመሰረቱትና ከመሩት ጀምሮ የዴሞክራሲ እሴት የሌላቸው እንደነበሩ አቋም ይዘው ይከራከራሉ።



ረዳት ፕሮፌሰር ሲሳይ አስምሬ

የጁንታው ቡድን /ስርዓቱ/ ዴሞክራሲን ያመከነው ከሕገመንግስቱ ጀምሮ ነው። ሕገመንግስቱን የሚያመለኩ ቢኖሩም እንደ ሀገር ዴሞክራሲያዊ መብቶች የታሰሩት በዚሁ ሰነድ ነው የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰር ሲሳይ፤ አንድ ሀገር ስርዓት የምትፈጥረው በሕገመንግስት ላይ ተመስርታ ነው። ፖሊሲም ሆነ ሕግ ብታወጣ መሰረቱ ሕገመንግስት ነው። በመሆኑም አገሪቱ ዴሞክራሲያዊ እንዳትሆን ተደርጎ የተቀረጸ ነው። በዚህ ሕገ መንግስት ሕዝቦች አብረው መኖርም አገር መገንባትም አልተቻለም፤ በመሆኑም የሚፈለገውን ዴሞክራሲ ማምጣት አይቻልም ብለዋል። የሀገሪቱ ትልቁ ነቀርሳ ሕገ መንግስቱ ነው። ከ20 እስከ 25 የሚደርሱ አንቀፆች አሉ ዴሞክራሲ በአገሪቱ እንዳይኖር ሆን ተብለው የተሰነቀሩ። ለዚህ ነው በርካታ ምሁራን በአገሪቱ ዴሞክራሲ ተጨናግፏል የሚሉት ይላሉ።

ተባባሪ ፕሮፌሰር ውሂብእዜር እንዳመለከቱት፤ በአገሪቱ ያለው የፖለቲካ ባህል በሚገባ መታየት አለበት ባይ ናቸው። «ዴሞክራሲ ሳይኖር ዴሞክራሲ መገንባት አይቻልም፤ በማህበረሰቡ ውስጥ የዴሞክራሲ ባህል ከሌለ ዴሞክራሲን የመገንባቱ ሂደት አስቸጋሪ ነው» ሲሉ ዶክተሩ የማህበረሰብ የፖለቲካ ባህል እሴት ለዴሞክራሲ

ስርዓት ግንባታ ወሳኝነት አመልክተዋል። በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ‹ትዕግስት› ትልቅ ቦታ ሊሰጠው የሚገባ እሴት ነው ሲሉ በአብነት ያስቀምጣሉ። አንዳንድ የዴሞክራሲ ጉዳዮች ትዕግስት የሚጠይቁ በመሆናቸው ዴሞክራሲን ለመገንባት ማህበረሰባዊ ትዕግስት ወሳኝ እሴት ነው። የሌሎች ሀሳብ ለእኛ በማይዋጥልን ወቅት የራሳችን አቋም ይኖረናል። በሌሎች ሀሳብ ባንስማማም ሀሳቡን በሀሳብ መልክ በቅንነት ተቀብሎ መቆየት ይገባል። ይህ በሀገራችን በጣም ኋላ የቀረ እሴት ነው። ይህ እሴት በማህበረሰቡ ውስጥ የነበረ ቢሆንም በጁንታው የሴራ ተግባር ሊጠፋ እንደቻለ ይናገራሉ። የአንድ ማህበረሰብ ወሳኝ የዴሞክራሲ እሴት ፍትህ እና ጤናማ የፖለቲካ ውድድር የማድረግ ባህል በመሆኑ ሊነሱ የሚገባቸው እሴቶች ናቸው።

ፍትህ በሁሉም ቦታዎች እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ይህ እሴት በእምነት ተቋማት ሳይቀር አስፈላጊ ነው። በእርግጥ ፍትህ በኢ-መደበኛ ጭምር በማህበረሰቡ ውስጥ የቆየ ቢሆንም በተሰራው ክፉ ስራ ሊመክን ችሏል። ከእነዚህ ጉዳዮች አንፃር በስርዓቱ ውስጥ የነበረው በፍትህ የአለመተማመን አባዜ ወደ ማህበረሰቡ ተጋብቶ ክፍተቱ ሰፍቶ ዛሬ ሌላ መልክ ይዟል። የነበረው ስርዓት ልዩነትን በእጅጉ የሚነዛ ስለነበር ከላይ ያነሳናቸው የዴሞክራሲ እሴቶች ከአገሪቱ ርቀው ዴሞክራሲ ለህዝቡ ከምኞት ሳያልፍ ዛሬ ላይ ደርሰናል።

«ለእኔ ከማህበረሰባዊ የዴሞክራሲ ባህል ደረጃ በዘለለ ስልጣን ላይ የነበረው ስርዓት በማህበረሰቡ ውስጥ በሴቷና በማህበረሰቡ መካከል የነበረውን ግጭት ወደ ታች /decentralized/ በማድረግ ማህበረሰቡ ውስጥ ከቶታል። በተለይ ከሶስት አመታት ወዲህ ግጭቶች ማህበረሰባዊ ሆነው አንድ ህዝብ በሌላው ህዝብ ላይ እንዲነሳ፣ እንዲጋጭ የተሰራበት ነበር። ይህ የሚያመለክተው ከዴሞክራሲ ጋር የተጣላው ሀይል፣ መንግስት/ቡድን/ በመሆኑ የነበረበትን የስነልቦና ጉድለት /የበታችነት/ ማህበረሰቡ ውስጥ ማስረፁን ነው። በዚህ ሳቢያ በአገሪቱ የሚከሰቱ ግጭቶች በአጠቃላይ መንግስትና ማህበረሰብን መለየት እስካለመቻል አድርሶታል» ሲሉ ተባባሪ ፕሮፌሰር አፅንኦት ይሰጣሉ።

ረዳት ፕሮፌሰር ሲሳይ ዴሞክራሲ አለት ላይ ተዘርቶ የሚበቅል አይደለም ሲሉ ሀሳባቸውን ይገልፃሉ። በአንድ አገር ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ለመገንባት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች አሉ። ጠንካራ የፍትህ ተቋማት፣ ጠንካራ የመገናኛ ብዙሀን፣ ጠንካራ ዴሞክራሲያዊና የተማረ ማህበረሰብ የዴሞክራሲ ስርዓትን በሚገባ ለመገንባት ስራዎች ናቸው። እነዚህ ጉዳዮች በሌሉበት ዴሞክራሲ አለ አሊያም ተጀምሯል ማለት አይቻልም። ሲሉም የዶክተር ውሂብእዜርን ሀሳብ ያጠናክራሉ። በአገሪቱ እነዚህ መሰረታዊ ጉዳዮች ተሟልተው የተገኙበት ሁኔታ ባለመኖሩ ዴሞክራሲ ያለፉት 28 ዓመታት የውሸት ነበር ሲሉ ይገልፃሉ።

ኢትዮጵያ ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች አሟልታ ያልተጓዘች አገር በመሆኗ ስለ ዴሞክራሲ ማውራት በእጅጉ አስቸገሪ ነው ሲሉ ያስገነዝባሉ። በመሆኑም ባለፉት ስርዓቶች ስለ ዴሞክራሲ የምናወራበት ሁኔታዎች አልነበሩም። አለት ላይ መዝራት እንደማይቻለው ሁሉ በሌለ የዴሞክራሲ መሰረት ዴሞክራሲ ብሎ መነጋገር አይቻልም። የህግ የበላይነት፣እኩልነት፣ ህዝብ የስልጣን ባለቤት ሆኖ በመረጠው መተዳደር/የህዝብ የመሾም እና የማውረድ ተግባራዊ መብት/ የፍትህ ስርዓት አፈር ድሜ የገቡበት እንጂ ነፍስ ዘርተው አልታዩም። በሁሉም የዴሞክራሲ መስፈርቶች ስትመዝነው የአገሪቱ ዴሞክራሲ «ሙት ዴሞክራሲ» ነበር ብሎ መሰየም ይቻላል ባይ ናቸው።

የዴሞክራሲ ተቋማትን በሚገባ ስንፈትሽ ጥንካሬያቸውም ሆነ ውድቀታቸው በቀጥታ ከማህበረሰብ ንቃተ ህሊን ጋር ይያያዛል። ጠንካራና ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ጠንካራ የዴሞክራሲ ስርዓት የመገንባት እድሉ ሰፊ ነው። ምክንያቱም ተቋማት የማህበረሰባዊ ንቃተ ህሊና መገለጫዎች ናቸው። የዜጎች የፖለቲካ ንቃተ ህሊና በማህበረሰብ እድገት ልክ የሚጓዝና የሚቀዳ ነው። ይህ ደግሞ ማህበረሰቡ ውስጥ ያለ የዴሞክራሲ ስርዓት እሴት ነው። የዜጎች ንቃተ ህሊና ባደገ ቁጥር የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታው ቀና ይሆናል። ይህ በትምህርት የሚገኝ ነው እንጂ አገር ዴሞክራሲያዊ ሆኖ አይፈጠርም። ጠንካራ ተቋማት የምንፈጥረው በትምህርት በመሆኑ የነቃ ማህበረሰብ በመፍጠር ረገድ አስፈላጊ ነው።

በመሆኑም ስለ ዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታ ሲነሳ ያማረ ህንፃ እና ጠንካራ አመራር ማስቀመጥ ብቻውን የሚያመጣው ውጤት አይኖርም። ጠንካራ የዴሞክራሲ ተቋማት በቀጥታ የሚገናኙት ከማህበረሰብ ንቃተ ህሊና ጋር ነው። ንቃተ ህሊናው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ ማህበረሰብ ጠንካራ የዴሞክራሲ ተቋማት ይገነባል። በፖለቲካል ሳይንስ ውስጥ ያለው አንድ አነጋገር አለ፤ «The people get the goverment they deserve» ይህ ማለት «ህዝብ በልኩ የሚገባውን መንግስት ያገኛል» ማለት ነው። የአሜሪካ ህዝብ ያለው የዴሞክራሲ ደረጃ ማለት ህዝቡ ያለው ንቃተ ህሊና ልክ ማለት ነው። የሚመራን መንግስት፣ ሕዝቡ ያለው ንቃተ ህሊና እና ተቋማቱ ከዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታው ጋር መሳ ለመሳ ሆነው ይገኛሉ። በመሆኑም ንቃተ ህሊናው የዳበረ ማህበረሰብ የዴሞክራሲ ተቋማትን ከመገንባት አስቀድሞ ሊኖረን የሚገባ ወሳኝ ጉዳይ ይሆናል። የፍትህም ሆነ የትምህርት ተቋማት ግንባታ እና ዘመናዊነት ከህብረተሰብ ንቃተ ህሊና ጋር በቀጥታ የተያያዙ ናቸው።

## በጁንታው መቃብር ላይ...

አሁን ያለው ትውልድ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታን በሚገባው ልክ መሰረት ለማስያዝ በእጁ ያለውን ወርቅ መጠቀም እንጂ በከንቱ ማስቀረት የለበትም። በመሆኑም ይህን ስርዓት መሰረቱን ለማቆም የሚጠበቁ መሰረታዊ ነገሮች ውስጥ የተወሰኑትን ነጥቦች የሚያነሱት ረዳት ፕሮፌሰር ሲሳይ ናቸው። ቀዳሚው የቤት ስራ ሕገመንግስቱን ማሻሻል ነው። ሕገመንግስቱ የጁንታው ቡድን ሰነድ እንጂ የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት ብሎ መውሰድ አይቻልም። ይህ ሰነድ እንዳይኖሩ የሚያደርግ፤ አብሮ አገር መገንባት የማያስችል፤ ፀረ- ዴሞክራሲያዊ በመሆኑ እያንዳንዷ አንቀፅ ተለቅሞ መቀየር ያለበት እንዲቀየር፤ መጨመር ያለበት ደግሞ እንዲጨመር እድሉ መመቻቸት አለበት። ይህ ሳይሆን ዴሞክራሲን ለመጀመር ማሰብ በራሱ አዳጋች ነው።

ሁለተኛው ጉዳይ ስርዓቱ ወድቋል ተቀብሯል። ሆኖም ግን ስርዓቱ ምንድን ነው? ብሎ በትኩረት ማየት ለሚገነባው ዴሞክራሲ ትልቅ ጥቅም አለው። ስርአቱ ግለሰብም ተቋምም ነው። እነዚህ ሰዎች /የጁንታው ቁንጮዎች/ ስለተወገዱ ብቻ ነገሩ አብሮ ይሞታል ማለት አይደለም። የስርዓቱ ተከታዮች በስፋት በመኖራቸው የፖለቲካ አስተሳሰቡ ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታው እንቅፋት በመሆኑ እንዳይመለስ ተደርጎ መዘጋት አለበት በማለት ሁለቱም ምሁራን ተመሳሳይ ምክረ ሀሳብ ያቀርባሉ።

መንግስትም ሆነ ህዝብ ይህን ስርዓት እስከመጨረሻው ተጨባጭ በሆነ ሁኔታ ማራገፍ አለበት። ይህ ስራ በሁሉም ክልሎች በአጠቃላይ ሊሰራ ይገባል ምክንያቱም የነበረው ስርዓት ፀረ- ዴሞክራሲያዊ ነው። በጁንታው መቃብር ላይ የሚገነባ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ በመሰረታዊነት ሊሰራው የሚገባ ቀዳሚ ስራ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ የሆነውን አስተሳሰብ ታሪክ ከማድረግ ነው። አስተሳሰቡን ዳግም ህይወት ሊዘራ የሚያደርጉ ተቋማት ዳግም የማይመለሱበትን ሁኔታ ማስቀረት መቻል ትልቁ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታው የቤት ስራ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

በሶስተኛነት የዴሞክራሲ ስርዓት ትልቁ አቅም እና መሰረት ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብን መገንባት መቻል ነው። ማህበረሰቡን ዴሞክራሲያዊ የማድረግ ጉዳይ በራሱ ውስጥ ካሉ መልካም እሴቶች ሊጀምር ይገባል። ባህላዊ የሆኑ ዴሞክራሲያዊ እሴቶቹን ማጎልበት። ከዚህ ባለፈ ማህበረሰቡን በመደበኛም ሆነ ኢ- መደበኛ በሆነ መንገድ ማስተማር እና ማሰልጠን ይቻላል። በተለይ ከእነዚህ መሰረታዊ የዴሞክራሲ ስርዓት ግብዓቶች ውስጥ የህዝብ ስልጣንን ማረጋገጥ፤ ህዝብ ይሾማል፤ ይሽራል የሚለውን ትክክለኛ አባባል ተግባራዊ ማድረግ ቀና የዴሞክራሲ መንገድን ይፈጥራል።

አንድ ማህበረሰብ ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን በፍትህ እምነት ኖሮት ሕግ ፊት ሁሉም እኩል እንዲዳኙ መደረግ አለበት። ይህ ደግሞ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብን ብቻ ሳይሆን ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን ለመመስረት ያስችላል። የዴሞክራሲ ተቋማት ከዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ እሴቶች ስለሚቀዳ የስርዓቱን ግንባታ ምቹ እንደሚያደርገው የበርካታ አገራት ተሞክሮም ሆነ በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች አመላክተዋል። በመሆኑም እንደ አንዳንድ አገራት ልምድ ማህበረሰብን ዴሞክራሲያዊ በማድረግ ረገድ የባህል አብዮት ሊያስፈልገን ይችላል። የዴሞክራሲ ስርዓቱን ስኬታማ በማድረግ ረገድ ደግሞ እንዳለፉት ዘመናት ጉዳዩን ሁሉ ለመንግስት እና ለፓርቲ መተው አይገባም። ዜጎች በሙሉ አቅማቸውና እውቀታቸው ተቀራራቢ አረዳድና ትግበራ ውስጥ ሊገቡ ይገባል ሲሉም ሃሳባቸውን አቅርበዋል።

ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብና ዴሞክራሲያዊ ተቋማት አንድ አገር እንደ አገር ዴሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲቀጥል የሚያስችሉ ጉዳዮች ናቸው ሲሉ ተመሳሳይ ሀሳብ የሚያቀርቡት ሁለቱ ምሁራን፤ አሜሪካን በእየ ምርጫ ዘመኗም ሆነ በአስተዳደር ጉዞዋ ዴሞክራሲያዊ ሆና እንድትቀጥል ያደረጋት ግለሰቦች አይደሉም፤ ዴሞክራሲያዊ ከሆነው ማህበረሰብ/ህዝብ የተቀዱት የዴሞክራሲ ተቋማቶቿ ናቸው ብለዋል።

እውነት ነው! አሜሪካ የማንክደው ዴሞክራሲያዊ የሆነ ማህበረሰብ አላት፤ ከዚህ ማህበረሰባዊ እሴቶች የሚቀዱ ዴሞክራሲያዊ ተቋማትም መስርታለች። የትኛውም ስርዓት እና ግለሰብ ይምጣም ይሂድ ዴሞክራሲያዊ ስርዓቱን የሚያስቀጥሉት ተቋማት እና ማህበረሰቡ አብረው ይጓዛሉ። በመሆኑም የህወሓት ጁንታ ቡድን ሄዶ የሚተካውን አዲስ ስርዓት የሚረከቡ እና በሕግ ደረጃ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ለመገንባት ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ እና ዴሞክራሲያዊ ተቋማት በዘላቂነት ሊኖሩን፣ሊገነቡ ግድ ይላል።

# የምርጫ 2013 ሰላማዊነት ተስፋና ስጋቶች

ሀብታሙ ስጦታው

ኢትዮጵያ አምስት አገራዊ ምርጫዎችን አከናውናለች። ምርጫዎቹ የዴሞክራሲ ሥርዓትን ይወልዳሉ የሚል ምኞት ቢኖርም የዜጎችን ነብስ ከመንጠቅ ባለፈ ከሽፈው ቀርተዋል። ምርጫ በአገር ደረጃ ዘላቂ ሰላም ያመጣል የሚል መግባባቶች ቢኖሩም ያለፉት አምስት አገራዊ ምርጫዎች የሰላም እጦት መንስኤ ሆነው ዛሬ ላይ ደርሰዋል። ዜጎች በተለይ ደግሞ ከሕዝቡ የተሻለ ሀሳብ አለን የሚሉት ፓርቲዎች ስድስተኛው አገራዊ ምርጫ ሰላማዊ ሆኖ እንደሚጠናቀቅ ሙሉ እምነት ቢኖራቸውም ከእነሱ የሚጠበቀውን ተወጥተዋል ወይ? ስትል ዘመን ትጠይቃለች።

ሰላምን ርዕሰ ጉዳይ አድርጋ ያነጋገረቻቸው የብልፅግና፣ የኦነግ፣ የኢዜማ እና የመድረክ ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮች በአገሪቱ ከሚሳተፉባቸው የምርጫ ጣቢያዎችን በማመላከት ምርጫ 2013 ሰላማዊ ሆኖ እንደሚጠናቀቅ ተስፋቸው ሙሉ ቢሆንም የዴሞክራሲ ስርዓት ውልደቱ የተሳካ እንዲሆን ሊያጋጥሙ ይችላሉ ያሏቸውን ሳንካዎች ከእነ ምክረ ሀሳባቸው እንዴህ ተሰናስኗል።

የብልፅግና ፓርቲ ከፍተኛ አመራር አቶ ዛዴግ አብርሃ እንደሚገልፁት ፓርቲው ገዥ ፓርቲ ከመሆኑ ጋር ተዳምሮ በርካታ ኃላፊነቶች ቢኖሩበትም በምርጫው ከመሳተፍ ባለፈ ዴሞክራሲ በአገሪቱ እውን እንዲሆን በእጁ ያለውን እድል አያባክንም። በመሆኑም በወቅታዊ የሕግ ማስከበር ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ከማይካሄድባቸው ምርጫ ጣቢያዎች ውጭ በመላ አገሪቱ ይሳተፋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ/ኢዜማ/ ሊቀመንበር አቶ የሺዋስ አሰፋ እንዳስታወቁት በመላው አገሪቱ ባሉ በ450 የምርጫ ጣቢያዎች ይሳተፋል። ይሁን እንጂ በትግራይ ክልል ከነበረው የሕግ ማስከበር ተግባር ጋር ተያያዞ በአስቸኳይ የነብስ አድን ስራው ምክንያት የስድስተኛው አገራዊ ምርጫ ከሁሉም ክልሎች እኩል አይከናወንም። በመሆኑም ኢዜማ ቢሮ ከመከፈት ያለፈ ስራ እንደማይኖረው አመልክተዋል። ኢዜማ በምርጫ ወረዳ ደረጃ መዘጋጀቱን ያስታወሱት አቶ የሽዋስ ወደ አስር የሚደርሱ ንቅናቄዎች እና ፓርቲዎች እንደ አንድ ፓርቲ ሆነው ለውድድር መዘጋጀቱን ጠቁመዋል።

የመድረክ ሊቀመንበር ፕሮፌሰር መረራ ጉዴና በበኩላቸው ፓርቲያቸው በአብዛኛው ኦሮሚያ፣ አዴስ አበባ፣ አፋር፣ ደቡብ በተለይ ሲዳማ ላይ የመወዳደር ፍላጎት አለው። ነገር ግን የሰላም እጦቱ ወቅቱን የምርጫ አላስመሰለውም ብለዋል። ‹‹በመድረክ ውስጥ አራት ፓርቲዎች አሁንም አለን፤ አፋር ፓርቲ ወጥቻለሁ እያለ ነው። አረና ትግራይ፣ ሲዳማ አርነት ንቅናቄ እና ኦፌኮ አለን። ‹ትብብር› ከሚባል ፓርቲ ጋር አብረን ልንሰራ ተፈራርመን ምርጫ ቦርድ አስገብተናል። በዚህ ውስጥ እነ ኦነግ፣የኦጋዴን ነጻ አውጪ ግንባር፣ የአገው ንቅናቄ እና ሌሎች አምስት ስድስት የሚደርሱ ፓርቲዎች ይገኛሉ።



አቶ ዛዲግ አብርሃ

**ብልፅግና ፓርቲ በምርጫው ተወዳድሮ ማሸነፍ የሚፈልገው የፓርቲ አባላትን በማሰር አሲያም ቢሮዎችን በመዝጋት አይደለም**

በአጠቃላይ አስር ከሚደርሱ ፓርቲዎች ጋር ለመስራት እየተዘጋጀን ነው፤›› ብለዋል።

‹‹ስሙ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር/ኦነግ/ ይሁን እንጂ አገራዊ ፓርቲ ነው። ሆኖም ግን በአብዛኛው ኦሮሚያ ይወዳደራል። ኦሮሚያ ባላት መቀመጫ ልክ በፌደራልም በክልልም እንወዳደራለን። ከዚህ ባለፈ በአማራ ክልል የተወሰኑ ቦታዎችን በማካለል፤ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣በሐረሪ፣ አዴስ አበባ እና በደቡብ ክልል ይወዳደራል፤›› ሲሉ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር /ኦነግ/ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ቀጀላ መርዳሳ አመልክተዋል።

## ቅድመ ግምገማ

አንድ ምርጫ ሰላማዊ ሆኖ እንዴጠናቀቅ ከሚነሱ በርካታ ምክንያቶች ውስጥ የመጀመሪያው የፓርቲ የውስጥ ዝግጅት ነው ያሉት አቶ ዛዴግ የውስጠ ፓርቲ ስነምግባር ደንብ ከማዘጋጀት ጀምሮ የፖለቲካ ፓርቲዎች የስነ ምግባር ደንብን መላው አባላት አክብረው እንዴገኙ በማስተማር ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል። ከዚህ ባለፈ ፓርቲው በምርጫው ሕግጋቶች አክብሮ በመንቀሳቀስ፤ ቢያሸነፍ ፕሮግራሙን በሚገባ ሊፈፅም፤ ቢሸነፍም ኢትዮጵያ እንዳሸነፈች በመቁጠር ውጤቱን በፀጋ ይቀበላል፤ለአሸነፈውም አካል ሥልጣኑን ያስረክባል ብለዋል።



አቶ የሺዋስ አሰፋ

በአገሪቱ ዴሞክራሲን የማዋለዱ ተስፋ ከትናንት በተሻለ እድሉ አለ። ይህ ግን ስጋቶችንም አብሮ እንደያዘ መዘንጋት የለበትም። ነገር ግን «ተስፋ ከቆረጡ ሰዎች ውስጥ አንዱ ነኝ »የሚሉት ፕሮፌሰር መረራ «ተስፋ ያስቆረጠኝ ጉዳይ ብሔራዊ መግባባት ላይ የነበረን ተስፋ መሟጠጡ ነው። የእስረኞች ጉዳይ፣ የምርጫ ቦርድ ገለልተኛ አለመሆን፣ የቢሮዎች መዘጋት ጉዳይ፣ እነዚህ በሙሉ ችግሮች ሰላም ይፈጥራሉ ተብለው በሁሉም የምርጫ ምዕራፎች ያሉ እንከኖች እየተቀረፉ አይደለም። ስለዚህ ገዥው ፓርቲ የራሱን ፍኖተ ካርታ ይዞ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ይህ ደግሞ ገዥውን ፓርቲ ሊመቸው ይችላል። መድረክን የመሰሉ በአገሪቱ ዴሞክራሲ እንዴሰፍን የሚጥሩ ፓርቲዎች የራሳቸውን አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ተብሎ ግምት አልተሰጣቸውም፤» ሲሉ ወቅሰዋል።

ኦነግ አንድን አገራዊ ምርጫ ለማከናወን ሰላምና መረጋጋት ወሳኝ ናቸው ብሎ ያምናል ሲሉ አቶ ቀጀላ ይገልፃሉ። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የሰላም መደፍረሶች በተለይ ግጭቶች መኖራቸውን የፓርቲው ግምገማ ያመለክታል። እነዚህ ግጭቶች መወገድ አለባቸው። በተለይ በፓርቲ- ፓርቲ፤በመንግስት- ፓርቲ መካከል ባሉ ችግሮች የፖለቲካ አለመረጋጋት ተወልደዋል። እነዚህ የተጠራቀሙ ችግሮች ከምርጫው በፊት እልባት ሊያገኙ ይገባል የሚል እምነት እንዳላቸው አቶ ቀጀላ አስታውቀዋል። ለመፍትሄው መንግሥት ብቻ ሳይሆን ፓርቲዎችም በትኩረት ሊሰሩ ይገባል። ፓርቲዎች በግጭት ካለመሳተፍ ጀምሮ መፍትሔዎችን በማመቻቸት ግዴታቸውን ሊወጡ ይገባል ብለዋል።

እንደ አቶ የሽዋስ ገለፃ በአገሪቱ ያለው የሰላም ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል። ይህን ጉዳይ ኢዜማ ብቻ ሳይሆን በርካታ ፓርቲዎች እና ህብረተሰቡ ካለፉት ዓመታት በተሻለ የተረጋጋ እና ሰላማዊ ሁኔታ መኖሩን በንፅፅር እየገለፁ ይገኛል። በመሆኑም ምርጫ 2013 ሰላማዊ ሆኖ እንዲከናወን በሚሰሩ ስራዎች ላይ የሚወሰን ቢሆንም ሁኔታው የተሻለ እንደሚሆን ያላቸውን ፅኑ እምነት አስቀምጠዋል፡

ምርጫ 2013ን ሰላማዊ በማድረግ ረገድ ገዥው ፓርቲ /ብልፅግና/ ትንሹ የሚጠበቅበትን ሕገመንግስታዊ የሕግ የበላይነትን ማስከበር ሚና እየተወጣ መሆኑን ጠቁመዋል። ምርጫውን ሰላማዊ ከማድረግ አኳያ መንግስት የአንበሳውን ድርሻ የሚይዝ ቢሆንም ሕዝብ እና የመገናኛ ብዙሀንም ከመንግስት ያልተናነሰ ተግባር ማከናወን ይጠበቅባቸዋል ብለዋል አቶ የሽዋስ። ህብረተሰቡ በአሁኑ ወቅት ከተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆነ አክቲቪስቶች የሚሰነዘሩ ሀሳቦች በተለይ መርዛማ መልዕክቶችን ሳያላምጥ መውሰድ የለበትም። ህብረተሰቡ ከእነዚህ አካላት በተሻለ የተረጋጋ እና ሚዛናዊ በመሆን ፀረ-ሰላም እና ፀረ- ኢትዮጵያ አመለካከቶችን እስከ ድምፅ የመንፈግ እርምጃ በመውሰድ ሊያስተምራቸው ይገባል ሲሉ ለጉዳዩ አፅንኦት ይሰጣሉ።

**ለመፍትሄው መንግሥት ብቻ ሳይሆን ፓርቲዎችም በትኩረት ሲሰሩ ይገባል። ፓርቲዎች በግጭት ካለመሳተፍ ጀምሮ መፍትሔዎችን በማመቻቸት ግዴታቸውን ሲወጡ ይገባል**

በመሆኑም ግራ የሚያጋቡና የሚያደናግሩ መረጃዎችን የማጥራት እና ትክክለኛ መልካቸውን በሚገባ በመፈተሽ ትክክለኛውን ለሕዝብ የማቅረብ የመገናኛ ብዙሀን ተግባር አሁን ካለው በበለጠ በዘንድሮው ምርጫ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ሲሉ ይመክራሉ። በዚህ ረገድ የተበላሸ መረጃን የሚያስተላልፉ ፓርቲዎችና ጋዜጠኞችም ሥራቸውን በጥንቃቄ ሊያከናውኑ ይገባል ሲሉ የፓርቲያቸውን ቅድመ ግምገማ አስቀምጠዋል።

ከዚህ በበለጠ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ግብረሰናይ ድርጅቶች፣ አክቲቪስቶች መንግሥትም ጭምር ከሕዝቡ ጋር በተለየ ጥምረት የሚሰሩት ስራ አገሪቱ ያገኘችው እድል ወሳኝ መሆኑን አምነውና ተገንዝበው ሊሆን ይገባል። የዘንድሮ ምርጫ የኢትዮጵያን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የማዋለድ አንዱ ትልቅ ስር በመሆኑ በትኩረት ሊሰራበት ይገባል። በፓርቲው ግምገማ ላለፉት አምስት አገራዊ ምርጫዎች ሙከራዎች ተደርገዋል፤ነገር ግን የዴሞክራሲ ስርዓት ምኞት ብቻ ሆኖ ተጨናገፈ ሲሉ በቁጭት ተናግረዋል፤ አቶ የሽዋስ። እነዚህ ምርጫዎች ከሽፈዋል ተብለው የሚታለፉ አይደሉም፤ አገር እና ሕዝብን ችግር ውስጥ ከተው አልፈዋል። በመሆኑም የዘንድሮው ምርጫ እንደ ኢዜማ በከፍተኛ ኃላፊነት የሚወጣው መሆኑ የፓርቲው አቋም ነው። በመሆኑም ሁሉም የአገሪቱ ሕዝብ በየትኛውም ሙያ እና የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ቢሆንም በአገሩ ጉዳይ እኩል ባለድርሻ ስለሆነ የሚጠበቅበትን ሊያደርግ ይገባል ባይ ናቸው። ያም ሆኖ ይህ ግን ለምርጫው ሰላማዊነት የህወሓት መጥፋት እና የኦነግ ሸኔ እጅጉን መዳከም እና መጥፋት መልካም አጋጣሚ እንደሆነ አስቀምጠዋል።

## ተስፋና ስጋቶች

ከዚህ ምርጫ የሚጠበቀው ዋናው ውጤት በአገሪቱ ሰላም እና መረጋጋትን ማስፈን ነው የሚሉት ፕሮፌሰር መረራ በተለይ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ እንዴወለድ ማስቻል አለበት ብለዋል።ነገር ግን መሰረታዊ በሆነ መንገድ በገዥው ፓርቲና በተቃዋሚዎች መካከል በተደጋጋሚ ሲጠየቅ የነበረው ብሔራዊ መግባባት የትም አለመድረስ መንግስት ለጉዳዩ ምንም ትኩረት አለመስጠቱ ለምርጫው ሰላማዊነት አሉታዊ ጫና ይኖረዋል ሲሉ አመልክተዋል።

የህወሓት መወገድ እና የኦነግ ሸኔ መዳከም ብቻውን የምርጫ 2013ን ሰላማዊነት አልጋ በአልጋ ያደርገዋል ብሎ በየዋህነት መናገር እንደማይቻል የሚገልፁት አቶ የሸዋስ የተለያዩ ፈተናዎች ይኖራሉ የሚለውን ስጋታቸውን በማስቀደም ነው። ጥራዝ ነጠቅ እና ፅንፍ የወጣ አስተሳሰብን ወደ አንድ ለማምጣት የሚደረግ እንቅስቃሴ በተለይ በዘር እና በሃይማኖት ላይ የተንጠለጠለ በመሆኑ ፈተናው ይከብዳል። በብሔረሰብ ፣በሃይማኖት፣ በጎሳ እንዴሁም በአካባቢ ተቧድኖ የነበረን የፖለቲካ አስተሳሰብ ወደ አንድ ለማምጣት የሚደረገው ጥረት ቁልፍ ፈተና ነው ብለዋል።

‹‹ዴያስፖራ ሆኖ ከአገር ውጭ የነበረ፤ ግማሹ ጠመንጃ ታጥቆ በረሀ የወረደ፤ እኛን ጨምሮ ገሚሱ እስር ቤት የቆየ በመሆኑ ይህን አስተሳሰብ በአንድ ከተማ በተለይ



ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና

## ህብረተሰቡ በአሁኑ ወቅት ከተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆነ አክቲቪስቶች የሚሰነዘሩ ሀሳቦችን በተለይ መርዛማ መልዕክቶችን ሳያላምጥ መውሰድ የለበትም

በአንድ ጠረጴዛ አስቀምጠህ በሀሳብ እንድንፋጭ ማድረግ ትልቅ ስራ ነው፤›› ሲሉ አቶ የሽዋስ ይናገራሉ። ይህ ሁኔታ በአገሪቱ ካለው ድህነት እና ኋላቀርነት ጋር ተዳምሮ ፈተናውን የበረታ ያደርገዋል ብለዋል። የኢኮኖሚው ግሽበት እና የስራ አጥነት ቁጥር መብዛት በምርጫ 2013 ሰላማዊነት ላይ የራሱን ክንድ ያሳርፋል። ወጣቱ ስራ እንደልብ ማግኘት አለመቻሉ እና ለኑሮው የሚያስፈልገውን መሰረታዊ ግብዓቶች አለማግኘቱ ካለው የፖለቲካ ደንቃራ ጋር ተዳምሮ የምርጫውን አጠቃላይ ሰላም እንዳያውክ ስጋታቸውን አስቀምጠዋል።

ወደ ዴሞክራሲ የሚደረገውን ጉዞ ከፉኛ እየተገዳደረው የሚገኘው የማህበራዊ ሚዲያ ተደማሪ ፈተና እንደሚሆን አቶ የሽዋስ ይናገራሉ። በጣም በተለየ እና ሁሉም ሰው የፈለገውን በሚተፋበትና በሚወረውርበት ይህ ሜዳ ለምርጫው ፈተና ነው ብሎ ኢዜማ ያመለክታል። ፍፁም ተጠያቂነት የሌላቸው ሀገር ሊያፈርስ የሚያስችል አጥፊ መረጃ የሚያመላልሱ የበዙበት ሜዳ በመሆኑ ስጋቱን ከፍ ያደርገዋል። ማህበራዊ ሚዲያ ሀገር እስከማፍረስ የሚደርስባቸው በርካታ መልኮች እንዳሉት የሚጠቁሙት አቶ የሽዋስ ጉዳዩ ከእንጀራ ጋር ሁሉ የተያያዘ በመሆኑ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች የሚገኙበትም ነው። እነዚህ ዜጎች ምስሉንም ሆነ ፅሁፍ /Like/ ድጋፍ በመቁጠር እንጀራ የሚበሉበት መንገድ በመሆኑ ከህልውና ጋር ተያይዟል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል። አንድ ቤተሰብ የበላው የጠጣው ሳይቀር የተነጋገረው ጉዳይ ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ተዝረክርኮ ስምህ የሚጠፋበት፤ ፍፁም ኃላፊነት የጎደለው ተግባር ሆኖ ዜጎች በተለይ ንፁሀን ዳግመኛ እንዳይነሱ የሚመቱበት ሆኖ በተግባር ታይቷል። ይህ ሁኔታ በተለይ በምርጫ ወቅት ከእሳት በላይ ይለበልባል ብለዋል።

ፓርቲዎች ሀሳብ ላይ የሚንጠለጠሉ ከሆነ ሀሳቦች መቀራረብ ይችላሉ፤ ወጣቱ ህይወት ላይ ለመንጠልጠል ከሆነ ደግሞ ሕዝብ ሌላ ዋጋ መክፈል የለበትም ሲሉ የኢዜማ ሊቀመንበር አፅንኦት ይሰጣሉ። ፓርቲዎች በወጣቱ ህይወት ላይ ሲንጠለጠሉ የምርጫውን ሰላማዊነት በማደናቀፍ ራሳቸው ፈተና ይሆናሉ። ፓርቲዎች /ኢዜማን ጨምሮ/ አዴስ የዴሞክራሲ ሥርዓትን በአገሪቱ ለማዋለድ መስራት ላይ ብቻ ትኩረታቸው ሊሆን ይገባል ሲሉ መልዕክታቸውን ያስተላልፋሉ። በመሆኑም ሀሳብ ለመሸጥ የመጣ ተወዳዳሪ ፓርቲም ሆነ ግለሰብ ሕዝብን ላለማስጨረስ አስቀድሞ ቃል መግባት ይጠበቅበታል።

የኦሮሞ ነፃነት ግንባር በውስጥ ችግር እየተናጠ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ቀጀላ ለምርጫው ዝግጅትም ከፍተኛ ጫና እንደፈጠረባቸው ይናገራሉ። ምናልባትም በምርጫው ላይሳተፉ እንደሚችሉ አፅንኦት ሰጥተው ተናግረዋል። በውስጥ አሰራር ያጋጠማቸው ችግር በአገሪቱ የፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ሕግ የማይፈቀዱ ሁኔታዎች ተወጥሯል ሲሉም ጉዳዩን አስረድተዋል። በሚሊዮን የሚቆጠር ደጋፊ ስላለው በአገሪቱ ምርጫ ላይ አንድ ፈተና ሊሆን ይችላል የአቶ ቀጀላ ሀሳብ ነው። ኦነግ ውስጥ በአንድ በኩል ለችግሩ መንግሥትን ጥፋተኛ የሚያደርግ አካል ያለበት፤ በሌላ በኩል ዋናው የውስጥ ችግር ሳቢያ ፓርቲው አጣብቂኝ ውስጥ ገብቷል ብለዋል።

ምርጫ 2013 ሰላማዊ ሆኖ እንዳይከናወን ትልቁ ፈተና እየተፈፀሙ ያሉ እስሮች ናቸው ያሉት ፕሮፌሰር መረራ ለምርጫ በምንሳተፍባቸው አብዛኛው ኦሮሚያ ውስጥ ገዥው ፓርቲ ቢሮዎችን ዘግቷል። ብዛት ያላቸው አባላት በተለይ ፓርቲያችን ለበርካታ የምርጫ ስራዎች የመደባቸው አባሎች ሳይቀሩ ያለበቂ ምክንያት መታሰራቸውን ጠቁመዋል።

‹‹ኦነግን ጨምሮ ከመንግሥት ጋር የተወሰኑ ምክክሮች ነበሩ። እሱም አልተፈታም። የኦነግ ችግር ከእኛ የባሰ ነው፤ ብዙ አባላት ታስረውባቸዋል። ቢሮዎቻቸው ከአዴስ አበባ ጀምሮ በአብዛኛዎቹ ተዘግተዋል። ብሔራዊ መግባባት የምንለው ታጣቂዎችን፣ የታሰሩ የፖለቲካ ኃይሎች ወደ አንድ መጥተው ፍትሐዊ ምርጫ እናድርግ፤ይሄም ይቻላል ነው የምንለው፤››ሲሉ ፕሮፌሰሩ አመልክተዋል።

ኢዜማ እንደ ፓርቲ በበርካታ ክልሎች የአባላት እስር እና የቢሮ መዘጋት እንዳጋጠመው አቶ የሽዋስ አስታውቀው ፓርቲው በመላ አገሪቱ ስለሚወዳደር ጥቃቱ የተወሰነ ቦታ ላይ ብቻ አይደለም ይላሉ። ችግሩ ከመንግስት እና አካባቢው ‹‹የእኛ ነው›› ከሚሉ የሰፈር ጎረምሶች በሁለት መንገድ የሚከሰት ነው። በኦሮሚያ፣ትግራይ፣ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ችግሮች ነበሩ፤ የተሻለ የነበረው በደቡብ ክልል እና አዴስ አበባ ነው። በመሆኑም ኢዜማ ችግሮች ቢኖሩበትም እነዚህን ተቋቁሞ እየሰራ ይገኛል ብለዋል።

‹‹ኦሮሚያ ውስጥ ቢሮ ይዘጋብናል፤ ትግራይ ውስጥ በተደጋጋሚ እየተዘጋብን በቅርቡ ነው የከፈትነው። ትግራይ ውስጥ ለአብነት ዘጠኝ ወረዳ ውስጥ የነበረንን ቢሮ ወደ ሁለት ሶስት ዝቅ ብሎ አባሎቻችን እየተሳቀቁ ነበር የሚሰሩት። ከሕግ ማስከበሩ በኋላ ብልፅግናን ጨምሮ ፓርቲዎች ቢሯቸውን እየከፈቱ ነው›› ሲሉ አቶ የሽዋስ ይገልፃሉ።

ብልፅግና ፓርቲ በምርጫው ተወዳድሮ ማሸነፍ የሚፈልገው የፓርቲ አባላትን በማሰር አሊያም ቢሮዎችን በመዝጋት አይደለም ሲሉ ሀሳባቸውን ያቀረቡት አቶ ዛዴግ ይሄ አካሄድ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ብቻ ሳይሆን ሀሳብ የሌላቸው አካላት የሚጠቀሙት አካሄድ ነው። ብልፅግና በአገሪቱ ሰላም ፣ዴሞክራሲና እድገት ሊያመጡ ይችላሉ ያላቸውን ሀሳቦች ለሕዝብ አቅርቦ ሕዝብም አምኖበት እንዲመርጠው ነው በሀቅ እየሰራ ያለው። በራሱ አሊያም ሕግን ጥሶ የታሰረን አካል በሕግ አግባብ መጠየቅ እንጂ ለመወነጃጀል የሚውል መሆን የለበትም፤ ተገቢም አይደለም ብለዋል።

ማንም ፓርቲ እንዳይወዳደር ታግዶ፤ ቢሮ ተዘግቶበት በምርጫ እንዲሳተፍ ብልፅግና አይፈልግም። ሙሉ በሙሉ ሀሳብ ላይ ተመስርቶ በምርጫው አሸናፊ መሆን ይፈልጋል። ሁሉም ነገር ተሰርቶ ቅሬታ ቢኖር ባለው ሥርዓት በመነጋገር ይስተካከላል። በፓርቲ ደረጃም ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅሬታ ሲኖራቸው ምርጫ ቦርድ እየሰበሰበ ችግሩ የሚፈታበት የሶስትዮሽ ተጨማሪ ሥርዓት አለ። ይህ በኦሮሚያ፣ቤኒሻንጉል እና ሌሎች አካባቢዎች ተግባራዊ እየተደረገ ነው።

በአጠቃላይ ችግር የደረሰባቸው ፓርቲዎች በምርጫ በሚሳተፉበት የትኛውም ቦታ ያጋጠማቸውን ችግር በተዘረጉ መድረኮች አቅርበውት ሊፈታ ይገባል። ብልፅግና ሁሉም ፓርቲ በምርጫው እንዲሳተፍ ይፈልጋል። ፓርቲዎች የሚያጋጥማቸው ችግር ካለም ተረዳድቶ አንድም ፓርቲ ሳይቀር የአቅሙን እንዲወዳደር በዘመቻው ተሳትፎ ሕዝብም ሀሳቡን ተረድቶ እንዲዳኘው እንፈልጋለን።

## ምርጫ ቦርድ

‹‹የምርጫ ቦርድ መዋቅር እያስደነገጠን ነው። መዋቅሩ ወደታች ሲዘረጋ በየዞኑና ወረዳው ምርጫውን ያስፈፅማሉ ተብለው ተመልምለው የተመደቡ አስፈጻሚዎች የማይመጥኑ ናቸው። የሕግ እና የፖለቲካ ሳይንስ ሌላው ቢቀር የሶሻል ሳይንስ እውቀት እንኳ ያላቸው ሳይሆኑ ዝም ብሎ የተመደቡ ናቸው። ኤሌክትሪሺያን፣ እንጨት አውራጅ፣ተላላኪ ቢልም ቦታው የምርጫ ጉዳይ በመሆኑ እነዚህን ሙያዎች አይመጥንም፤›› ሲሉ መድረክ በሊቀመንበሩ በኩል ወቅሷል።

ከዚህ ቀደም አስፈጻሚዎች የሚታሙት በሌብነት ነው፤ የአሁኖቹ ደግሞ ምርጫን በማስፈፀም እውቀት ችግር ነው። በመሆኑም የበለጠ ሊበጠብጡና ምናልባትም ያልተጠበቁ ችግሮችን ሊፈጥሩ ይችላሉ ብለው ሁኔታውን ለምርጫ ቦርድ ሰብሳቢዋ መናገራቸውን ጠቁመው ነገር ግን በጉዳዩ ላይ በቂ ምላሽ አልተሰጠም ባይ ናቸው። ‹‹በአጠቃላይ በምርጫ አስፈፃሚዎቹ እምነት እንደሌለን ለምርጫ ቦርዱ ፅፈን አስገብተናል። ምንም መልስ አልተሰጠንም። ምርጫ ቦርድ ግን ጨዋታውን ቀጥሏል። በእነዚህ ጥቅል ጉዳዮች በምርጫ ቦርዱም ምንም እምነት የለንም።›› ሲሉ ፕሮፌሰሩ አመልክተዋል።

ምርጫ ቦርድ በሰው ኃይል፣ በመዋቅርም ሆነ በሕግ ማቋቋሚያም ገና እየተፈጠረ ያለ ተቋም ነው። በመሆኑም በለውጥ ሂደት ላይ ያለ ተቋም ነው። አሁን ምርጫ ቦርድ ላይ የሚሰጠው አስተያየት ‹አንድ ህፃን ተወልዶ፤ ወዲያው እሩጥ› እንደ ማለት ነው ሲሉ አቶ የሽዋስ የፕሮፌሰርን ሀሳብ ይቃወማሉ። ተቋሙ እየተፈጠረ ያለ ብቻ ሳይሆን በዚህ ምስረታው ምርጫ እንዲያስፈፅም ሌላ ግዴታ የተጣለበት መሆኑን በቅጡ መረዳት ያስፈልጋል ሲሉ ሀሳባቸውን አቅርበዋል።

ምርጫ ቦርድ አሁን ያለበት ሁኔታ ይህን ይመስላል ማለት ከዚህ በፊት ችግር የለበትም፤ ቅዱስ ነበር እየተባለም አይደለም። ከዚህ በፊት የነበረው መዋቅር ስልጠና አግኝቶና ተሻሽሎ ካልመጣ ወይዘሪት ብርቱካንን እና የቦርድ አባላትን በመምረጥ የሚመጣ ለውጥ የለም። አሁን ያሉት መሪዎች ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታው ያላቸውን ፍላጎት እና ቀናኢነት ማየት ያስፈልጋል። በወይዘሪት ብርቱካንም ሆነች በዶክተር አብይ ዙሪያ ያሉ መሪዎች ሁኔታውን በሚገባ ተረድተው እንዲሰሩ ጠንካራ የፖለቲካ ቁርጠኝነት እንደተያዘ በግልፅ የሚታይ ነው ብለዋል፤ አቶ የሺዋስ።

እንደ አቶ የሺዋስ ገለፃ ይህን ሁኔታ በደንብ ተረድቶ የሚፈጠሩ ችግሮችን አብሮ በጋራ መፍታት እንጂ ‹‹እምነት አጥተናል›› ማለት መፍትሔ አይደለም። በዚህም ሁኔታ ‹ወደቀ ሲባል ተሰበረ› እያልን ተቋም መመስረት አንችልም፤ ሰላማዊ ምርጫ ለማከናወን ስለሚያዳግት አገራችንን ወደምንፈልገው የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማሻገር አንችልም። የሚፈጠር ችግርም ቢሆን የእኛው ጉድ ስለሚሆን አብረን መስራት ነው የሚገባን። ነገር ግን ሁኔታው የማያሰራ እና ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ከሌለው እንጂ ሙያ ነክ ጉዳዮችን በጋራ ቁጭ ብሎ መፍታት አንዱ የዴሞክራሲ ሥርዓት የቤት ሥራ ነው።

ምርጫ ቦርድ ላይ ሶስት ነገሮች ተለውጠዋል። አንዱ የሰው ኃይል ነው፤ የሰው ለውጥ ሲደረግ ባልተለመደ ሁኔታ ሁሉም የፓርቲ አመራር ‘እከሌ ቢሆን እከሌ ቢሆን’ የሚል አስተያየት ሰጥቷል። የመዋቅር ለውጥ ታች ድረስ ሊደረግ ሲል ፓርቲዎች በእያንዳንዱ ሰው ላይ ግልፅ አስተያየት እንዲሰጥ እድሉ ተመቻችቷል። ይህ በሁሉም ክልል በተመሳሳይ ሁኔታ የተፈፀመ ነው። ችግር አይኖርም ባይባልም ችግሩ የጋራ ነው ብሎ በጋራ የመፍታት ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ በመሆኑ ችግር ሲከሰት የምንወራወረው ጉዳይ መሆን የለበትም። ስለሆነም ችግር ሲፈጠር የአሜሪካ አሊያም የሌላ ወዳጅ አገር ምርጫ ቦርድ የሚያስፈፅምልን አይደለም። ስለዚህ ችግሩን መረዳትና መፍታት ያስፈልጋል።



አቶ ቀጀላ መርዳሣ

## አለመሳተፍና መሳተፍ ለምን ስጋት ይሆናሉ?

በምርጫ ወቅት ከውጤት ጋር ተያይዞ ፓርቲዎች የማሸነፍ ዕድላቸውን በግልፅና ምክንያታዊ በመሆን ገምተው መግባት አለባቸው የሚሉት አቶ የሺዋስ አንድ ፓርቲ የማሸነፍ እድሉ 50 በመቶ ሲሆን፤ የመሸነፍ እድሉም ተመሳሳይ ነው። ኢዜማ ሊያሸንፍ አሊያም ሊሸነፍ እንደሚችል አምኖ ነው የሚገባው። ካሸነፈ ያሸነፈውን ክልልም ይሁን ዞን፣ወረዳም ይሁን ቀበሌ ያስተዳድራል። በመሆኑም ሕዝብ የሰጠውን አደራ ለመቀበል ዝግጁ ነው። ከተሸነፈ ደግሞ ውጤቱን ተቀብሎ ስህተቱን አሻሽሎ ለቀጣይ ይዘጋጃል። ለአንድ ጊዜ ምርጫ ብቻ የሚደረግ ዝግጅት የለም።

ሁሉም ተወዳዳሪ ፓርቲ በዚህ ልክ መዘጋጀት አለበት። ነገር ግን በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ድጋፍን ቆጥሮ ‹‹አሸንፌያለሁ፤ አልቋል ነገሩ፤ ምርጫ ቦርድ የሚለውን ውጤት ተቀበል›› የሚል ፓርቲ ካለ ጨዋታው ሌላ ይሆናል ማለት ነው። ምክንያቱም በማህበራዊ ሚዲያው ላይ /ላይክ/ ድጋፍ የሚሰጠው ሰው አሜሪካ አሊያም አውሮፓ ሆኖ እንጂ አገር ውስጥ አይደለም። ‹‹መራጩ ደግሞ የእኛ ወረዳ ሕዝብ ነው። የወረዳው ሕዝባችን ደግሞ አንዱም ማህበራዊ ሚዲያ ላይጠቀም ይችላል፤ በመሆኑም የማህበራዊ ሚዲያው ጩኸት ሀቁን አያሳይም።›› ያሉት የኢዜም ሊቀመንበር ለምርጫ የሚኖር

**ሕግን ጥሶ የታሰረን አካል በሕግ አግባብ መጠየቅ እንጂ ለመወነጃጀል የሚውል መሆን የለበትም፤ ተገቢም አይደለም**

ስነልቦና ሀቅ ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባል ባይ ናቸው።

ስለሆነም ከተሸነፉ ውጤቱን ለመቀበል መዘጋጀት ይገባል። በማስፈራራት፣ ‹‹እንዴህ አደርጋለሁ›› ማለት ፍፁም አይሰራም። በዚህ ቅኝት ውስጥ መጓዝ እንጂ ‹የአንዱ ደረት ከብረት፤ የሌላው ከካርቶን› የተሰራ አድርጎ በማሰብ በጉልበት ውጤትን መጠበቅ አይገባም። ‹‹እኛ ወንድማማቾች ነን፤ ለምን እንጠፋፋለን? ነገር ግን የውድድር ሜዳውን በሚያሳምነን ልክ የእኛ እናድርገው፤ ለዚህ የተከበረ ሕዝብ ደግሞ በታሪካችን የሚፈልገውን መሪ እንዲመርጥ አቅም እንሁን›› ሲሉ አቶ የሺዋስ ጦረኛነት አያስፈልግም፤ አይገባምም ብለዋል።

ፕሮፌሰር መረራ በአቶ የሺዋስ ሀሳብ በመስማማት ሲገልፁ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ቢሸነፉም ቢያሸንፉም በሀቅ የሚደረግ የምርጫ ውድድር ውስጥ መግባት አለባቸው። ፓርቲዎች ቢሸነፉም ችግራቸውን ሁሉ ወደ ገዥው ፓርቲ ማጣበቅ የለባቸውም ብለው ፓርቲዎች የራሳቸውን ስጋትና ጭንቀት ወደ ገዥው ፓርቲ መውሰድ አይገባም።

ወደ ገጽ 24 ዞሯል

# የምርጫ 2013 ሰላማዊነት...

ከገጽ 21 የዞረ

አነግ በምርጫ 2013 የማይሳተፍ ከሆነ የአገሪቱ የምርጫ ሂደት ሰላማዊ ሆኖ እንዳይጠናቀቅ ትልቅ ችግር ይፈጥራል የሚሉት አቶ ቀጀላ ፓርቲው ከምርጫው የሚገለልበት ጠንከር ያሉ ገፊ ምክንያቶች ቢኖሩም ተጠያቂው የድርጅቱ ሊቀመንበር ነው። በዚህ ጉዳይ ምርጫ ቦርድ አስተዳደራዊ ካልሆነ በስተቀር ሕጋዊ ውሳኔ ሊሰጥ አይችልም ብለዋል። አነግ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ወደ ምርጫው የማይገቡ ከሆነ የሰላም መደፍረስ ሊያስከትል ይችላል።

አቶ የሺዋስ በአቶ ቀጀላ ሀሳብ አይስማሙም። የትኛውም ፓርቲ በውስጥ ችግሩ ምክንያት በምርጫው ስለማይሳተፍ ሰላም አይኖርም ማለትም ሆነ በምርጫው ተሸንፎ ሲያበቃ አልቀ በልም «እኔ አሸንፌያለሁ» ማለቱ በዴሞክራሲ ሥርዓት ልኬት ስታየው «ሕዝቡ የእኔን ሀሳብ ብቻ ነው የሚጠብቀው ሌላ ሀሳብ የለም፤» የሚል ያልሰለጠነ መልክ ውስጥ ተገባ ማለት ነው። ይህ ለራስ፣ ለፓርቲም ሆነ ለአገር አይጠቅምም፤ አያስፈልግም።

እንደ አቶ የሺዋስ ገለፃ ለሀገር አቀፍ አስር ሺ፤ የክልል አራት ሺ አስፈርሙ ተባለ። የተሟላ መዋቅር ስላለን ለእኛ ቀላል ነበር። ለአንዳንድ ፓርቲዎችም ተመሳሳይ ችግር አልነበረባቸውም፤ በተሳካ ሁኔታ አስፈርመዋል። አንዳንዶቹ ግን የሚጠበቅባቸውን ማስፈረም ሳይችሉ 40 ሰው አባል ሳይኖራቸው «እኛ የተሰረዝን እንደሆን ሰማይ እና ምድር ነው የሚጣበቀው» አሉ። ነገር ግን ምንም የሕዝብ ድጋፍም ሆነ የሚፈለግ የአባላት ብዛት አላሟሉም፤ አልተመዘገቡም፤ በዚህም ከፉከራቸው ውጭ የመጣ ነገር የለም።

በዚህ ምርጫ ከሁሉም ተወዳዳሪ ፓርቲ የሚጠበቀው የተቀመጠውን ሕግና ሥርዓት አክብሮ መስራት እንጂ አለመመዝገባቸውን የሀገር ችግር አድርገው ማምጣት አይገባቸውም። ራሳቸውን የአለም ፍጻሜ አድርገው የተናገሩ ሰዎች እኮ አለፉ፤ ከእነዚህ ሰዎች እንዴት አንማርም። ይህ እኮ ከዚህ በኋላ አይሰራም። «አሁን አልተዘጋጀሁም፤ ለቀጣይ በሁሉም ረገድ ተዘጋጅቼ እመጣለሁ» ማለት ይሻላል። ነገር ግን የሕዝብ ወኪል ሳይሆኑ፤ ሕዝብ ሳይመርጣቸው ራሳቸውን «ወኪል ነን» ብለው መቅረብ አይገባም የአቶ የሺዋስ አስተያየት ነው።

## ምን ይሰራ?

ኢትዮጵያ ውስጥ እንደ እድል ሆኖ 51 በመቶ የሚባል ብሔረሰብ የለም። በጣም ብዙ ነኝ የሚለው እንኳ 20 ወይም 25 በመቶ ነው። የጋራ አገር እንጂ ማንም ጠፍቶ ማንም መኖር እንደማይችል የሚያሳይ ነው፤ በቅርብ እየወጡ ያሉ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ከ40 እስከ 45 በመቶ የሚደርሱ ዜጎች ውህድ ማንነት ያላቸው ናቸው። በመሆኑም መጪው ሁኔታ የተለየና የተሻለ ነው።

እንደ አቶ የሺዋስ ሀሳብ አሁን በአገሪቱ ያለውን ይህን እውነታ በቅጡ መረዳት በቅድሚያ ከመንግሥት የሚጠበቅ ነው፤ በመሆኑም ትልቁ እድል ብልፅግና ፓርቲ እጅ ነው፤ በተለይ ደግሞ ዶክተር አብይ። ዋናው የመንግሥት ሥራ ሕግ ማስከበር ነው። የፖሊስ ተቋም፣የደህንነት ተቋም፣ የመከላከያ ተቋም፣ የሰላም የፀጥታ እና የፍትህ ተቋማት «የፖለቲካ ምህዳሩ ሰፋ፤ አልሰፋ» እያሉ መናገር አይገባቸውም፤አይመለከታቸውም። በእርግጥ እነዚህ ተቋማት የማያልፏቸው መስመሮች አሉ፤ እነዚህን ለይቶ መስራት ይገባቸዋል።

ሀገረ መንግሥቱ እንዴቀጥል ሕግ መከበር አለበት። ምክንያቱም ከአገር በተቃራኒው መቆም አይቻልም። በቅርቡ በአሜሪካ ምርጫ የታየው ሀቅ ስንመለከት ከሥልጣን የተወገዱት ትራምፕ እንደ ግለሰብ የፈለገውን ሊሆን ቻለ፤ ነገር ግን ከአሜሪካ በተቃራኒው መቆም እንደማይችል የፍትሕ ስርዓቱ/ተቋማት/ ዓለምን ጭምር አስተማሩበት።

ፕሮፌሰር መረራ ሕግ ማስከበር ላይ «የተለየ አስተያየት አለኝ» ይላሉ። ጠዋትና ማታ የሕግ የበላይነት እየተባለ እስኪሰለች ድረስ ይነገራል። ማን ነው በአገሪቱ የሕግ የበላይነትን የሚጥሰው? የሚለው በአግባቡ አይመለስም። ፍርድ ቤት ሁለት ሶስት ጊዜ ፈቶት፣ ፖሊስ ደግሞ ደጋግሞ ያስርብናል። ስለዚህ ገዥው ፓርቲም ሆነ ተቃዋሚዎች ሕግና እና ሕዝብን ማክበር አለባቸው የሚሉት ፕሮፌሰር መረራ የዴሞክራሲ ተቋማት የሚባሉትም ቢሆኑ ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው ይላሉ። ነገር ግን ገዡው ፓርቲ ካላንቀሳቀሳቸው ምንም አይሰሩም። ብቻቸውን መስራት እንደማይችሉ ብዙ ማሳያ ማቅረብ ይቻላል ሲሉ ይመክራሉ።

«ሕግን ማክበር እና ማስከበር የብልፅግና ፓርቲ መለያው ነው። ያለ ምንም ድርድር አገራዊ የሕግ ማስከበር ሕገመንግሥታዊ ግዴታውን ለሚፈለገው የዴሞክራሲ ሰርዓት ግንባታ ትዕግስት በተሞላበት አካሄድ እየፈፀመ ነው፤ ዜጎችም እንዲፈጽሙት እያደረገ ይገኛል። በአጠቃላይ ፓርቲው በአገሪቱ ያሉ የጫወታ ሕጎችን በማክበር ወደ ምርጫው የገባበት ሁኔታ የመጀመሪያው ተግባሩ ነው፤» ሲሉ አቶ ዛዴግ የሕግ ማስከበሩን ጉዳይ አፅንኦት ሰጥተዋል።

ሁለተኛው ጉዳይ ብልፅግና ገዥ ፓርቲ በመሆኑ ሌላ ተጨማሪ ድርብ ኃላፊነት አለበት። ይህ ኃላፊነት የዜጎች ደህንነት የተሟላ እንዲሆን ወደ ምርጫ ጣቢያ ከመሄድ ጀምሮ ዜጎች ደህንነት እንዲሰማቸው ያደርጋል። በተለያዩ ምክንያቶች ከቀያቸው የራቁ ዜጎች ወደ አካባቢያቸው እንዲመለሱ የሚያስችል ሰላም የማስከበር ሥራ በሚገባ ማከናወን እንደሚጠበቅበት አቶ ዛዴግ ይገነዘባሉ።

ገዥው ፓርቲ የፀጥታ ተቋማትን በማስተባበር ምርጫ ቦርድም ያለበት አንድ ኮሚቴ ተቋቁሟል። ይህ ኮሚቴ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ገብቷል። ስለዚህ ግጭት ለመቀነስ ብሎም ለማስቀረት የሚያስችል ሥራ እየሰራ ነው ብሎ ያምናል ያሉት አቶ ዛዴግ መንግሥት ግጭትን ለማስወገድ የሚያስችል ቁመና ላይ ከመኖሩ በተጨማሪ ችግር ሲያጋጥም የሚፈታበትን ሥርዓት በመዘርጋቱ የትኛውም ፓርቲ አለ የሚለውን ችግር ወይም ቅሬታ አቅርቦ ይፈታል የሚል እምነት ተይዟል። ‹አንድ እጅ ብቻውን አያጨበጭብም› እንደሚባለው ተፎካካሪ ፓርቲዎችም ምርጫው በአገሪቱ ታሪክ ዴሞክራሲን በሚገባ ለማዋለድ መሆኑን ተገንዝበው በምርጫው ሰላማዊነት ላይ የጋራ ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል።

ስለዚህ በአገር ላይ ሕግ ማስከበር ምን ማለት ነው? ሕገ መንግሥቱን በሥርዓት እስከምንቀይረው ድረስ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማው፣ መዝሙሩ፣ ብሔረሰቦች፤ ሃይማኖ ቶችን መንካት ወይም እንዲጋጩ ማድረግ ለማንም መፈቀድ የለበትም። በምርጫ ክርክር ወቅትም እነዚህን መጠለያ ማድረግ አይገባም የአቶ የሺዋስ ምክረ ሀሳብ ነው። ይህን ሥርዓት ማስከበር ደግሞ የመንግሥት ነው። ዶክተር አብይ አገሪቱን ወደሚፈለገው ደረጃ አሸጋግረው በታሪክ እንደ ማንዴላ ሊነሱ የሚችሉበት እድል አለ ሲሉ ጠቁመዋል፡

«ማንዴላ ከ27 ዓመት እስር በኋላ አራት ዓመት ነው የመሩት፤ ነገር ግን ዛሬ ድረስ ማንዴላ የደቡብ አፍሪካ የሁልጊዜ መሪ ናቸው። ከእርሳቸው በኋላ ብዙ መሪዎች ተቀያይረዋል። ማንዴላ ግን እነዚህን ሁሉ ተሻግረው ስማቸው የሚጠራ መሪ ናቸው። ስለዚህ በኢትዮጵያም ዶክተር አብይ ይህን የመሰለ እድል በእጃቸው አለ። በመሆኑም ይህን ፕሮጀክት በትክክል ማጠናቀቅ ከቻሉ ስማቸውን ይተከላል ብለዋል» አቶ የሺዋስ።

የፖለቲካ ፓርቲዎችም ቢሆኑ «የ60ዎቹ ትውልድ ተበላሸ፤አበላሸ» እየተባለ ሲናገሩ ይታያል ያሉት አቶ የሺዋስ ዛሬም እንደትናንቱ በእጃችን ያለውን የአሁኑን ትውልድ እንዳናበላሸው በተለይ ምርጫውን በጥንቃቄና ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ ማከናወን ይገባል፤ ይጠበቃልም። ይህ እድል እንዳለፉት የ60ዎቹ የሚበላሽ ከሆነ እከሌ ፓርቲ አበላሸው አይባልም ፤’ይህ ትውልድ አበላሸው’ ነው የሚባለው። ስለዚህ ተወቃሽ ትውልድ ላለመሆን ጭምር መሥራት ይገባል። በተወዳዳሪነትም ሆነ በመራጭነት የሚሳተፈው የትኛውም ዜጋ ኃላፊነት ወስዶ ሊሰራ ይገባል።

በአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት እድሉ አለ ሲባል አጠቃላይ የፖለቲካ ሁኔታው የተሻሻለ መሆኑ ነው የሚሉት ፕሮፌሰር መረራ ወዳጅ አገራትም ሆኑ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ሲንቀሳቀሱ ይታያል። የአገር ሽማግሌዎች አባገዳዎች እና ትላልቅ የሃይማኖት አባቶች በነፃነት ሲንቀሳቀሱ ይታያሉ። ገዥው ብልፅግና ፓርቲ ያለውን ቁርጠኝነት በሚገባ ይዞ ከዘለቀ በእርግጥም ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ሊወለድ ይችላል የሚል ተስፋ አለ። ተስፋዬ ከገዥው ፓርቲ በተለይ ያሉ መልካም ተሞክሮዎችና ልምዶችን በሚገባ ከወሰድን ዴሞክራሲ እውን ይሆናል።

«ከምርጫ በኋላ አገር አለች፤ ትቀጥላለች። ለሥልጣን ሁላችንም እንፎካከራለን ነገር ግን ምርጫን እንደ አንድ የዓለም ፍፃሜ አድርገን ከምርጫው በኋላ የአገርን ቀጣይነት ሳናስብ ወደ ምርጫ መገባት የለበትም ፓርቲያችን ወደ ምርጫ ዘመቻ ሲገባ የሚፎካከራቸው ፓርቲዎች እንዳሉ በመገንዘብ በወንድማማችነት መንፈስ ነው። ለሥልጣን እየተፎካከርን ሕዝብና አገርን ማሰብ ይገባል።» የአቶ ዛዴግ መልዕክት ነው።




# አካባቢያዊ ስጋት የፈጠረው የሶማሊያ ምርጫ

**ማለደ ዋስይሁን**

የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ጥበቃ ምክር ቤት ሶማሊያን በተመለከተ ‹‹February 2021 Monthly Forecast›› በሚል ባወጣው ሪፖርት የሶማሊያ የወቅቱ የምርጫ ሁኔታ የደቀነው ስጋት እንዳለ ይተነትናል።

ሶማሊያ ከብዙ ውጣ ውረዶች በኋላ የፌደራል መንግሥት በማቋቋም ተስፋ ሰጪ ጅምር ላይ ነች የተባለው በ2012/እ.አ.አ/ ነበር። የዚያን ጊዜው ምርጫ ሃሰን ሼክ መሐመድን ፕሬዚዳንት፣ አብዴ ፋራህ ሺሮንን ጠቅላይ ሚንስትር አድርጎ መርጦ ነበር። በወቅቱ የተጀመረው የምርጫ ሥርዓትም በየጊዜው እያደገ ሶማሊያም ሀገራዊ አቋሟ ጠንካራ እየሆነ እንደሚሄድ ተስፋ ተጥሎበት ቆይቷል። የሶማሊያን የወደፊት እጣ ፈንታ ብሩህ ለማድረግ፣ የፌደራሉንም ሥርዓት ለማጠናከር፣ ሕገ መንግሥቱንም የቀና ለማድረግ፣ ዴሞክራሲያዊነትን ለማስፋፋት፣ ሀገሪቱ በ2016 ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ ለማድረግም ውጥን ነበር።

ይህን ውጥን ግን ለሚመረጡ መሪዎችም ሆነ ለሚመሠረተው መንግሥት ተፈጻሚ ለማድረግ በሚያደርገው ጥረት ውስጥ የገጠሙት ፈተናዎች የዋዛ አልነበሩም። የመጀመሪያው የአልሸባብ ከፍተኛ የሽብር እንቅስቃሴ ነበር። ስለዚህም እርምጃው ሁሉ ከብሩንዲ፣ ከኢትዮጵያ፣ ከኡጋንዳ፣ ኬኒያ ሴራሊዮንና ጂቡቲ የተውጣጡ እስከ ሃያ ሺህ በሚደርሱ የአፍሪካ ሰላም አስከባሪ ኃይሎች ለመደገፍ ተገዷል። ይህም ሆኖ አልሸባብ ተደጋጋሚ ጥቃቶችን ሲሰነዝር ቆይቷል። የሀገር ውድቀትን፣ ረሃብን፣ የባሕር ላይ ዝርፊያን እና የአልሸባብን የሽብር ጥቃቶች ስታፈራርቅ የቆየች ሀገር በተጨማሪ ሀገሪቱ የህግ የበላይነትን የማስፈን፣ የህገመንግሥቱን ውስንነቶች የመሸከም፣ ብቃት የሌለው አስተዳደር ዘይቤ፣ የህዝብ ደኅንነት ጉዳይና መሰል ችግሮችም ወጥመድ ሆነውባታል።

ያም ሆኖ እንኳን በ2016 ከበፊቱ የተሻለ ምርጫ የማድረግ እንቅስቃሴ ታይቷል። በ2016ቱ ምርጫ አዳዴስ ተሳታፊ ሶማሊዎች የታዩበት፣ በተለይም የዲያስፖራው ማኅበረሰብ የታደመበት፣ ከፓርላማ አባልነት እስከ ፕሬዚዳንትነት ብርቱ ፉክክር ለማድረግ ከሞቃዴሹ ባሻገር በሌሎችም ኪስማዮ፣ ጋሮዌ፣ ባይደዋ፣ አዳዶን በመሰሉ ከተሞችም ሰፊ ቅስቀሳ ይደረግ እንደነበር ይታወሳል።

ይህ ሁኔታ በቀጣዩ ምርጫም በ2020 የተሻለና ተአማኒነቱ የጨመረ ሆኖ እውን ይሆናል በሚል ተስፋ የ2016 ምርጫ ሂደትና ውጤትን በማበረታታት ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ለሶማሊያ ትኩረት ሰጥቶ ቆይቷል። ጊዜያት አልፈው ዓመታት ተቆጥረው ዛሬ ላይ የምርጫው ጊዜ ላይ ተደርሷል። ድባቡ ግን ምን ይመስላል የሚለው የዚህ ጽሑፍ ዋነኛ ትኩረት ነው።

## የቅድመ ምርጫ ፈተናዎች

በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ያሉ ሀገራት እርስ በእርስ ካላቸው ፍሬያማ ያልሆነ ግንኙነት በላይ ስጋት እየፈጠረባቸው የመጣው የውስጥ ፖለቲካዊ አለመረጋጋትና መከፋፈል ነው። ይህ ሁኔታ ተጨባጭ አድርጎ ለመረዳት በቀላሉ በሱዳን በኢትዮጵያና በሶማሊያ ያሉ የውስጥ ፖለቲካዊ አለመረጋጋትን ማጤን በቂ ነው።

የሶማሊያ የውስጥ አለመረጋጋት ግን በአሥርት ዓመታት የተቆጠረ በመሆኑና በውጤቱም ሶማሊያን ወደ መከፋፈል ያመራና ፌደራል ሥርዓቱ ውዳቂ ሆኖ መታየቱ ነው። እነዚህን ሁኔታዎች ለማሻሻል በየአራት ዓመቱ የሚደረግ ምርጫ ተስፋ የሚደረግበት ቢሆንም የሶማሊያ ጎሳዎች አለመደማመጥ ግን ምርጫ በመጣ ቁጥር የሶማሊያ ፖለቲካ ከራሷ ዜጎች አልፎ ለአካባቢው ሀገራ ሁሉ ስጋት ይፈጥራል።

ከአሁኑ ምርጫ ዋዜማም ላይ ሶማሊያ የገጠሟት ፈተናዎች ቁጥራቸው ተበራክቷል። የመጀመሪያው የምርጫው ጊዜ መራዘምና የምርጫ ሥርዓቱ ላይ ስምምነት አለመደረሱ ነው። በ2020 መካሄድ የነበረበት ምርጫ የፌደራሉ መንግሥት አካል ተደርገው የሚታሰቡት ጁባላንድ እና ፑንትላንድ ማራዘማቸው ነው። እነዚሁ ሁለት ግዛቶች የተዘጋጀውን የተሻሻለ የምርጫ ሥርዓት/ model/ ተስማምተው መፈረም አለመቻላቸው ነው።

እንደ ዘ አፍሪካን ሪፖርት ‹‹The African report›› ዘገባ የምርጫ ሥርዓት ማሻሻያው በ2016 ከተደረገው የምርጫ አካሄድ ብዙ የማይለይ ቢሆንም በታችኛው ምክር ቤት የሚኖሩ የፓርላማ አባላትን ቁጥር ከነበረው በ101 የሚያሳድግ ነው። በዚህ የምርጫ ሞዴል ሌሎቹ ሦስቱ የፌደራል

ግዛት አካሎችና የሶማሊያ ከተማ አስተዳደር ቢስማሙበትም የጁባላንድና ፑንትላንድ አለመስማማት ግን ቅሬታዎችን ፈጥሮ ቆይቷል። እነዚህ ሁለት ግዛቶች የወቅቱ ሶማሊያ ፕሬዚዳንት ሞሃመድ አብዱላሂ ሞሃመድ /ፋርማጆ/ አሁንም በሥልጣን ላይ ለመቆየት ሤራ የሠሩበት ሞዴል ነው በሚል ተቃውሞ አቅርበዋል።

ሌላው የማሻሻያ ነጥብ በእያንዳንዱ ግዛት ምርጫ የሚካሄድባቸው አካባቢዎች ቁጥር አራት የነበሩ ሲሆን አሁን ሁለት ብቻ እንዲሆን የሚያዝ ነው። በሶማሊያ ዜጎች በቀጥታ መሪዎቻቸውን የሚመርጡበት ቀጥተኛ ምርጫ ተካሂዶ ስለማያውቅና ምርጫው በልዑካን የሚፈጸም በመሆኑ የሚካሄድባቸውን ቦታዎች ማጥበቡን አስፈላጊ ሆኖ በማግኘቱ ፌደራል መንግሥቱ ማሻሻያ አድርጓል። ልዑካኑንም የሚመረጡት በሲቪክ ሶሳይቲ፣ በአገር ሽማግሌዎችና በክልሉ መንግሥት ትብብር ሆኗል። ሌላው ከዚሁ ጋር የተያያዘው ነገር ተገንጣይ የሆነው የሶማሊላንድ የሁለቱም ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ በሞቃዲሾ እንዲፈጸም ያዛል። ሴቶችም በሁለቱም ምክር ቤቶች ከ30 በመቶ ያላነሰ ድርሻ እንዲኖራቸው ያዛል። በላይኛው ምክር ቤት ያሉ ተወካዮች የሚመረጡት ደግሞ በየግዛቱ ባሉ ምክር ቤቶች ይሆናል። በዚህ ሞዴል ላይ የነበረው ውይይት መስከረም 17/2020 የተደረገ ሲሆን ሁለቱ ግዛቶች ግን ለመፈረም አልቻሉም። በዚህ ሁኔታ የምርጫወ ጊዜ መተላለፉና የፋርማጆ መንግሥት ሕጋዊነት የካቲት 8 /2021 መጠናቀቁ አለመስማማቱን አጡዞታል።

ያም ሆነ ይህ ግን በሶማሊያ ምርጫው እንዲካሄድ ግፊቱ አይሏል። ዓለም አቀፉ ማህበረሰብም የምርጫውን ሞዴል በመቃወም የምርጫውን ሂደት በማዘግየት ላይ በነበሩት በሁለቱ ግዛቶች ላይ ጫና ማድረጋቸውን ቀጥለዋል። በሶማሊያ የተመድ ልዩ መልእክተኛ ጀምስ ስዋን በምርጫው ጉዳይ የተወዛገቡ ኃይሎችን ለማስማማት ሞክረዋል። በሶማሊያ የአሜሪካ ኤምባሲም ከፊል ምርጫን፣ ትይዩ ሂደትን እና ግጭትን እንደማይቀበል አስታውቋል።

በዚህም መሠረት ሁለቱ ግዛት እያንዳንዳቸው ስምንት ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴዎችን መርጠው ስማቸውን ለተመድ ልዩ ልዑክ አስተላልፈዋል። ይህ የሶማሊያ መንግሥትን ፕሮቶኮል የጣሰ የሁለቱ ግዛቶች አካሄድ ያበሳጫቸው ፋርማጆ የሞቃዲሾን የላይኛው ምክር ቤት አባላት ቁጥር 13 እንዲሆን ተቀብለዋል። ይሄ መካረሩን አሳድጎታል።

## የምርጫው ፉክክር

የፕሬዚዳንቱ ተቃዋሚና የቀጣይ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ባለዕድል ሊሆኑ የሚፈልጉ አካላት ፋርማጆን የሶማሊያ ሀገረ መንግሥት ተጨባጭ አደጋ ናቸው ይላሉ። የምርጫ ሥርዓቱም ላይ ሤራ መፈጸማቸው የዚሁ ማሳያ ነው ይላሉ። በተለይ የጁባላንዱ ፕሬዚዳንት ሼክ አህመድ ሞሃመድ ኢስላን ማዶቤ እና የፑንትላንዱ ሴይድ አብዱላሂ ዴኒ የሶማሊያን ብሔርተኝነት አጥብቆ በመስበክ የፌደራላዊ ሥርዓቱን ለማጥፋት የመጡ ናቸው በማለት



ሞሃመድ አብዱላሂ ሞሃመድ /ፋርማጆ/

**የሶማሊያ ምርጫ በምሥራቅ አፍሪካ የኃይሎች አሰላለፍ ላይም ጫና አለው። ኬኒያ ከጁባላንድ ግዛት ጋር ያላት ቅርበት ጁባላንድ ለምታራምደው ፀረ ፋርማጆ እንቅስቃሴ ድጋፍ እንደ መስጠት ነው**

ይከሷቸዋል። ለዚህም እንደ ማሳያ የሚጠቅሱት ፋርማጆ በሌሎቹ ሦስት ግዛቶች ማለትም በደቡብ ምዕራብ ግዛት፣ በጋልሙደግና በሂርሻቤሌ ማን ፕሬዚዳንት መሆን እንዳለበት ምክረ ሐሳብ ሰጥተዋል የሚል ነው። ይህ የሚያሳየው ፋርማጆ በሶማሊያ ጠበቅ ያለ ማእከላዊነት በማምጣት ከመበተን ለመታደግ ፍላጎት ያላቸው ቢሆንም ፑንትላንድና ጁባላንድ ይሄንን ፍላጎታቸውን አጥብቀው በመቃወም ተሰልፈዋል።

ይህ የቀጣዩ የሶማሊያ ምርጫ ሐሳብ ምን እንደሆነ ከወዲሁ አመላካች ሆኗል። የሚታገሉት ኃይሎች የሶማሊያ ብሔርተኝነትና የማእከላዊ መንግሥቱን ጠንካራ የሆነ የፌደራል ሥርዓት በሚፈልጉ ኃይሎችና እስካሁን ባለው ሁኔታ የላላ ማእከላዊነት ያለው የፌደራል መንግሥት ሥርዓት እንዲቀጥል በሚፈልጉ ኃይሎች ናቸው። ይህ ጉዳይ ሞቃዲሾን ማእከል ያደረገው የፋርማጆ ሐሳብና ጁባላንድና ፑንትላንድን ማእከል ያረገው የፖለቲካ ኃይል በግልጽ የሚታገሉበት ይሆናል ማለት ነው። ይህ ጉዳይ በአንድ በኩል እስከ አሁን ሰፍኖ በነበረው የጎሳ/ክላን ፖለቲካ/ prevalent clan-oriented/ ማዳበርና ማስፋፋት የሚፈልጉት ኃይሎች በሶማሊያ ተሰልችተው ከሆነ የፋርማጆ ፖለቲካ ወደፊት ለመራመድ ዕድል ያገኛል ማለት ነው። በሌላ በኩል የሶማሊያ ዜጎች የሞቃዲሹ ዓይን ሳያያቸው የግዛታቸው አመራር ጣዕም ማርኳቸው ከሆነ ፋርማጆ አጣብቂኝ ውስጥ መግባታቸው አይቀርም።

ሌላው የፉክክር ጉዳይ የሞቃዲሹ ጉዳይ ነው። በሞቃዲሹ ሁለት ጎሳዎች በአብዛኛው የሚኖሩበት ከሦስት ሚሊዮን ያላነሰ ሕዝብ የሚይዝ ከተማ




ነው። በዚህ ከተማ ያለው የላይኛው ምክር ቤት የውክልና ድምጽ በ13 ያሳደጉት ፋርማጆ በአንድ በኩል ተቀባይነታቸውን የጨመረላቸው ቢሆንም ጁባላንድና ፑንትላንድን ብዙም ያስደሰተ አልነበረም ምክንያቱ ደግሞ በሞቃዴሹ በብዛት የሚኖሩትን ሁለቱን ጎሳዎች ብቻ መነሻ ያደረገ ሳይሆን ሌሎቹንም ከግምት ያስገባና ከተማዋ የሁሉም ሶማሊያውያን ነች በሚል መነሻ በከተማዋ ውስጥ በቁጥር አናሳ ሆነው የሚኖሩትን ጎሳዎችንም ዕድል የሚያሰፋ ሆኖ ነው። ስለዚህ የፎርማጆ እርምጃ አንድነትን ያጠናክራል በሚል የሚደግፉ ኃይሎች ጁባላንድና ፑንትላንድ ከፋፋይ ሐሳብ ይዘዋል በሚል እየሞገቷቸው ነው።

ፎርማጆ በምርጫው የሚጋፈጧቸው እጩዎች በብርቱ ሁኔታ ሊገዳደሩ የተዘጋጁ ናቸው። እነዚሁ ተፎካካሪዎች የአፍሪካን ቀንድ ሀገራት ግንኙነት እንደ ስትራቴጂ ተጠቅመው ለመመረጥ እየሠሩ ነው። የመጀመሪያው ተፎካካሪ ሃሰን አሊ ካሂሬ ሲሆኑ ከቱርክና ከኳታር ድጋፍ ያላቸው እጩ ናቸው። ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ሲሠሩ እውቅና ያገኙ ነበሩ። ሌላው ተገዳዳሪ ሃሰን ሼክ መሃመድ ናቸው የሶማሊያ ፕሬዚዳንት ሆነው እስከ 2017 የሠሩ ነበሩ። እስከ ሲያድባሬ ውድቀትም የሲቪል ሶሳይቲ መሪ ሆነው እውቅና ነበራቸው። በሶማሊያ በትምህርት ጉዳዮች ሰፊ ሥራ የመሥራት ፍላጎት ያላቸው እጩ ናቸው። ዳሂር ሞሃመድ ጊሌ ደግሞ ሌላው ተፎካካሪ ናቸው። ከሳውዲ መንግሥት ድጋፍ ያላቸው ናቸው። ቀድሞ የእስላማዊ ፍርድ ቤቶች የሚባለው እንቅስቃሴ አባል ነበሩ። እስላማዊ ትምህርትን በማስፋት የሚሠራውን የሞቃዴሾ ሬዴዮ የመሠረቱ ናቸው። በ2019 የማስታወቂያ ሚኒስትር ሆነው ቢሾሙም ከፋርማጆ ጋር ባለመስማማታቸው ሥልጣናቸውን ለቀዋል። ሌላው ተፎካካሪ ሸሪፍ ሼክ አህመድ ናቸው። ቀድሞ የእስላማዊ ፍርድ ቤቶች የሥራ አስፈጻሚ ነበሩ። ከተባበሩት አረብ ኤምሬቶችና ከሳውዲ አረቢያ ጋር ጥሩ ግንኙነት ነበራቸው። ፕሬዚዳንት ሆነውም እስከ 2012 ሠርተዋል። በወቅቱ አልሸባብን በመደምሰስ ሥራ የቀናቸው ሰው ነበሩ። አብዴራህማ አብዴሸኩር ዋርሳሜ የሚባሉት እጩ ደግሞ ሌላው ተፈታታኝ ናቸው። የዋዳጂር ፓርቲ መሪ ናቸው። የፓርላማ አባል ሆነውም ከ2009 እስከ 2010 ቆይተዋል። በፕሬዚዳንት ሸሪፍ ሼክ አህመድ አማካኝነት የውጪ ግንኙነት ሚኒስትር ሆነው ተሾመው ነበር። ከተባባሩት አረብ ኤምሬትስ ጋር ጥሩ ግንኙነት አላቸው።

## ኬኒያና የሶማሊያ ምርጫ

የሶማሊያ ምርጫ በምሥራቅ አፍሪካ የኃይሎች አሰላለፍ ላይም ጫና አለው። ኬኒያ ከጁባላንድ ግዛት ጋር ያላት ቅርበት ጁባላንድ ለምታራምደው ፀረ ፋርማጆ እንቅስቃሴ ድጋፍ እንደ መስጠት ነው። ይህ ደግሞ በግልጽ የታየ ክስተት ነው።

ሶማሊያ ጎረቤቷን ኬኒያን በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባትና ሉዓላዊነትን በመዳፈር ጉዳይ ትከሳለች። ከዚያም ተሻግራ በህዳር 30/2020 ላይ በሶማሊያ የኬኒያን አምባሳደር ከሞቃዴሾ አባራለች። ይህ የሆነው የኬኒያው ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬኒያታ የተገንጣዩን የሶማሊ ግዛት የሶማሊላንድ ፕሬዚዳንትን ሙሳ ቢ አብዴን ከተገናኙ በኋላ ነው። ተ.መ.ድ እውቅና ካልሰጠው የሶማሊላንድ መሪ ጋር ኬኒያ ግንኙነት ማድረጓ እና በሃርጌሳ ቆኒሲላ ጽሕፈት ቤት እንደምትከፍትና ወደዚያው በረራም እንደምትጀምር ማስታወቋን ተከትሎ ነበር። በተጨማሪም ኬኒያ የፑንትላንድ ግዛት በምርጫው እንዳይሳተፍ ግፊት አድርጋለች የሚል ክስም ይቀርብባታል።

በጥር ወር 2020 ላይም የሶማሊያ ፌደራል ወታደሮች ከጁባላንድ ኃይሎች ጋር ተጋጭተው 11 ሰላማዊ ዜጎች ቡላ ሐዋ በተባለ ቦታ ሲገደሉ ሶማሊያ የከሰሰችው ድርጊቱን የፈጸሙት የኬኒያ ኃይሎችና ሸማቂ አማጽያን ናቸው በማለት ነበር። ይህ በሶማሊያ እና በኬኒያ መካከል ያለው ውዝግብ እየተካረረ ከሄደ ምርጫውን ተከትሎ ግጭቶች ሊቀሰቀሱ ይችላሉ የሚል ስጋት አስከትሏል። ከዚያም አልፎ ከፎርማጆ ጎን ያሉ የአካባቢውን ሀገራት እና ከተገንጣይ የሶማሊያ ኃይሎች ጎን ያሉ የቀጠናውን ሀገራት መፋጠጥ ውስጥ ሊከት ይችላል።

የፌደራል ኃይሎች አብዴራሺድ ጃናን በተባለው የጌዶ አካባቢ ገዢ መሪነት ተሰልፈው ወደ ግጭት የገቡት ከኬኒያ ግዛት ተንደርድረው እንደሆነ የሶማሊያ መንግሥት ይገልጻል። በዚህም ምክንያት የተቀሰቀሰው የጌዶ ግጭት የኬኒያ የሶማሊያን ግጭት አባብሷል። የኬኒያ ኃይሎችና የጌዶ ግዛት መሪዎች ግን ፎርማጆ የጌዶን ቀውስ የፈለጉት የሶማሊያን ብሔርተኝነት ለማጠናከር ፍላጎት ስላላቸውና ለዚያም እንዴረዳ ኬኒያን በሉዓላዊነት መዳፈር ደጋግመው መክሰስ ይፈልጋሉ ይላሉ።

በአጠቃላይ ሲታይም ሶማሊያ በምርጫው ምክንያት የገባችበት የውስጥ ቀውስ ከኬኒያ ጋር ከገባችበት እሰጣ ገባ ጋር ተዳምሮ ጭንቁ ከፍ ያለ ሆኗል። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ የተባበሩት መንግሥታት የሰላም አስከባሪ UN Assistance Mission in Somalia (UNSOM) እና የአፍሪካ ሰላም አስከባሪ ኃይሎችም AU Mission in Somalia (AMISOM), ከሶማሊያ የሚወጡበት ሁኔታ መፈጠሩ ነገሩን ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብና በተለይም ለጎረቤት ሀገሮች ከፍተኛ ስጋት መፍጠሩን በቀላሉ ማስተዋል ይቻላል።



# ማስታገሻ እንጂ ፈውስ ያልተገኘለት ፓርኪንሰን

ስሜነህ ደስታ

ወይዘሮ ክብራ ከበደ ይባላሉ። የተወለዱት በቀድሞው ትግራይ ክፍለ ሀገር ጉሎማከዳ ወረዳ አዴጠቀና በምትባል መንደር ነው። አሥራ ሁለተኛ ክፍል በ1971 ዓ.ም. ጨርሰው ደብረዘይት እርሻ ኮሌጅ በመግባት በአዝርዕት ሳይንስ በዴፕሎማ የማዕረግ ተመራቂ በመሆን አጠናቀዋል። ከምረቃ በኋላ በግብርና ሚኒስቴር ተቀጥረው በወቅቱ ጅማ ክፍለ ሀገር በእርሻ ባለሙያነት ሠርተዋል። ከፍተኛ ትምህርት ለመማር ባላቸው ፍላጎት በዓለማያ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዴግሪያቸውን በአዝርዕት ሳይንስ አግኝተዋል። ከዛም የልማት ፕሮጀክቶች ጥናት ባለስልጣን መሥሪያ ቤት ከሠሩ በኋላ ኖርዌይ በመሄድ በማኔጅመንት ኦፍ ናቹራል ሪሶርስ የማስተር ዴግሪያቸውን አግኝተዋል። ከኖርዌይ በመመለስ በማኅበረ ረድኤት ትግራይ ተቀጥረው አምስት ዓመት ካገለገሉ በኋላ በግላቸው የአማካሪነት ሥራ ጀምረው አንድ ዓመት እንኳን ሳይሰሩ በፓርኪንሰን ህመም ተጠቁ።

የፓርኪንሰን ህመም ተጠቂ ሲሆኑ የሰላሳ ሁለት ዓመት ወጣት፣ ባለትዳር እና የሁለት ልጆች እናት ነበሩ። ስለህመሙ አጀማመር ሁኔታ ሲናገሩ ‹‹በመጀመሪያ የማስታውሰው የህመም ምልክት አንድ እግሬ አልራመድ ብሎ ያስቸግረኝ እንደነበረ ነው። እግሬ በመርገጥ ፋንታ ለመራመድ ስፈልግ ጣቶቼ በተለይም አውራ ጣቴ ላይ እየተቀሰረ ለመራመድ ያስቸግረኝ ነበር። ይህ ቢሆንም በእግር የምጓዝበት ጊዜ አጭር በመሆኑና መኪናም እነዳ ስለነበር መታመሜ ሳይገባኝ ብዙ ጊዜ ቆየሁ። የህመም ምልክት ከተሰማኝ ከ6 ወር በኋላ የእግር ጉዞ የማደርግበት አጋጣሚ ተፈጠረና ለመራመድ ስሞክር እግሬ በትክክል አልነሳ በማለት ለመራመድ በጣም ተቸገርኩኝ። ብዙ ቦታ እያረፍኩኝ ደርሼ ተመለስኩኝ። በዚያን ጊዜ የተሰማኝ ስቃይ ከፍተኛ ስለነበር ችግር ውስጥ እንደሆንኩኝ ተረዳሁ። በተጨማሪ አንድ እግሬ ላይ ብቻ ይሰማኝ የነበረው ህመም ወደ ሁለተኛው እግሬ እየተላለፈ መሆኑን ተደራሁ። የእግር ጣቶቼ ብቻ ሳይሆኑ ከጉልበቴ በታች ያለው የእግር ጡንቻዬ በጣም ያመኝ ነበር›› በማለት ያስታውሳሉ።

በ1990 ዓ.ም. መታመማቸውን እንዳወቁ በሀገር ውስጥ የተለያዩ ሐኪሞች ዘንድ ቢሄዱም ህመማቸው ይህ ነው የሚላቸው አላገኙም። ህመሙ መሻሻል ሳያሳይ እየተባባሰበት ሄደ። የተለያዩ ፀበል

**ፓርኪንሰን በሽታ ጠቅላላ እንቅስቃሴን የሚያውክ፣ አንድ ጊዜ ከጀመረ እየባሰበት የሚሄድ እና በአሁኑ ጊዜ በህክምና የማይድን የአንጎል ነርቭ ህመም ነው**

ቦታዎች ቢሄዱም ለውጥ የለም። ባህላዊ መድኃኒት አዋቂዎች የሰጧቸውን ቢወስዱም መሻሻል አላዩም። ሐኪሞች ምን እንደሆኑ ባይነግሯቸውም ሰዎች አስፈሪና አስደንጋጭ አስተያየት ሲሰነዝሩ ይጨነቁ እንደነበር ያስታውሳሉ። ከመሳቀቃቸው የተነሳ ሰው ባያያቸው ይመርጡ ነበር። በጊዜው በሽታው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታወቅ ባለመሆኑ በውጭ ሀገር በተደረገ ህክምና ነበር የበሽታው ምንነት የታወቀላቸው። አሜሪካን ሀገር በተደረገ ህክምና በሽታው ታውቆላቸው ኪኒን ሲውጡ የነበረውን ሁኔታ ሲያስረዱ « በዶክተሩ ትዕዛዝ ‘ሴኒሜት’ የሚባል መድኃኒት አንድ ኪኒን ተሰጥቶኝ ከዋጥኩ ከግማሽ ሰዓት በኋላ ሰውነቴ ያለ አመሉ መፍታታት ጀመረ። ብድግ ስል ቀለል አለኝ፤ ተነስቼ መሄድ ጀመርኩኝ » በማለት ይገልጻሉ።

በሽታቸውን አውቀው ህክምና መከታተል ከጀመሩ በኋላ እሳቸው ያገኙትን እፎይታ የበሽታው ተጠቂ ሆነው ህክምናውን ላላገኙ ሌሎች ሰዎች ለማድረስ ፈለጉ። “ፓርኪንሰን ፔሸንትስ ሰፖርት ኦርጋናዜሽን - ኢትዮጵያ” የሚል ድርጅት በመመስረት የመጀመሪያዋ ዳይሬክተር በመሆን ህሙማን ስለፓርኪንሰን በሽታ ግንዛቤ እንዲያዳብሩ፣ መድኃኒት በመጠቀምና የሰውነት እንቅስቃሴ በማድረግ የተሻለ ህይወት ለመኖር እንዲጥሩ አግዘዋል። በዚህም ህሙማን ቤት ተዘግቶባቸው ይኖሩ ከነበረበት ሁኔታ ወጥተው ህመማቸውን አውቀው ህክምና አግኝተዋል፤ ከመሰሎቻቸው ጋር ለመወያየትና የሰውነት እንቅስቃሴ ለማድረግ ችለዋል፤ የመንቀሳቀሻ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው መንቀሳቀሻ ተበርክቶላቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ ህሙማኑ በድርጅቱ በኩል ለመድኃኒት መግዣና ለህይወት ለሚያስፈልጓቸው ሌሎች አገልግሎቶች (አልባሳት፣ ምግብ፣ ወዘተ. ) ድጋፍ አግኝተዋል። ቤተሰቦቻቸውም ስለህመሙ ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጎ እንዴት እንደሚያስታሙሟቸው ስልጠና አግኝተውበታል። አሥር ከማይሞሉ የድርጅቱ ህሙማን አባላት ቁጥር ተነስቶ አሁን በድርጅቱ የሚረዱ ታማሚ አባላት 742 ደርሷል፤ 542 ወንዶች ሲሆኑ 200 ሴቶች ናቸው። ለ60 ታማሚዎች የመድኃኒት ድጋፍ ይደረግላቸው የነበረውን በማሳደግ አሁን 260 ታማሚዎች የመድኃኒት ድጋፍ ይደረግላቸዋል። አልጋ ላይ ለዋሉ ለ70 ታማሚዎች በሰለጠነ ነርስ ቤት ለቤት እገዛና እንክብካቤ እየተደረገላቸው ይገኛል። የአካል ድጋፍ የሚሆን 30 ምርኩዝ፣ 10 ወከር (ከፍ ብለው ቆመው የሚይዙት መደገፊያ) እንዲሁም 5 መንቀሳቀሻ ዊልቸር ለአባላት ተሰጥቷቸዋል። ሽንት ቤት ለመጠቀም ለሚቸገሩ 37 አባላት ምቹ የሆነ ሽንት ቤት መጠቀሚያ በድርጅቱ ተሰርቶላቸዋል።

ወይዘሮ ክብራ ድርጅቱን በመመስረት ለአምስት ዓመት በዳይሬክተርነት ከመምራታቸው ባሻገር በ2010 ዓ.ም. ስለፓርኪንሰን ግንዛቤ የሚሰጡ «በፓርኪንሰን ላይ 100 ጥያቄዎችና መልሶች» እና «የፓርኪንሰን ፔሸንትስ ሰፖርት ኦርጋናይዜሽን - ኢትዮጵያ አመሠራረትና ዕድገት» የሚሉ ሁለት መጽሐፎች አሳትመዋል። ለዚህ ሁሉ መልካም ተግባራቸው የባለቤታቸውና የልጆቻቸው ድጋፍና እገዛ ከፍተኛ እንደሆነ በአጽንኦት ይናገራሉ። የህክምና ባለሙያዎችና ጎረቤቶቻቸው የሚሰጧቸውን የሞራል ድጋፍም በምስጋና ያነሳሉ። አሁን ስላሉበት ሁኔታ ሲናገሩ « ከፍተኛው ደረጃ ላይ ስለደረስኩኝ በየአራት ሰዓት ልዩነት ኪኒን እወስዳለሁ፣ የአካል እንቅስቃሴም በቤት ውስጥ አደርጋለሁ። የአካል እንቅስቃሴ ለማድረግ በድርጅቱ በኩል በጋራ ማድረጉ ጠቀሜታ ነበረው፤ በኮቪድ 19 በሽታ ምክንያት አሁን እየተደረገ አይደለም። ከቦታ ወደ ቦታ ለመንቀሳቀስ የአካል ድጋፍ እጠቀማለሁ ወይም በሰው ድጋፍ እዘዋወራለሁ» ብለዋል። ወይዘሮ ክብራ አሁን ድርጅቱን በማማከርና በትምህርታዊ ሥራ ዙሪያ እንዲሁም በተጠየቁት ሌሎች ተግባራት በመሳተፍ እገዛ እያደረጉ ይገኛሉ።


ፓርኪንሰን በሽታ ጠቅላላ እንቅስቃሴን የሚያውክ፣ አንድ ጊዜ ከጀመረ እየባሰበት የሚሄድ እና በአሁኑ ጊዜ በህክምና የማይድን የአንጎል ነርቭ ህመም ነው። እንግሊዛዊው ሀኪም ፓርኪንሰን በ1817 ዓ.ም በሽታውን በስድስት ሰዎች ላይ ካገኘ ከ40 ዓመት በኋላ በሽታው በስሙ ፓርኪንሰን ተብሎ ተሰይሟል። በሀገራችንም ፓርኪንሰን በሚል ስያሜ እየተጠራ ይገኛል። የፓርኪንሰን ሕመምተኞች ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ላይ በአብዛኛው ስለማይሳተፉ ለኢኮኖሚያዊ ጉዳቶች ይዳረጋሉ። በኢኮኖሚ ተጎጂ በመሆናቸው ለማስታገሻ የሚሆነውን መድኃኒት እና የዕለት ምግባቸውን ለማግኘት በጣም ይቸገራሉ። በሽታው በህብረተሰቡ ዘንድ በተገቢው ሁኔታ አለመታወቁ ታማሚዎችን ለመገለል ስለሚዳርጋቸው ማህበራዊ ተቀባይነት ማጣታቸው ለስነ ልቦና ችግር ይዳርጋቸዋል፤ ከኢኮኖሚ ጉዳቱ ባልተናነሰም ይጎዳቸዋል።

በፓርኪንሰን በሽታ ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል ሊያዝ ይችላል። የበለጠ አጋላጭ መንስኤዎች ተብለው የሚጠቀሱት የዕድሜ መግፋት በተለይ ከ60 ዓመት በላይ መሆን፣ ለአረም ማጥፊያ ኬሚካል መጋለጥ፣ ለተባይ ማጥፊያ ኬሚካል መጋለጥ፣ በዘረመል አልፎ አልፎ የሚተላለፍ መሆኑ እና ጭንቅላት ላይ ጉዳት መድረስና በብዛት ጭንቅላት መመታት ናቸው።

ዝግመታዊ በሆነ ሂደት አዕምሮ ውስጥ የሚገኝ “ባዛል ጋንግሊያ” የሚባል ክፍል ላይ የሚኖሩ የነርቭ ሴሎች አሉ። እነዚህ ሴሎች “ዶፓሚን” የሚባል ንጥረ ነገር ያመነጫሉ። እነዚህ ሴሎች ሲሞቱ ደግሞ ንጥረ ነገሩ መመረት ያቆማል። የዶፓሚን ማነስ ወይም አለመኖር ለፓርኪንሰን በሽታ ያጋልጣል። ንጥረ ነገሩ ዘርፈ ብዙ ጥቅም አለው። ዋነኛው ጥቅሙ ግን በሞተርነት የጡንቻዎችን እንቅስቃሴ ማቀላጠፍና ማነቃቃት ነው። “ባዛል ጋንግሊያ” የሚባለው የአእምሮ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ዶፓሚን አምራች ሴሎች ምክንያቱ በውል ባልታወቀ ሁኔታ ቀስ በቀስ ይሞታሉ። ከ80 በመቶ በላይ ሲሞቱ ደግሞ የንጥረ ነገሩ እጥረት ይከሰትና የበሽታው ዋና ዋና ምልክቶች መታየት ይጀምራሉ።

የስኳር ህመም መኖሩን ለማረጋገጥ ደምን መለካት ይቻላል። የፓርኪንሰን ህመምን ግን ለመለየት በልኬት ማወቅ የሚቻልበት ሂደት የለም። የፓርኪንሰን ህመምን ለማወቅ ያለው አማራጭ ምልክቶቹን ጠንቅቆ መለየት ብቻ ይሆናል። የፓርኪንሰን ህመም ምልክቶች ተብለው ከሚጠቀሱት ውስጥ የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው።

- በጣም የተወላገደ አቋም፡- በሚቆምበት ጊዜ እንደ ድሮ ቀጥ ብለው አለመቆም፣ ወደፊት ማጎንበስ፣ ወደ አንድ በኩል ዘንበል ማለት እንዲሁም እጅና እግር አስተካክሎ ቀጥ ብሎ ለመቆም መቸገር
- መንቀጥቀጥ፡- እረፍት ላይ እያሉ ወይም በመዝናናት ላይ በሚሆኑበት ጊዜ መንቀጥቀጥ (የእግር፣ የእጅ፣ የአገጭና የምላስ መንቀጥቀጥ)
- የጡንቻ መገታተር
- ለመንቀሳቀስ ወይም ለመራመድ መቸገር
- ሰውነት ጨምድዶ መያዝ
- ደስተኛ ያልሆነ ፊት (ፈዘዝ ያለ ወይም የተከፋ የፊት ገፅታ)
- የእጅ ጽሑፍ መጻፍ መቸገር
- የምራቅ መዋጥ ችግር፣ ድምጽ ለማውጣት መቸገር ወይም ንግግር ለማድረግ መክበድ




የወይዘሮ ክብራ ሁለት መጽሐፍቶች

**በሽታው ከአንዱ ወደ ሌላው የሚተላለፍ ባለመሆኑ ስጋትም ሆነ የተለየ ጥንቃቄ የሚያሻው አይሆንም**

- የስነልቦናና የአእምሮ ችግር
- እንቅልፍ ማጣት
- ብዥ ማለት ወይም ራስን ስቶ መውደቅ
- በአብዛኞቹ ህመምተኞች ላይ የመርሳት ችግር መታየት ናቸው።

የፓርኪንሰን ህመም የያዘው ሰው ብዙውን ጊዜ መንቀጥቀጥ ይስተዋልበታል። ሰውነቱን ጨምድዶ የመያዝ ስሜትና ሚዛኑን የመሳት ሁኔታም ይኖረዋል። አንዳንድ ጊዜ የፓርኪንሰን ተጠቂው በመዝናናት አልያም በእረፍት ላይ በሚሆንበት ወቅት እጆቹና እግሮቹ ብቻ ተለይተው ሊንቀጠቀጡ ይችላሉ። መንቀጥቀጡ ደግሞ በአንድ ወይም በሁለት እጆቹ ላይ ሊሆን ይችላል። እጆቹ ቡና ወይም ሌላ መሰል ነገሮችን ለመቀበል በሚዘጋጁበት ጊዜ ደግሞ በድንገት መንቀጥቀጣቸውን ሊያቆሙ ይችላሉ። የሰውነቱ መገታተር የሚጀምረውም መንቀጥቀጥ በሚታይበት ጎን በኩል ያለው የእጅና እግር ጡንቻዎቹ ላይ ነው። ይህ ስሜት ብዙውን ጊዜ ሪህ ህመም ሊመሳሰል ይችላል። የመገጣጠሚያ ጡንቻዎች ህመም መኖሩ ከሪህ ጋር ቢያመሳስለውም ፓርኪንሰንን ከሪህ ህመም ለየት ከሚያደርገው አንዱ የዕብጠት ምልክት አለመኖሩ ነው።

ፓርኪንሰን አብዛኛውን ጊዜ የሚያጠቃው ከ60 ዓመት ዕድሜ በላይ የሆናቸውን ቢሆንም ከአሥር እስከ አሥራ አምስት በመቶ የሚሆኑት በወጣትነት አፍላ ጊዜያቸው ( በ20 እና በ30 ዓመት ዕድሜ) እንዲሁም በጎልማሳነት የዕድሜ ጊዜያት በሕመሙ እንደሚያዙ መረጃዎች ያመለክታሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ተጠቂዎች ቁጥር በውል እንደማይታወቅ የህክምና ባለሙያዎች ያስረዳሉ። መንግሥት ተነሳሽነቱን በመውሰድ የታማሚዎችን ቁጥር በጥናት ላይ ተመስርቶ በማወቅ ለህመምተኞቹ ተገቢውን ድጋፍና እርዳታ እንዲያደርግ ባለሙያዎች ያሳስባሉ።

ማስታገሻ እንጂ ፈውስ ያልተገኘለት ይህ በሽታ ከሴቶች በበለጠ ወንዶችን የሚያጠቃ ሲሆን ከተማ ከሚኖሩ ገጠር የሚኖሩት ላይ ይበረታል። በሀገራችን ተላላፊ ያልሆኑት በሽታዎች የሚባሉት እንደ ስኳር፣ ኩላሊት፣ ደም ግፊትና የመሳሰሉት ውስጥ ፓርኪንሰን ሊመደብ ይችላል። በሽታውን የሚያጠፋ መድኃኒት የለም፤ የሚያስታግስ እንጂ። ለምሳሌ የስኳር ታማሚዎች “ኢንሱሊን” በተደጋጋሚ እንደሚሰጣቸው ሁሉ የፓርኪንሰን ታማሚዎችም መድኃኒቱን በሐኪም ትዕዛዝ ልኬቱ እየተነገራቸው ዕድሜ ልክ በቋሚነት በመውሰድ ህመማቸውን በማስታገስ ረጅም ጊዜ ይኖራሉ። ከህመሙ ባህሪ የተነሳ ታማሚው ከጊዜ ወደ ጊዜ የህመሙ ሁኔታ እየባሰበትና እየከፋበት የሚሄድ ስለሆነ የሚወስደውም መድኃኒት መጠን እየጨመረ ስለሚሄድ አወሳሰዱ በሐኪም ትዕዛዝ መሰረት መሆን ይገባዋል።

ፓርኪንሰን በራሱ ገዳይ አይደለም፤ ይህ ይሁን እንጂ በሽታው ለሌሎች ጉዳቶች ያጋልጣል። ለምሳሌ ለመሰበር አደጋ ያጋልጣል። ሚዛን መጠበቅ ስለማይችሉ ይወድቃሉ፤ ያን ጊዜ ስብራት ይመጣል። የፓርኪንሰን ታማሚዎች በአብዛኛው ለሳንባ ምች በተደጋጋሚ ይጋለጣሉ። የዚህ ዋነኛ ምክንያቱ ሳንባን እንዲንቀሳቀስ የሚያደርጉ ጡንቻዎችና የደረት ጡንቻዎች እንቅስቃሴ ለማድረግ በሚታወኩ ጊዜ መሆኑን ባለሙያዎች ያስረዳሉ።

ፓርኪንሰን በሽታ በላቦራቶሪ ወይም በኤክስሬይ የህክምና መመርመሪያ መሳሪያ አይታወቅም። ሐኪሞች በሽታውን የሚያውቁት በእንቅስቃሴ ችግሮች ዙሪያ ኒውሮሎጂስቶችና የፓርኪንሰን ህሙማን በሚነግሯቸው የህመም ምልክቶች እንዲሁም በታዘቡት እንቅስቃሴ ነው። ህክምናውም ኃይሉ አነስ ባለ መድኃኒት በመጀመር መስራቱ ሲቀንስ ጨመር እየተደረገ መድኃኒት መውሰድ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ህሙማን በፊዚዮቴራፒስት(በመታሸት ወይም የአካል ብቃት እንቅስቃሴ የሚያሰሯቸው)፣ በንግግር ቴራፒስት (የንግግር ክህሎት የሚያስተካክሉላቸው፣መዋጥም ሊሆን ይችላል)፣ በኦኩፔሽናል ቴራፔስት(የቀን ኑሮአቸውን እንዴት ማካሄድ እንዳለባቸው በሚያለማምዷቸው) ባለሙያዎች በመረዳት እንቅስቃሴያቸውን ማሻሻል ይችላሉ።

ብዙውን ጊዜ ህመሙ ካለባቸው ሰዎች ጋር ቅርበት ያላቸው ሰዎች የፓርኪንሰን በሽታ ወደ እነሱ የሚተላለፍ መስሎ ሊሰማቸው ይችላል። ይሁን እንጂ በሽታው ከአንዱ ወደ ሌላው የሚተላለፍ ባለመሆኑ ስጋትም ሆነ የተለየ ጥንቃቄ የሚያሻው አይሆንም።

ዶክተር ያሬድ ዘነበ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የነርቭ በሽታ ስፔሻሊስት ሐኪምና በረዳት ፕሮፌሰር ማዕረግ መምህር ናቸው። የፓርኪንሰን ህመም በአንድ ወቅት ጀምሮ እየባሰ የሚሄድ ማስታገሻ እንጂ በአሁኑ ወቅት ማዳን የሚያስችል ህክምና የሌለው የዕድሜ ልክ በሽታ እንደሆነ ይገልጻሉ። በዋናነት የሚጠቀስ መንስኤ እስከ አሁን እንዳልተገኘለትና ከላይ የቀረቡት አጋላጭ መንስኤዎችና ምልክቶች እሳቸውም ይጋሯቸዋል። በሽታው ሲጀምር አካባቢ ከሌሎች በሽታዎች ጋር የመመሳሰል ሁኔታ ይኖራል፤ ፓርኪንሰን መሆኑ ታውቆ ህክምና እንዲያገኙ የሚያስገድደው የሰውነት ማንቀጥቀጥ፣ አካል አልታዘዝ ማለት፣ የአካል ሚዛን መጠበቅ መቸገርና ለመንቀሳቀስ መቸገር ደረጃ ሲደርሱ መሆኑን ያስረዳሉ።

ስለፓርኪንሰን ህመም ደረጃ ሲናገሩ « ጠቅለል አድርገን ስናየው በሁለት እንከፍለዋለን። አንደኛው ደረጃ ህመሙ ሲጀምር አካባቢ ያለውን የታማሚውን እንቅስቃሴ የማይገታ አይነት ነው። ለምሳሌ አንድ እጅን ወይም አንድ እግርን ለይቶ መንቀጥቀጥ፣ ወይም ፈጠን ብሎ አለመሄድ፣ የፊት ገጽታዎችን ለማውጣት መቸገር፣ ሰውነት ቀልጠፍ ብሎ አለመንቀሳቀስ እና የመገተር ሁኔታዎች ናቸው። ሁለተኛው ደረጃ ቀደም ብለው የተጠቀሱት የህመም ምልክቶች ባህሪ እየተባባሰና እየጨመረ በመጣ ቁጥር ከአካል ህመም በተጨማሪ እንቅስቃሴን ይገታል፤ የስነልቦና፣ የማስታወስ ችግርና የባህሪ ለውጥ ያመጣል። እዚህ ደረጃ ላይ ሲደረስ በመድኃኒት መረዳት ይቀንስና አብዛኞቹን የአልጋ ቁራኛ ያደርጋል » ብለዋል።


በእኛ ሀገር የህክምና አሰጣጡ ህመሙን የሚያስታግስ በኪኒን የሚሰጥ መድኃኒት ነው ያለው። በአደጉት ሀገሮች ግን በመርፌ የሚሰጡ ህክምናዎች አሉ። ከዚህ በተጨማሪ አንጎልን ኦፕራሲዮን በማድረግ ማከም የሚቻልበት አማራጮችም እንዳሉ ዶክተር ያሬድ ይናገራሉ። አዳዴስ በሽታውን ለመፈወስ የሚያስችሉ ህክምናዎች በምርምር ሂደት ላይ ስላሉ ከዓመታት በኋላ ሲደርሱ ከበሽታው የመፈወስ ተስፋም እንዳለ ይገልጻሉ።

ዶክተር ያሬድ ከፓርኪንሰን በሽታ ጋር በተያያዘ ያላቸውን አስተያየት ሲሰጡ፤ « ታማሚዎች እቤት ውስጥ ዝም ብሎ ከመቀመጥ ወይም ሌላ ቦታ ከመሄድ ይልቅ ዘመናዊ ህክምና ያለው መሆኑን አውቀው ወደ ህክምና ተቋም ለመታከም መሄድ ይገባቸዋል። ህክምና እየተከታተሉ ያሉ ታካሚዎች ሁሉ ህመሙ እንዳይባባስባቸው የአካል እንቅስቃሴ ማድረጋቸው በእጅጉ እንደሚጠቅማቸው አውቀው ዕለት በዕለት መተገበር ይገባቸዋል። አስታማሚዎችም ጫናው እነሱ ላይ ስለሚበረታ ህመሙን ማወቅ፣ ህመምተኞቹ የአካላና የስነልቦና ችግር ሊፈጠርባቸው እንደሚችል በመረዳት ታካሚው የሚያስፈልገውን በማቅረብ ሳይሰለቹ እያገዙ መቀጠል ይገባቸዋል። ህብረተሰቡም ለህመሙ ያለውን የተዛባ አመለካከት በዕውቀት ላይ ተመስርቶ አስተካክሎ ለስነልቦና ችግር እንዳይጋለጡ ከማግለል ይልቅ ማገዝና ማበረታታት ይጠበቅባቸዋል » በማለት ሙያዊ ምክር ሰጥተዋል።

የፓርኪንሰን ሕመም ጠቅላላ እንቅስቃሴንና ንግግርን የሚያውክ፣ በጊዜ ሂደትም አስከፊነቱ እየጨመረ የሚሄድ፣ ከአእምሮ ጋር በተያያዘ የሚከሰት የነርቭ ችግር ነው። የፓርኪንሰን በሽታ ታማሚዎች ላይ ከሚያሳድረው የህመም ስሜት በተጨማሪ ዕድሜያቸውን ሙሉ መሥራት አለመቻላቸውና ምርታማ አለመሆናቸው የሚያሳድርባቸው የኢኮኖሚ እንዲሁም የስነልቦና ጫና ከፍተኛ ነው። ስለሆነም ኅብረተሰቡ ፓርኪንሰን እንደማንኛውም ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች አንዱ መሆኑን በመረዳት ታማሚዎቹን ማበረታታትና መደገፍ ይኖርበታል። የሚመለከተው የመንግሥት አካል ደግሞ በዘርፉ የሰለጠኑ በቂ ባለሙያዎችን ማፍራት፣ ለታማሚዎች የህክምና እንዲሁም የመድኃኒት ድጋፍና ክትትል የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት ላይ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራ ይገባል የሚለው መልዕክታችን ነው።

# ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለምን ጠላት አበዛብን?

**ስሜነህ ደስታ**



ዓባይ ወይም ናይል ወንዝ 6 ሺህ 700 ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት የዓለም ረጅሙን ጉዞ ያደርጋል:: በዚህ ጉዞው ውስጥም በቀጥታ ወሰናቸውን አቋርጦ የሚያልፍባቸውም ሆኑ ወሰናቸውን ሣይነካ ግብር የሚከፍሉለት አነስተኛ ወንዞች ያላቸው 11 አገራት አሉት:: የሚገርመው ሁሉም አገራት ዝናውን እና ጉልበተኛነቱን ከመመሥከር ያለፈ ተጠቅመውበታል አይባልም:: በግዛቱ ውስጥ ከሚገኙት መካከል የግብጽን ያህል አቅሙን አሟጦ የተጠቀመበት አገር አይገኝም:: ከእሷ በመቀጠል ሱዳን በናይል ወንዝ ላይ የተሻለ ተጠቃሚ ናት:: ከዚያ ባለፈ 85 በመቶ የሚሆነውን የውሃ መጠን የሚመግበውን ዓባይን ከአብራኳ የምትወልደው ኢትዮጵያ በወንዙ ላይ ምንም አልተጠቀመችበትም:: ለታችኛው የተፋሰሱ አገራት ለእርሻ ሥራ የሚሆነው ለም አፈርም የሚሄደው በአብዛኛው ከዓባይ ወንዝ ነው:: ናይል እንዲያው ሥሙ ብቻ እንጂ በተለይ ለላይኛው የተፋሰሱ አባል አገራት ምንም ፋይዳ አልሠጠም:: በናይል ላይ የተገነቡት የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ እንኳ ከአንድ እጅ ጣቶች ቁጥር አይበልጡም:: የላይኛው የተፋሰሱ አገራት አቅም ማነስ እና የታችኞቹ የተፋሰሱ አገራት የላይኞቹን አንድም የልማት እንቅስቃሴ እንዳያከናውኑበት ተፅዕኖ ሲያደርጉ መቆየታቸው ከናይል ጋር የማይመጣጠን ተግባር እንዲያከናውኑ አድርጐ ቆይቷል::

ወደ ምድረ ግብጽ ቁልቁል ከሚፈሰው የናይል ወራጅ ውሃ 85 በመቶው ከኢትዮጵያ ነው። ከውጭ ወደ ኢትዮጵያ ሽቅብ ከሚፈሱት ክፋቶች 85 በመቶው ከግብጽ ሳይሆኑ አይቀሩም። ብዙዎቹ ውጭ-ወለድ የኢትዮጵያ ችግሮች ምንጫቸው ቢጠና ግብጽ ከመሆን አይዘልም። ለምሳሌ የአፍሪካ ቀንድ ለብዙ ዘመናት እርጋታና ሰላም የራቀው ቀጣና ሆኖ መዝለቁ። የኢትዮጵያ በዓላትና የማይሰራባቸው ቀናት መብዛታቸው ራሱ የግብጽ ተንኮል ነው በማለት አስረጅ ጠቅሰው የሚከራከሩ ምሁራን አሉ። በግብጾችም ቢሆን አይፈረድም። እርግጥ ዘላቂ አገራዊ ጥቅም ዋስትና እሚያገኘው ከወዳጅነትና ከፍትህ ነው።፥ልክ ናቸው አይደሉም፥ን ትተን ግን ኢትዮጵያን አቆርቁዞና ቀስፎ መያዝ ዋነኛ የህልውናቸው ዋስትና አድርገው ስለቆጠሩት በዚያ አቅጣጫ በሙሉ አቅማቸው ቢረባረቡ እሚገርም አይሆንም። የግብጽ ጥፍሮችን ከአንገታችን ማላቀቅ ደግሞ ለእኛ የህልውናና የሞት ሽረት ጉዳይ ይሆናል።

ኢትዮጵያ የራሴን የተፈጥሮ ሀብት፣ የአባይን ወንዝ ውሃ በመጠቀም የማልማት መሠረታዊ መብት አለኝ፤ ሌሎች ባለድርሻ አካላትም ከውሃው ማግኘት ያለባቸውን ድርሻ ያገኛሉ።የግድቡ መሰራት በውሃው መጠን ላይ የሚያደርሰው ችግር የለም፤ ግድቡ የአካባቢውንም፤ ሀገሮች ተጠቃሚ ያደርጋል የሚለውን አቋሟን በተደጋጋሚ ገልጻለች።

ኢትዮጵያ የዓባይን ውሃ ገድባ ፍትሃዊ በሆነ ሁኔታ ለመጠቀም በምታደርገው እንቅስቃሴ ከውስጥም ከውጭም አካላት እንከኖችና ፈተናዎች ለምን ይበዙባታል? መፍትሔውስ ምን መሆን ይገባዋል? የሚሉትንና ተዛማጅ ጉዳዮች በመያዝ በአ.አ.ዩ. የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህርና የዓባይ ውሃ ጉዳይ ተመራማሪ ከሆኑት ከፕሮፌሰር ያዕቆብ አርሳኖ፣ በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ቅርስ ጥናት ትምህርት ክፍል መምህር ከሆኑት ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ በከሬ እና የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሕዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ዋና ዳይሬክተር ከሆኑት ዶክተር አረጋዊ በርሄ ጋር ቆይታ አድርገናል።

የዓባይ ተፋሰስ የውሃ ገብነትና የበርሃማነት ሁለት ተቃራኒ ጫፎችን በአንድ የሚያስተሳስር ቢሆንም፣ ሁለቱን ጫፎች በአንድ የሚያዋህድና የኢኮኖሚ ጥቅም ተጋሪ ማድረግ አዳጋች ሆኖ ለዘመናት ቆይቷል።የተፈጥሮ ሀብቱ የጋራ ባለቤትነትን ባረጋገጠ መንገድ፣ በፍትሐዊነት ሊጋሩት የሚገባ የውሃ ሀብት መሆን ሲገባው የአንድ ወገን ተጠቃሚነት እንዲቀጥል የሚፈልጉ አካላት አሁንም አሉ።

ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብቱ አመንጪና ባለቤት ብትሆንም ይህንን ሀብቷን ሳትጠቀምበት ቆይታለች።የተለያዩ የኢትዮጵያ መንግሥታትና ነገሥታት ተፋሰሱን የማልማት ጽኑ ፍላጐታቸውን በሚገልጹበት ወቅት ዘንግተውት የማያውቁት ጽኑ የሆነው አቋም፣ በተፋሰሱ ተጋሪ ሀገር ሕዝቦች ላይ ጉዳት ያለማድረስ መርሆ እንደሆነ ታሪካዊ ማስረጃዎች ያመላክታሉ።

በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ቅርስ ጥናት ትምህርት ክፍል መምህር ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ በከሬ እንደሚሉት የዓባይ ወንዝ ታሪክ 30 ሚሊዮን ዓመታት ታሪክ ያለውና ግብጽ፣ አክሱም እና ኑቢያ ሥልጣኔ ያበረከቱበት ነው።እነዚህ ሥልጣኔዎች አንዱ ከአንዱ ጋር በንግድ ዕርስ በዕርስ በጥቅም የተሳሰሩና የትብብር መንፈስ ያለው ታሪክ አላቸው። ዘመናዊው ታሪክ ሲመጣ ግን ግጭቱ መጣ። የቅኝ አገዛዝ ታሪክ

ተጀምሮ በዘመናዊ እርሻ ምርት በማምረት ወደ ውጭ መላክ ሲጀመር እንግሊዞች ግብጽን መቆጣጠር ማለት ዓባይን መቆጣጠር መሆኑን አምነው አስዋን ግድብን ገድበው የማያቋርጥ የመስኖ ልማት ለማልማት የሚያስችል ስትራቴጂ ነደፉ።ሱዳንም አብራ ተጠቃሚ ሆነች።ግብጽም እ.ኤ.አ. 1922 ነፃ ስትወጣ የእንግሊዝን ስትራቴጂ ተከተለች።ከዚያ በኋላ ግብጾች ‹‹የውሃው የመጀመሪያዎቹ ተጠቃሚዎች እኛ ነን፤ ማንም ሊነካ አይችልም፤ ታሪካዊ መብት አለን›› ማለት ጀመሩ።ሱዳንም የግብጽን ጥቅም በማይነካ መልኩ ተጠቃሚ ሆናለች፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት በመጋቢት ወር 2003 ዓ.ም. የታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታን ይፋ ባደረገበት ወቅት ለዘመናት ሲንፀባረቅ የቆየውን የኢትዮጵያ ጽኑ አቋም የሆነውን ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን አልዘነጋም።በአሁኑ ወቅት ከአዲስ አበባ በ850 ኪሎ ሜትር በሚርቀው በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጉባ እውን እየሆነ ያለው የዓባይ ውሃ ልማት ፕሮጀክትን ለመገንባት ተወጥኖ የነበረው በ1956 ዓ.ም. ነበር።ከቀድሞው ዕቅድ እጅግ ብዙ እጥፍ ሆኖ ዛሬ ላይ የኢትዮጵያንና የተፋሰሱ ሀገራት ተጋሪነት ሊያረጋግጥ እየተቃረበ ይገኛል።የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ይፋ ሆኖ ወደ ትግበራ መግባት በዘመናት የቆየውንና የአንድ ሀገር የብቻ ሀብት መስሎ የሚታየውን ፖለቲካዊ አስተሳሰብና እምነት በመቀየር ላይ ጉልህ ምልክት አለው።ግድቡ ሲጠናቀቅ የዘመናት የኢፍትሃዊነት ቀንበርን በመስበር ኢትዮጵያንም ሆነ ሌሎች የተፋሰሱ ተጋሪ ሀገሮችን ነፃ ከማውጣት ባሻገር ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ፋይዳ አለው።

ይሁን እንጂ ግድቡን በተመለከተ የተለያዩ እንከኖችና ሳንካዎች ሲያጋጥሙ ይስተዋላል።ኢትዮጵያ የዓባይን ውሃ ተጠቅማ ግድብ በመገንባት ፍትሃዊ በሆነ ሁኔታ ለመጠቀም የምታደርገው እንቅስቃሴ ከሀገር ውስጥና ከውጭ አካላት ለምን ፈተናዎች እንደበዙባት በርካቶች ብዙ ብለዋል።እንደዶክተር አረጋዊ በርሄ ገለፃ የታላቁ ህዳሴ ግድብ የኢትዮጵያውያንን ሕይወት በዋናነት የሚለውጥ ከመሆኑ በላይ ሉዓላዊነትን የሚያስከብር ነው።ከዚህ አልፎ የዚህ ግድብ መጠናቀቅ ለአካባቢውም አስተዋጽኦ አለው።በውጤቱም ይሁን በሚያመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል ለኢትዮጵያ መቀየርና መለወጥ ለአካባቢውም የሚያበረክተው ትልቅ አስተዋጽኦ አለው።ይሄን ዕድገት የማይፈልጉ ወገኖች እንቅፋት ሆነው መቆየታቸውን ያስረዳሉ።

የኢትዮጵያን እድገት የማይፈልጉ ወገኖች እነማን እንደሆኑም ዶክተር አረጋዊ ይዘረዝራሉ።በተለይ የህወሓት አመራር



ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ በከሬ

ከፖለቲካው መገንጠል ጋር ተያይዞ የውጭ ኃይሎችም እንዲገቡ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ አንጻር ጥቅማቸው የሚጎድል እየመሰላቸው በህዳሴ ግድቡ ላይ ተጽዕኖ ለመፍጠር ሙከራዎች ሲያደርጉ ቆይተዋል።ይሄ ሙከራ ግን በፕሮፖጋንዳ ደረጃ እንጂ በተጨባጭ መሬት ላይ የዋለ ችግር አልፈጠረም።አንዳንድ ጽንፈኞች ከህወሓት አመራር ጋር በመተባበር ሕዝቡን እየከፋፈሉ፣ ተጽዕኖ ለመፍጠር ሞክረዋል፤ ሰላም እንዳያገኝ፣ ተረጋግቶ እንዳይቀጥል፣ ለህዳሴ ግድቡ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዳያደርግ መጠነኛ እንቅፋት ፈጥረዋል። እነዚህ ከህወሓት አመራር ጋር አብረው የሚጠፉ ኃይሎች ስለሆኑ እስከዚህ ድረስ ከባድ ናቸው ተብለው አይገመቱም።የውጭ ኃይሎች ተልዕኮ ይዘው የሚመጡም ሰዎች ይኖራሉ።ለግል ጥቅማቸው ብለው ወይም ሥልጣን ለመያዝ ብለው ከውጭ ኃይሎች ጋር በመተባበር የሚሠሩም አይጠፉም።እነዚህ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብን ጥቅም ለማቆም አይችሉም።ሕዝቡ አሁን ተባብሮ ተነስቷል፤ እዚህ ግባ የሚባል እንቅፋት ይፈጠራሉ ብለው እንደማይገምቱ ዶክተር አረጋዊ ያረጋግጣሉ።

ዶክተር አረጋዊ እንደሚሉት ከውጭ አካላት እንከን ፈጣሪዋ በዋናነት ግብጽ ነች።የግብጽን ዱካ እየተከተለች እንቅፋት የምትፈጥረው ደግሞ ሱዳን ነች።ሱዳን ከግብጽ እንዲሁም ከህወሓት አመራሮችና ርዝራዦች ጋር ባላቸው ቅርበት የተነሳ የሚፈጥሩት ይመስለኛል ይላሉ።እነዚህ ኃይሎች ቀኝ ገዢዎች ሲሠሩት የነበረው ሴራ በመከተል ከዓባይ ውሃ የሚገኘውን ጥቅም ለብቻቸው ለማድረግ ባላቸው ምኞት፣ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ችግር ለመፍጠር ይነሳሳሉ።የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለነቃ፣ የዓለም ሕዝብም የዓባይን ግድብ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ስለሚገባው ልፋታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየመነመነ ነው ያለው።የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድ ልብ ተነስቷል።ይሄን ግድብ ዳር ለማድረስ አሻራውን ለማኖር በአድዋ ጦርነት ጊዜ በአንድነት ተነሳስቶ የጣልያንን ወራሪ ኃይል እንዳሸነፈው ሁሉ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ትልቅ ትንሽ ሳይል ከምንጊዜውም በላይ ተነቃቅቶ ስለተነሳ ግድቡ ተጠናቆ እንደሚታይ እርግጠኛ መሆን እንደሚቻል ዶክተር አረጋዊ እምነታቸውን ያስቀምጣሉ።

ኢትዮጵያ ቀደም ሲል በያዘችው ዕቅድ የታላቁ ህዳሴ ግድብን አጠናቃ የኢኮኖሚ ተጠቃሚ ሆና ከፍተኛ ደረጃ እንዳትደርስ ከውስጥም ከውጭም ስለገጠሟት እንከኖች ፕሮፌሰር ያዕቆብም ይዘረዝራሉ።እንደእሳቸው ገለፃ በዋናነት የሚጠቀስ ፈተና ግድቡ በተጀ



ዶክተር አረጋዊ በርሄ

መረበት ዕቅድ መሠረት በፍጥነትና ጥራት ባለው ሁኔታ በጥንቃቄ እንዳይሠራ በኃላፊነት የተመደበው የኢፌዴሪ ብረታብረት እና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን /ሜቴክ/ የተባለው ድርጅት የፈጠረው ችግር አለ።ግድቡ በተያዘለት ዕቅድ ባለመጠናቀቁ የሕዝብም የመንግሥትም ወጪ ጨምሯል።በዚህም በሀብት ብክነት በኩል ጫና መፍጠሩ የሚታወቅ ነው።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ዋና ሳንካና እንቅፋት ግብጽ መሆኗ ሁሉንም ያስማማ ይመስላል።የአባይ ውሃ ባለሙሉ መብት እኔ ብቻ ነኝ የሚል አቋሟን በግልፅ አቅርባ ሞግታለች።ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብቷን ተጠቅማ ልማቶችን አካሂዳለሁ ብላ ስትነሳ በይፋ ተቃውማለች።የዲፕሎማሲ መድረኮችን ተጠቅማ በቅርቡም በሩቅም ላሉ ወገኖች አሳሳች መረጃዎችን ረጭታለች። በቅርቡ ደግሞ ሱዳን የግብጽን ፈለግ የምትከተል እንደምትመስል ፕሮፌሰር ያዕቆብ ይገልጻሉ፡፡

ከዚህም ባለፈ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ውጤት ለኢትዮጵያም ሆነ ለአካባቢው ሀገሮች የሚሰጠው ጥቅም በይፋ የሚታወቅ ቢሆንም አንዳንድ ኢትዮጵያዊ ዜጎች ግድቡ እንዲስተጓጎል ሲሠሩ ይታያል። እንደ ዶክተር አረጋዊ አነጋገር እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች አርቀው የማያስቡ፣ ለሀገር እድገት ግድ የሌላቸው እንዲሁም ለግል ጥቅምና ሥልጣን የተስገበረቡ ወገኖች ናቸው። በኢትዮጵያ ታሪክ ባንዳዎች ነበሩ፤

**የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የኢትዮጵያን የኃይል ፍላጐት ከማረጋገጡ በላይ ኢትዮጵያን በዓለም የኃይል አቅርቦት ገበያ ያስተዋውቃታል።**

እነዚህ ባንዳዎች በየትኛውም ክልል ከማንኛው ብሔረሰብ ይገኛሉ።ይሄ የነበረም፣ አሁንም ያለ ነገር ነው። እነዚህ ሰዎች የሀገራቸውን ጥቅም ቅድሚያ ስለማይሰጡ፣ ለራሳቸው ጥቅምና ሥልጣን ቅድሚያ ስለሚሰጡ አሳልፎ የመስጠት አዝማሚያ የሚያሳዩ ወገኖች አሉ። ይህ ተግባራቸው በሕዝቡ በተባበረ ትግል ሊገታ የሚችል ነገር ነው። እነዚህ ኃይላት የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም ለማሰናከል ያላቸው ችሎታ በጣም ትንሽ ነው። ሕዝቡ አሁን ተባብሮ ተነስቷል፤ መተባበሩ እስከቀጠለ ድረስ እዚህ ግባ የሚባል እንቅፋት ይፈጠራል ብለው አይገምቱም።

ቅጥረኝነት፣ ከሃዲነትና ጥቅም ፈላጊነት ቢኖርም ብዙ ጊዜ ታሪካችን የሚያሳየው አንድነታችንን የሚያጠናክር ነው የሚሉት ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ አብዛኛው ሕዝብ በህብረት ስር በመሆኑ እንከን ለመፍጠር የሚሞክሩትን ሰዎች ይቋቋማል። በመሆኑም ፋታ ባለመስጠት ሁልጊዜም በአንድነት በመቀጠል ግድቡ እንዲያልቅ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚያስ ፈልግ ያስገነዝባሉ።

ፕሮፌሰር ያዕቆብ በበኩላቸው ኢትዮጵያዊ ሆነው ግድቡ በተያዘው እቅድ እንዳይጠናቀቅ ለማስተጓጎል ጥረት የሚያደርጉ ሰዎች በሁለት ምክንያት የተሳሳቱ ናቸው ይላሉ።አንደኛው ስህተት ነገረ ዓለሙ ሁሉ ጠፍቷቸዋል፤ ብሔራዊ ጥቅም ምን እንደሆነ አልተረዱም ማለት ነው። የሀገራቸው ኢትዮጵያ ልማት ነገ ለእነሱም ልጆች፣ የልጅ ልጆቻቸው የሚጠቅማቸው መሆኑን ያልተገነዘቡ ናቸው። ሁለተኛው የሀገራቸው የኢትዮጵያን ልማት እንዳያዩ በተለያዩ ምክንያቶች የተደለሉ ወይም ደግሞ ከግብጽ ጋር መተባበሩ እነሱ የሚፈልጉትን የፖለቲካ ጥቅም ያስገኝልኛል በሚል ራስ ወዳድ የሆነ የተሳሳተ አስተሳሰብ በመነሳት ይመስላል።ደግነቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀገር ወዳድ፣ ብሔራዊ ጥቅም የሚጠብቅና ዳር ድንበር የሚያስከብር ነው።በታሪክም በተለያዩ ጊዜያት የታየ በመሆኑ እነዚህ ኃይሎች በጊዜያዊነት አንዳንድ ችግር ሊፈጥሩ ቢችሉም እርባና ሊኖራቸው አይችልም። ኢትዮጵያውያን በጋራ ጥቅማቸው ላይ ህብረት በመፍጠር ጥቅማቸውን ያለማስነካት ታሪክ ባለቤት እንደሆኑ ይገልጻሉ።

የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የኢትዮጵያን የኃይል ፍላጐት ከማረጋገጡ በላይ ኢትዮጵያን በዓለም የኃይል አቅርቦት ገበያ ያስተዋውቃታል። ከህዳሴው ግድብ የሚመነጨው ኃይልን በሱዳን - ግብፅ - ሊቢያ - ሞሮኮና ስፔን ድረስ መሸጥ ይቻላል።በሌላ መስመር በሱዳን - ግብፅ - ጆርዳን - ሶሪያና ቱርክ ድረስ የኤሌክትሪክ ኃይል ማቅረብ ያስችላል። የቀድሞው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ የነበሩት አቶ ምሕረት ደበበ፣ በአንድ ወቅት እንደተናገሩት በዓለም ገበያ ለኤሌክትሪክ ኃይል በኪሎ ዋት ሰዓት የሚሰጠው አማካኝ ዋጋ 20 የአሜሪካን ሳንቲም መሆኑን ገልጸው፣ በዚህ የዋጋ ተመን መሠረት ከህዳሴው ግድብ የኃይል ሽያጭ 3.06 ቢሊዮን ዶላር በዓመት ማግኘት እንደሚቻል፤ ይኸውም በጂዲፒው ላይ የስድስት መቶኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ተናግረዋል።ይህ ከሆነ የህዳሴው ግድብን እውን ለማድረግ የሚጠይቀውን ወጪ በአጭር ጊዜ መመለስ

ይቻላል። በመሆኑም በግድቡ የሚመነጨውን የኤሌክትሪክ ኃይል ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ከማዋል በተጨማሪ ሌሎችም የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ሆነው ኢትዮጵያም በኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንደምትሆን ያሳያል።

የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የሚያጠራቅመው ውሃ ምንም ዓይነት ሰው ሠራሽ ጣልቃ ገብነት ሳይጨመርበት በዓመት 6,540 ቶን የዓሣ ምርት ማግኘት ይቻላል። በዚህ የህዳሴ ግድብ ውሃ ላይ በሰው ሠራሽ መንገድ የዓሣ ልማት ማካሄድ ከተቻለ ደግሞ በዓመት 30 ሺህ ቶን ዓሣ ማለትም በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ የሚመረተውን ዓሣ መጠን እጥፍ ሊያደርገው እንደሚችል፤ የሚለማውን የዓሣ ሀብትን ወደ ውጭ በመላክ እስከ 100 ሺህ ዶላር ዓመታዊ ገቢ ማግኘት እንደሚቻል በሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ መምህርና የዓሣ ሀብት ልማት ላይ ተመራማሪ የሆኑት የዶ/ር ዮሴፍ ተክለ ጊዮርጊስን የጥናት ግኝትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

በአካባቢው የሚከማቸው የውሃ መጠንና ተራራማው መልከዓ ምድር አዕዋፍን በመሳብ የቱሪስቶችን ቀልብ ሊገዛ እንደሚችል ይታወቃል። ጐብኚዎችን በግድቡና በኃይል ማመንጫ ቤቶች ውስጥ ለውስጥ በማስጐብኘት ገቢ ማግኘት ይቻላል።በምሽት ደግሞ በውሃው ላይ የተለያዩ ሰው ሠራሽ ተለዋዋጭ ብርሃናማ ቀለማት በመፍጠር፣ ከውሃው ፍሰት ጋር የሚቀናጅ ማጀቢያ ሙዚቃ በማከል የጐብኚዎች ቁጥር ጨምሮ የቱሪስት የመስህብ ቦታ ማድረግ ይቻላል።

ከኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ፣ ከዓሣ ሽያጭም ሆነ ከጎብኝዎች የሚገኘው ገቢ ለኢኮኖሚ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው።የግድቡ መገንባት ሌሎችም ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች አሉት። ለዚህ ነው የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ጉዳይ ለኢትዮጵያውያን የህልውና ጉዳይ የሚሆነው።

ኢትዮጵያ የዓባይን ውሃ ከተፋሰሱ ሀገራት ጋር ፍትሃዊ በሆነ ሁኔታ ተጠቅመን እንልማ የሚል ሀሳብ ይዛ ስትንቀሳቀስ ከሌሎቹ የተፋሰሱ ሀገራት በጎ ምላሽ አግኝታለች።ግብጽ በቅርቡ ደግሞ ሱዳን ለመቀበል ተቸግረዋል።ዶክተር አረጋዊ በጉዳዩ ላይ አስተያየታቸውን ሲሰጡ፤ ግብጽም ሆነ ሱዳን ለመቀበል የተቸገሩትበት ምክንያት ጥቅሙን ለብቻቸው ለማድረግ ፈልገው ነው።የግድቡ ሥራ ተጠናቆ ተግባር ላይ ሲውል የውሃ መጠኑ ይቀንሳል የሚል ፍራቻ ስላላቸው ነው። ፍራቻቸው ግን ሀቁን ተንተርሶ የመነጨ አይደለም። ከኢትዮጵያ ጋር ቢተባበሩ ኖሮ የበለጠ ይጠቀሙ ነበር። በአንድ በኩል ፍራቻ ነው።በሌላ በኩል ደግሞ የገዢዎቻቸውን የኮሎኒያሊስቶችን አሠራር በመከተል ለብቻ ለመጠቀም ያለ ፍላጎት እየተጫናቸው ይመስላል ብለዋል።




ፕሮፌሰር ያዕቆብ አርሳኖ

**ኢትዮጵያ ግድቡን ሙሉ በሙሉ በመጨረስ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ መሆን ስትጀምር የግብጽ ሞኖፖሊ ይሰበራል።**

በዘመናዊው ታሪክ ግብጽ በዓባይ ውሃ ጠፍጣፋ የሆነውን ለም መሬት ተጠቅማ ሰፋ ባለ ሁኔታ አልምታለች።ሱዳን በወንዙ ዳርቻ ያለው መሬቷ ይሄንን ያህል ሰፊ ስላልሆነ በመስኖ ተጠቅማ የምታለማው እንደ ግብጽ አይደለም። ሱዳን ውስጥ የተሠሩት ግድቦች የግብጽን ፍላጎት ሊነኩ በማይችሉ መልኩ የተሠሩ ናቸው። ዋናው ተጠቃሚና ውሃውን የምትቆጣጠረው ግብጽ ነች። ፕሮፌሰር አየለ ሌሎች የተፋሰሱ ሀገራት ፍትሐዊ በሆነ ሁኔታ በጋራ ለመጠቀም ስምምነት ላይ መድረሳቸው ለግብጽ በሽታ ነው ይላሉ። ምክንያታቸውን ሲገልጹ በዓባይ ውሃ የኤሌክትሪክ ኃይል ታመነጫለች፣ የመስኖ እርሻ ትጠቀማለች፣ ዓሣ ለማምረት ሆነ ለቱሪዝም ትጠቀማለች። ከዚህ በተጨማሪ ውሃውን ከግድቡ በማውጣት በረሃውን እያለማች ትገኛለች። ከዚህ በሚገኘው ጥቅም ከፍተኛ የሆነ የመከላከያ ኃይል ፈጥራለች። በዚህ የመከላከያ ኃይሏ በመመካት የዓባይን ውሃ ማንም መንካት አይችልም በማለት ለማስፈራራት እንደምትሞክርና ሱዳንም የጥቅም ተጋሪ ለመሆን ካላት ፍላጎት የተነሳ የምትተባበር መሆኑን ያስረዳሉ። ሰው ሠራሽ የሆነው የናስር ሀይቅ በረሃ ላይ የተገነባ ስለሆነ ውሃው በአብዛኛው ተኖ ነው የሚያልቀው።ኢትዮጵያ ዓባይን በመገደቧ ዓመቱን ሙሉ የተመጠነ ውሃ ለግብጽም ለሱዳንም ስለሚደርሳቸው ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ገልጸው ባለፈው ዓመት ወደ ሙቶ ሺህ ሕዝብ በጎርፍ ምክንያት ሱዳን ውስጥ መፈናቀላቸውን እንደ ማሳያ ያቀርባሉ።

ግድቡን በተመለከተ ሌሎች የተፋሰስ ሀገሮች



ግድቡ በምሽትም ይሠራል

ኬንያ፣ ሩዋንዳ፣ ታንዛንያ፣ ቡሩንዲ ከኢትዮጵያ ጋር በጣም በቅርብ እየተጋገዙ የሚሠሩ ሀገሮች ናቸው።ከአሁን በፊት ከግብጽና ከሱዳን አንገት ለአንገት ተያይዘው ድርድር አካሂደው የትብብር ማዕቀፍ ሁሉ ፈርመዋል። ስለዚህ እነዚህ የኢትዮጵያ ጎረቤት ሀገሮች በኢትዮጵያ ላይ እንቅፋት ሆነው አይታዩም፤ እንዲያውም አጋዥና ተባባሪ ናቸው በማለት ፕሮፌሰር ያዕቆብ የተፋሰሱ ሀገራት የትብብር ማዕቀፍ እንዴት እንደተፈራረሙ ያስታውሳሉ።

ሀሳባቸውን በመቀጠል፤ ግብጽ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ሱዳን እንቅፋት የሚሆኑት ጥቅማችንን እናጣለን በሚል ነው።ውሃ አመንጪ የሆነችው ኢትዮጵያ በዓባይ ውሃ ለመጠቀም የምታደርገው እንቅስቃሴ ግብጽንም ሆነ ሱዳንን ለመጉዳት ታልሞ የሚተገበር ስላልሆነ የተፋሰሱ ሀገራት ፍትሃዊ በሆነ አጠቃቀም ልማትን እያካሄዱ ግብጽም ሆነ ሱዳን የውሃው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ፍላጎት አላት። ግብጾች በዚህ ጉዳይ ስለማይተማመኑ፣ ከዚህ በፊት ውሃውን እንደፈለጋቸው ይጠቀሙ ስለነበረ ይህን የበላይነታቸውን ማስቀጠል ይፈልጋሉ። በጋራ ጥቅም ላይ ከመመስረት ይልቅ የሌሎች መጠቀም እኛን ይጎዳል ብሎ በማሰብ መልካም ያልሆነ መንገድ ተከትለው ነው የሚገኙት ብለዋል።

ሱዳን ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ከምታገኘው ጥቅሟ ይልቅ ለግብጽ ፖለቲካዊ ጥምረት ትኩረት የሰጠችበትን ምክንያት ዶክተር አረጋዊ በርሄ ሲናገሩ፤ ሱዳኖች ከግብጽ ጋር የሚተባበሩት የፍራቻ ግንኙነት ነው።ኢትዮጵያ ዓባይን ገድባ ለራሷ ብቻ ተጠቃሚ ትሆናለች የሚል ፍራቻ ነው። ይሄ ፍራቻ ግን በውል ሲታይ፣ በዕውቀት ሲታይ ትርጉም የሌለው ፍራቻ ነው። ምክንያቱም ውሃውን በአግባቡ ከተጠቀምን፤ በተለይ ወደ ሰማይ በእንፋሎት መልክ የሚተነው መቀነስ ከተቻለ፤ ውሃ ወደ መሬት እንዲሰርግ ለማድረግ ከተቻለ፤ ጫካው እንዲለማና እንዲጠበቅ ማድረግ ከተቻለ፤ ይሄ ሁሉ ፍራቻቸው ትርጉም አይኖረውም ነበር።ፍራቻው ከመጠራጠርና ካለማወቅ የተነሳ ይመስላል በማለት ሱዳን ፍራቻዋ እያየለባት ከግብጽ ጋር ህብረት ለመፍጠር እንደተገደደች ይገልጻሉ፡፡

የዓባይን ውሃ አጠቃቀም በተመለከተ ግብጽ ይዛ የምትንገታገተው የቅኝ ገዥዋ እንግሊዝ የፈጠረችውን እንጂ ሀገራቱ በጋራ ስምምነት አድርገው አይደለም የሚሉት ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ ሱዳን የራሷን አቋም ይዛ ተንቀሳቅሳ እንደማታውቅና ግብጽ የምትላትን የምትከተል እንደሆነች ይገልጻሉ። በመሆኑም የሱዳን አቋም አይገርማቸውም።በመቀጠልም፤ ‹‹የዓባይን ውሃ አጠቃቀም ታሪክ ስገመግም አሁን ሱዳን ያደረገችው ወረራ፣ ሱዳን ሳትሆን ግብጽ ናት የወረረችን እላለሁ›› በማለት ግምገማቸውን ያስቀምጣሉ።

ሱዳን በግድቡ ዙሪያ የኢትዮጵያን ሀሳብ የምትቃወም ከሆነ የሱዳንን ብሔራዊ ጥቅም አጉልቶ የሚሠራ መንግሥትና አመራር ሱዳኖች የላቸውም ማለት ይቻላል የሚሉት ፕሮፌሰር ያዕቆብ ደግሞ ምክንያታቸውን ሲዘረዝሩ፤ ለሱዳን ውሃ ዓመቱን ሙሉ ስለሚሄድላት የጎርፍ ውሃ ይዞት የሚመጣውን ደለል በብዙ መጠን ይቀንስላታል።ዓመቱን ሙሉ ውሃ ማግኘቷ ውሃ አጠር በሆነውና በተንጣለለ ለም መሬት ላይ ለሚሠራ የእርሻ ሥራ እንዲሁም በመስኖ ለሚለማ የግብርና ሥራዎችም ተስፋ ይሆናታል።ይህ ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያ የሚቀርብላት የኤሌክትሪክ ኃይል በጣም ጥሩ በሆነ ዝቅ ባለ ዋጋ ዓመቱን ሙሉ የምታገኝበት ሁኔታም ነበር።ከኢትዮጵያ ጋር በሀገር ደረጃ ከሚደረጉ ትብብሮች ባሻገር በግድቡ

ምክንያት በሕዝቦችና በባለሀብቶች መካከል ሌሎች የትብብር መስኮችም ሊበ ጁና ሊደራጁ የሚችሉባቸው ዕድሎች አሉ ይላሉ።ሱዳን ይህን ብሔራዊ ጥቅሟን በግብጽ ጫና ወይም በአመራር ላይ ያሉ ተታለው ወደ ግብጽ ማድላታቸው አስገራሚ እንደሆነባቸው ይናገራሉ።

ኢትዮጵያ ከውስጥም ሆነ ከውጭ አካላት አሁንም ሆነ ወደፊት በዓባይ ውሃ አጠቃቀሟ እንከኖችና ፈተናዎች እንዳይደርሱባት ምን ማድረግ እንደሚገባትና ሲድርስባት እንዴት ባለ ሁኔታ መፍትሔ መስጠት እንደሚገባት ዶክተር አረጋዊ ቁልፉ መተባበር ነው ይላሉ።በሀገርና በጋራ ጥቅም ላይ አንድ ዓይነት ራዕይ፣ አንድ ዓይነት አስተሳሰብ፣ አንድ ዓይነት ሥነልቦና ማሳደር ያስፈልጋል። ይሄ ካለ ማንም የውጭ ኃይል ጥቃት ሊያደርስብን አይችልም።ቁልፉ ነገር በሀገር ጉዳይ ወይም በሕዝብ ጥቅም እና በግል ጉዳይ ወይም በግል ጥቅም መካከል ያለው ልዩነት ጠንቅቆ አውቆ በጋራ ስትራቴጂ መንደፍ፤ ማስተባበርና መተግበር ነው።ተባብሮ መቆም ይገባል።ጣልያንን ያሸነፍነው ስለተባበርን ነው።ከጫፍ እስከ ጫፍ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተባብሮ ጣልያንን ስለገጠመው አሸነፈው፤ ባይተባበር ኖሮ አያሸንፍም ነበር።ጠበንጃ ወይም ጀብደኝነት ብቻ አይደለም የሚያሸንፈው። የሚያሸንፈው ህብረት ነው።ሕዝቡ ስለተባበረ ነው ጠላትን ማሸነፍ የተቻለው።ጣልያንም ባህር ተሻግሮ መጥቶ ሀገራችንን የቅኝ ግዛት ሀገር ለማድረግ ሕዝባችንን ባርነት ውስጥ ለመክተት፣ መሬቷን ለራሱ ሕዝብ የእርሻ ቦታ ለማድረግና በግብርና ለመጠቀም አቅዶ ነበር፤ ነገር ግን አልተሳካለትም።ያልተሳካለት ዋናው ምክንያትና ምስጢር ሕዝቡ ሀገር ወዳድ ስለሆነና በህብረት ተነሳስቶ ሀገሬን አሳልፌ አልሰጥም ስላለ ነው።ይሄ እንደ አንድ ታሪክ በሕዝቡ ውስጥ ፀርፆ ያለ ስለሆነ ወደ ፊትም እንደዚህ ያለ ትንኮሳ ወይም የወረራ ዕቅድ የማይሠራ መሆኑን በተለያየ አጋጣሚ አሳይቷል፤ ያሳያልም።ህብረት ካለ የዓባይን ውሃ ተጠቃሚነት ይሁን ሌላ የሀገር ፍላጎቶች ሊጠበቁ ይችላሉ።

ፕሮፌሰር ያዕቆብ የዶክተር አረጋዊን ሀሳብ በመደገፍ ዋናው ነገር ኢትዮጵያ የራሷ ጥቅምና ህልውና፣ ዳር ድንበሯን፣ ልማቷንና ዕድገቷን ለማስቀጠል ኃላፊነቱን የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ መያዝ አለበት ይላሉ።የኢትዮጵያን ጥቅም የማይፈልጉ ከቅርብም ሆነ ከሩቅ ዛሬም ነገም እንደ ኢትዮጵያ ተባብሮ በመሥራት ነቅቶ መጠበቅ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ። ይህ ግድብ የሀገሪቱ የሰንደቅ አላማ ፕሮጀክት ተብሎ የተያዘ ስለሆነ በመላው ኅብረተሰብ ድጋፍ ሳንካዎቹንና

> **ግድቡን በፍጥነት ጨርሶ የታቀደውን የኤሌክትሪክ ኃይል በማመንጨት ተጠቃሚ በመሆን በቀጣይ ዘመን ላይ ኢትዮጵያ የተሻለ የኢኮኖሚ ዕድገትና ብልጽግና እንድታገኝ ጥረት ማድረጉ መቀጠል ያስፈልጋል።**

ተግዳሮቶቹን በጣጥሶ መሄድ ይገባል።ግድቡን በፍጥነት ጨርሶ የታቀደውን የኤሌክትሪክ ኃይል በማመንጨት ተጠቃሚ በመሆን በቀጣይ ዘመን ላይ ኢትዮጵያ የተሻለ የኢኮኖሚ ዕድገትና ብልጽግና እንድታገኝ ጥረት ማድረጉ መቀጠል ያስፈልጋል።የኢትዮጵያን እድገት የማይፈልጉ ምንጊዜም ስለማይተኙላት ነቅቶ በመጠበቅ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ እንደሚገባ ያሳስባሉ፡፡

ፕሮፌሰር ያዕቆብ እንደሚገልፁት በጉልበት ለመምጣት ለሚፈልጉ አካላት በተቀናጀ መንገድ እንደ አመጣጣቸው መመከት ነው።የኢትዮጵያ ተጻራሪዎች እንዳይጠናከሩ ከውስጥ ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያ ወዳጆች ጋር ከውጭም በጣም ተቀራርቦ መሥራት ያስፈልጋል።ትኩረት በመስጠት በጣም ከፍተኛ የሆነ የዲፕሎማሲ ሥራ መሥራት ይገባል።ይሄ ወዳጆቿ አጠገቧ እንዲሆኑ ይጠቅማል። ወዳጅነት እንዲጠነክር በንግድም፣ በኢንቨስትመንትም በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ ይገባል። ጠላቶቿ እንዲያፍሩና እንዲሸማቀቁ ኢትዮጵያን ለመጫን ፍላጎትና አቅም እንዳይኖራቸው ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። ይሄ በአንድ ጀንበር የሚደረግ ሳይሆን የሚገነባ፣ የሚያድግና ከዚያም አቅም የሚያገኝ የኢትዮጵያን ከፍታና ጉልበት በአካባቢውም ሆነ በዓለም ዙሪያ የሚያጎላ ስለሆነ ኢትዮጵያ በዚህ አቅጣጫ ራሷን ማስተካከልና መተግበር አለባት በማለት ኢትዮጵያውያን የጋራ ጥቅማቸው እንዳይነካ በህብረት መሥራታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በዲፕሎማሲ መድረክም በጣም መሥራት እንደሚገባ ያሳስባሉ፡፡

ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ ህብረትን ጠብቆ በአንድነት መሥራት ከሚለው ከሁለቱ ምሁራን ሀሳብ ጋር ይስማማሉ። ኢትዮጵያ ግድቡን ሙሉ በሙሉ በመጨረስ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ መሆን ስትጀምር የግብጽ ሞኖፖሊ ይሰበራል።ይህ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሦስት አራት ተጨባጭ የሆኑ በዓባይ ውሃ ላይ ማስቀመጥ ከተቻለ ያን ጊዜ ግብጽ ወደ ዴሞክራሲያዊ አሠራር እንዲሁም ፍትሃዊ በሆነ ሁኔታ ለመጠቀም ትስማማለች። ዋናው ቁልፍ ጉዳይ ግድቡን ጨርሶ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ እንዲሁም ሌሎች ተጨባጭ የሆኑ ሥራዎችን ዓባይ ላይ መተግበር እንደሆነ አጽንኦት ሰጥተው ይገልጻሉ።

ግብጾች ለዘመናት በኖረው ፕሮፓጋንዳቸው «ግብጽ ያለ ናይል መኖር አትችልም» የሚለው ስብከታቸው አሁን ጊዜው አልፎበታል። በተቃራኒው የናይል ወንዝ አመንጪ አገራት ያለ ወንዙ መኖር አይችሉም የሚባልበት ደረጃ ላይ እንደደረስን ማወቅና መረዳት አለባቸው። የግብጽ ኢኮኖሚ እርሷ እንደምትለው በግብርና ላይ የተንጠለጠለ አይደለም። ግብርና ያለው ድርሻ ከ13 በመቶ አይዘልም። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ የተፋሰሱ አገራት ኢኮኖሚ ግን በግብርና ላይ ያለው ጥገኝነት እስከ 80 በመቶ የሚደርስ ነው። ስለሆነም የአባይ ወንዝ ከግብጽ ይልቅ ለኢትዮጵያ በጣም አስፈላጊ መሆኑን በዚህች ቁንጽል ማስረጃ ብቻ መመልከት ይቻላል። መሬት ላይ ያለው እውነታ ይሄም ሆኖ ግን ኢትዮጵያ ወንዙን ብቻዬን ልጠቀምበት አላለችም። ቢቻል በጋራ አልምተን በጋራ እንጠቀምበት፤ ካልተቻለ ግን የመጠቀም መብቴ ላይ ማንም ከፊቴ ሊቆም አይገባም ነው የምትለው። ግብጾች አብረው መዋኘት አይችሉም፤ መስመጥ እንጂ። ዘመኑ ደግሞ አብሮ መዋኘትና ሻምፒዮን የሚኮንበት ነው። ይህ ግን ለግብጽ አይሠራም። ዛሬም ድረስ የቅኝ ግዛት ውልን ይዘው አደባባይ ይወጣሉ፤ ለድርድርም ይቀርባሉ። ይሄ ለግብጽ ሕዝብ ውርደት ነው። የቅኝ ግዛት ውልን ይዞ መብቴ ይከበርልኝ ማለት አገሪቷን ከቅኝ ግዛት ነፃ ለማውጣት በአንድም በሌላም ዋጋ የከፈሉ የአገሪቷን ባለውለታዎች ሁሉ መክዳትና ውለታቸውን አፈር ላይ መጣልም ነው። ስለሆነም ግብጽና ግብጻውያን ቅኝ ግዛት ትክክል ነው ከሚለው አቋማቸው ሊወጡ ይገባል።

# ከጉልበት ሠራተኛነት - የአውሮፕላን ባለቤትነት

ስሜነህ ደስታ

በቀድሞ አጠራሩ ኢሉባቦር ክፍለ ሀገር ሞቻ አውራጃ ቄቶ በሚባል ትንሽ መንደር ተወለዱ። በልጅነታቸው ለፈረንጆች (ለሚስዮናውያን) ለአውሮፕላን መነሻና ማረፊያ የሚውል ሜዳ በበሬ በማረስ ማስተካከል፤ በኋላም ተሻሽሎ በአካፋና በዶማ 20 ሜትር በ700 እና በ800 ሜትር መሬት ብቻቸውን ያስተካክሉ ነበር።ይህን ሥራ በልጅነት ዕድሜያቸው ሲከውኑ አብራሪ የመሆን ምኞት ተመኙ።ተመኝተው ብቻ አልቀሩም። የተለያዩ ተግዳሮቶች ቢያጋጥማቸውም የተመኙትን አውሮፕላን የማብረር ሙያ ተምረው አሜሪካ በሚገኝ አየር መንገድ ውስጥ ተቀጥረው አብራሪ ሆኑ።አብራሪ ከሆኑ በኋላ ምኞታቸውን ከፍ በማድረግ የአውሮፕላን ባለቤት ለመሆን ሌት ከቀን ለፉ።ምኞታቸውን እውን ለማድረግ ብዙ ውጣ ውረዶችን አሣለፉ።በመጨረሻም ኢትዮጵያ ውስጥ የግል አውሮፕላን ኦፕሬተር ማብረር ሠርተፍኬት አግኝተው በአንድ አውሮፕላን ሥራ ጀመሩ።የሥራ አድማሳቸውን በማስፋት የአቢሲኒያ የበረራ አገልግሎትና አቪዬሽን አካዳሚ በማቋቋም እስካሁን 150 የአውሮፕላን አብራሪ አሠልጥነው አስመርቀዋል።አሁን የ17 አውሮፕላን ባለቤት ናቸው።ካፒቴን ሰለሞን ግዛው ይባላሉ።ያለፉበት መንገድና ሥኬት ለወጣቶች አስተማሪነት ስላለው ከእሣቸው ጋር ቆይታ አድርገናል።መልካም ንባብ!



## ውልደትና ዕድገት

ካፒቴን ሰለሞን ግዛው በቀድሞ አጠራሩ ኢሉባቦር ክፍለ ሀገር ሞቻ አውራጃ (አሁን ደቡብ ክልል ሸካ ዞን ይባላል) ቄቶ በሚባል ትንሽ መንደር ነው የተወለዱት።እስከ አራተኛ ክፍል በተወለዱበት አካባቢ ከቤተሠባቸው ጋር ሆነው ተማሩ።ከአምስተኛ ክፍል ጀምሮ እስከ ሰባተኛ ክፍል ድረስ ማሻ፣ ጌጫ፣ እንደገና ማሻ እየተዘዋወሩ ተምረዋል።ከስምንት እስከ አሥራ አንደኛ ሚዛን ተፈሪ፣ ጎሬ እና ጅማ በመዘዋወር ተማሩ።በመሀል በዕድገት በሕብረት ዘመቻ ዘማች ሆነው በመሄዳቸው ትምህርት ተቋረጠ።ከዕድገት በሕብረት ዘመቻ እንደተመለሱ የሀገሪቷ ሁኔታ በተለይ ለወጣቶች በተረጋጋ ሕይወት ለመማርና ለመኖር አመቺ ሁኔታ ስላልነበረ ትምህርታቸውን ለማቆም ተገደዱ።፡

በልጅነታቸው እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ በክረምት ወቅት ከሠፈር ልጆች ጋር ተሰባስበው እግር ኳስ ይጫወታሉ፤ ፈረስ ይጋልቡም ነበር።መኪና እና አውሮፕላን ሣያዩ

> « 21 ዓመት ሠርቼ፣ ትናንሽ አውሮፕላኖች በመያዜ ትልቅ ነገር እንደሠራ ሰው ቃለ መጠይቅ እየተደረኩኝ ነው

ገመዶች የመጠላለፍ ዓይነት ጨዋታ ይወዱ ነበር።ከአምስተኛ ክፍል ጀምሮ ከቦታ ቦታ እየተንቀሳቀሱ መማራቸው ተቻችሎ መኖርን፣ ትዕዛዝ ማክበርን፣ ለፈለጉት ዓላማ ዋጋ መክፈልን፣ ወዘተ... ተለማምደውበታል።ማሻም ይሁን ጌጫ ሲማሩ ከወላጆቻቸው ተለይተው ነው።የኖሩባቸውን ዘመዶች የሚችሉትን ማንኛውንም ሥራ በመሥራት እያገዟቸው ነው የተማሩት።ከትምህርት መልስ ማታ... ማታ ባረፉበት የዘመድ ጠጅ ቤት ውስጥ ጠጅ በመቅዳት ያግዙ ነበር።የ13 ዓመት ልጅ ሆነው ሚዛን ተፈሪ ስምንተኛ ክፍልን ሲማሩም ከአንድ ልጅ ጋር አብረው በመኖር እንጀራ እየገዙ ሽሮ እየሠሩ ነበር የሚመገቡት።ብስክሌት ከሌሎች ተቀብለው ሃያ እና ሠላሳ ሣንቲም ለማግኘት ያከራዩ ነበር።

ሥራ ወዳዱና ታታሪው ሰለሞን በጎሬ ሚሽን ሆስቴል ውስጥ ወላጆቻቸው እየከፈሉላቸው ቢማሩም እሣቸው ግን በድርጅቱ ውስጥ እንደተቀጣሪ ሆነው ነበር የሚሠሩት።ፈረንጆቹን ያግዛሉ፣ ግቢውን ከማጽዳት እስከ መኪና ማጠብ ዓይነት ሥራዎችን በራሳቸው ተነሣሽነት ይሠሩም ነበር።የአውሮፕላን ማረፊያ ሜዳዎች 20 ሜትር በ700 እና በ800 ሜትር የሚሆን በበሬ በማረስ በኋላም ተሻሽሎ በዶማና በአካፋ ብቻቸውን ያስተካክሉ ነበር።የዚያን ጊዜ ከአውሮፕላን ጋር መተዋወቃቸው አሁን ላሉበት የሙያ ዘርፍ ውስጥ ለመግባት ሙሉ ለሙሉ በሩን ከፍቶላቸዋል።ሕልማቸውን ሁሉ በዚያ ዙሪያ እንዲያደርጉ አድርጓቸዋል።ጅማ አሥራ አንደኛ ክፍልን ሲማሩ ለተለያዩ ሚሰዮን ጣቢያዎች ዕቃዎችን እየገዙ የመላክ ሥራ ይሠሩ ነበር፤ ለዚህም ተግባራቸው ይከፈላቸው ነበር።ባገኙት ገንዘብ ብስክሌት ገዝተው ከጓደኞቻቸው ጋር ይጠቀሙበት ነበር እንጂ ለአልባሌ ጉዳይ አያውሉም።ኮሌጅ ካገኙት እውቀት ባልተናነሰ ከእነዚያ ቦታዎች ያገኙት ተመክሮ ብዙ አስተምሮኛል ብለው ያስባሉ።

አሥራ አንደኛ ክፍል ሳሉ የደርግ ሥርዓት መጥቶ የዕድገት በሕብረት ዘመቻ ታወጀ።ከዘመቻው መልስ ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ ያለው ፖለቲካዊ ሁኔታ አዳጋች ሆነባቸው።በወቅቱ በሀገር ደረጃ ትልቁ ነገር ላለመሞት ትግል ይደረግ ስለነበረ ለዚህ ትግል እንዲረዳቸው ቴፒ ይኖሩ የነበሩ እናታቸው የአንገት ሐብላቸውን ሸጠው እንዲጠቀሙበት በፖስታ አድርገው ልከውላቸዋል።ከዚያም አዲስ አበባ መጥተው ገነት ሆቴል አጠገብ ጋሽ ብሩ የሚባሉ ሰው ጋራዥ መሥራት ጀመሩ።ጋሽ ብሩም የሥራ ትጋታቸውንና ታማኝነታቸውን በማየት እምነት ሲጥሉባቸው ታክሲ እንዲነዱ መኪና ሰጧቸው።ታክሲ እየሠሩ ሕይወታቸውን በመምራት ላይ ሳሉ አዲስ አበባ ያለው ሁኔታ ደስ አልል ሲላቸው ሻሸመኔ ወንድማቸው ዘንድ ለመኖር ሄዱ።እዚያም የመኪና ሹፌር ሆነው ተቀጥረው ከሻሸመኔ ወንዶ



**በ**ነጭ ፓይለቶችና ሌሎች የሥራ ባልደረቦቻቸው «እንዴት ለአንድ ጥቁር፣ አፍሪካዊ አውሮፕላን ይሰጣል? እሱ ምን ስለሆነ ነው?» በሚል የቅናትና የምቀኝነት ጦርነት ተከፈተባቸው



ገነት፤ ከሻሸመኔ ደብረዘይት ሠሩ።በዚህ ጊዜ አሥራ ሁለተኛ ክፍልን የማታ ተማሩ።በኢህአፓ ወይም በሌላ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ላለመግባት ወስነው እንዲሁም በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ሣይገቡ በሕይወት ኖሮ ለመቀጠል ሲሉ ወደ ሦስት ዓመት አካባቢ ከትምህርት ውጭ ሆነው የተለያዩ ሥራዎች ሠርተዋል፡፡

## ሥደት

ቀደም ሲል የሚያውቋቸውን በወቅቱ አሜሪካ የነበሩትን ሚሲዮናውያንን ወደ ውጭ እንዲወስዷቸው ጠይቀው ፈቃደኛ ቢሆኑላቸውም ሀገር ውስጥ ያለው ሂደት ወደ ሦስት ዓመት አካባቢ ጊዜ ፈጅቶ መጋቢት 1972 ዓ.ም ተሳክቶ ወደ አሜሪካ ሄዱ።እዚያም ሄደው ሚስዮኖቹ ዘንድ ቆይተው መስከረም ላይ ስኮላርሽፕ አግኝተው ትምህርት ጀመሩ።የመጀመሪያውን አንድ ዓመት ስኮላርሽፕ በመጠቀም ተማሩ።ሚስዮናውያኑ እሳቸውን ለማስተማር ገንዘብ ከተለያዩ ቦታዎች እያፈላለጉ እየከፈሉ እንደሚያስተምሯቸው በመረዳት ‹‹መሥራት እችላለሁ፤ ስለዚህ ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ ሠርቼ ራሴን ማስተማር አለብኝ›› በማለት ወሰሡኑ።ኮሌጅ ውስጥ ሠሀን ማጠብ፣ ምግብ ማቅረብ፣ ሣር ማጨድ የመሣሰሉ ሥራዎችን በመሥራት ትምህርታቸውን እስኪጨርሱ ገንዘብ በመክፈል ተምረዋል።በተጨማሪም አንድ ቦታ ሁለት ሠዓት፣ ሌላ ቦታ አራት ሠዓት፣ እንደገና ሌላ ቦታ ስምንት ሠዓት የትርፍ ጊዜ ሥራ በመሥራት ቅዳሜና እሁድ ሕልምና ምኞታቸው የነበረውን አውሮፕላን የማብረር ትምህርት ከፍለው በመማር የሥነ መለኮትና የቢዝነስ ትምህርታቸውን ከመጨረሳቸው በፊት አጠናቀዋል።የጀመሩትንም ትምህርት አጠናቀው

**የ17 የተለያዩ አውሮፕላኖች ባለቤት ናቸው።የአገልግሎት አድማሣቸውን በማስፋት ከአራት የበረራ ሙያተኛ ከማሥመረቅ ተነስተው እስከ አሁን ከ150 በላይ ፕሮፌሽናል ፓይለቶችን አሥመርቀዋል**

የመጀመሪያ ዲግሪ አግኝተዋል።ከዚህ በኋላ ደግሞ ተፈላጊነታቸውን ለማስፋት በማሰብ አውቶብስ በመንዳት፣ ፋብሪካ ውስጥ የተለያዩ ሥራዎች በመሥራት በሚከፈላቸው ገንዘብ የአውሮፕላን ጥገና ትምህርት ከፍለው ተምረዋል።

## አውሮፕላን ማብረር

የአውሮፕላን ጥገና ትምህርቱን ካጠናቀቁ በኋላ አሜሪካ በሚገኝ አየር መንገድ ውስጥ አውሮፕላን የማብረር ሥራ መሥራት ጀመሩ።በመቀጠል በልጅነታቸው ያዩት የነበረውን በሽተኞችን የመርዳትና የዕርዳታ በረራዎችን ሥራ ለመሥራት ቀደም ሲል ኢትዮጵያ የጉልበት ሥራ ይሠሩበት የነበረው የበረራ ድርጅት ውስጥ በአብራሪነት እንዲቀጥሯቸው አመለከቱ።በድርጅቱ ለመቀጠር አውሮፕላን ማብረርና መጠገን እንደመሥፈርትነት ይቀመጥ ነበር፤ ባላቸው ብቃት ብዙ ፈረንጆችን በልጠው በመመረጣቸው ድርጅቱ ተቀብሏቸው መጀመሪያ ሃይቲ፣ በመቀጠል ዑጋንዳ ተልከው ሠርተዋል።በመጨረሻ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ያላቸው ፍላጎት ተሣክቶ በ1989 ዓ.ም በሚሠሩበት አየር መንገድ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ።በዚህም ሁለት ዓመት አካባቢ እንደሠሩ ድርጅቱ ከሀገር እንዲወጣ ስለተጠየቀ ወጣ።ለካፒቴን ሰለሞን ሌሎች ሦስት ሀገሮች ሄደው እንዲሠሩ በድርጅቱ እንደ አማራጭ ዕድሉ ቢሰጣቸውም እሣቸው ግን ከኢትዮጵያ መውጣት ስላልፈለጉ አልተቀበሉትም፡፡


## የግል አውሮፕላን ባለቤት

የሚሠሩበት ድርጅት ከኢትዮጵያ ሲወጣ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ጀመሩ።ዑጋንዳ ለሥራ ከሄዱበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት በጣም ይፈልጉ ነበር።ሀገሬ ሄጄ አንድ ቀን የግል

አውሮፕላን ቢኖረኝ እያሉ ይመኙ ነበር።ወደ ኢትዮጵያ ለበረራ ሥራ መጥተው በሚሠሩበት ጊዜ በበረራ ውስጥ ያሉ ክፍተቶችን ለመመልከት ዕድል ተፈጠረላቸው።እነዚህን ክፍተቶች ከሞላ ጎደል ይሠሩበት የነበረው ድርጅት ይሸፍን ነበር።ድርጅቱ ሲወጣ ክፍተቶችን መሙላት ያስፈልግ ነበር።እሣቸው አውሮፕላን ያበራሉ፤ የጥገና አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፤ ያሉት ሀገራቸው ላይ ነው፤ ፍላጎቱ አላቸው።ታዲያ ‹‹ለምንድን ነው ራሴ ይህን ክፍተት የማልሞላው›› ብለው አሰቡ።99 በመቶ ችግሩ አውሮፕላን የላቸውም፤ የሚያገኙበትንም መንገድ አያውቁም።ከኢትዮጵያ የተባረረው ድርጅት ውስጥ 11 ዓመታት አገልግለዋል።ሥራቸውን ስለሚያደንቁ በየዓመቱ የማበረታቻ ሽልማት ተሸልመዋል።በግል የአውሮፕላን ማብረር ሥራ በኢትዮጵያ ለማቋቋም ሐሳቡ እንዳላቸው ድርጅቱን ሲያማክሩ ‹‹ፈቃድ ካገኘህ አውሮፕላን እንሰጥሃለን›› ተባሉ።በማይታመን መልኩ በሦስት ወር ውስጥ ፈቃዱን አወጡ።ለዚህም በወቅቱ የነበረው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን መሥሪያ ቤትን አሁንም ወደፊትም በሕይወቴ እስካለሁ ድረስ አመሠግነዋለሁ ይላሉ።እሣቸው እንደሚሉት የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ከመንገዱ ወጥቶ ፎርም እንደዚህ ነው የሚሞላው፣ ይኼን እንደዚህ አድርግ፣ ይኼን በዚህ መልኩ አስተካክል ብሎ እጃቸውን ይዞ መንገዱን መራቸው።

ፍቃዱ ከተገኘ በኋላ አውሮፕላን የሚሰጧቸውን ሥርዓት ባለው ሁኔታ ማነጋገር ጀመሩ።አውሮፕላን ለማግኘት ባደረጉት እንቅስቃሴ ውስጥ በሕይወታቸው ትልቁ ተግዳሮትን ተጋፈጡ።ቀደም ሲል እንደብርቅ የሚያዩዋቸው፣ የሚያደንቋቸውና የሚያከብሯቸው ነጭ ፓይለቶችና ሌሎች የሥራ ባልደረቦቻቸው ‹‹እንዴት ለአንድ ጥቁር፣ አፍሪካዊ አውሮፕላን ይሰጣል? እሱ ምን ስለሆነ ነው?›› በሚል የቅናትና የምቀኝነት ጦርነት ተከፈተባቸው።በዚህም ሣቢያ አውሮፕላን ለማግኘት ግፋ ቢል ሁለት ወር ይፈጃል የተባለው ሂደት ስምንት ወር ገደማ ፈጅቶ ተጠናቀቀ።በሰባት ዓመት ተከፍሎ በሚያልቅ ብድር ውል ገብተው አሜሪካ ሥሪት የሆነ ሴሲና ካራቫን የሚባል ከ10 እስከ 12 ሰዎች የሚይዝ አውሮፕላን አዲስ አበባ በ1992 ዓ.ም አመጡ።

ውሉ በጣም አሣሪ ነበር፤ አሣሪነቱና የማያንቀሳቅስ መሆኑ ግን አላስከፋቸውም።እሥሩን ለመፍታት ሲሉ ተግተው መሥራት እንዳለባቸው ተገንዝበው በመተግበራቸው በሰባት ዓመት ማለቅ ያለበትን ብድር በአራት ዓመት ተኩል ከፍለው ዕዳቸውን አጠናቀቁ።በመሃል ሌሎች አውሮፕላኖችንም በብድር ገዙ።አሁን አቢሲኒያ በረራ አገልግሎትና አቪዬሽን አካዳሚ የሚል ድርጅት በመክፈት ከፍተኛው እስከ አሥራ አራት ሰዎች የሚይዝ የ17 የተለያዩ አውሮፕላኖች ባለቤት ናቸው። የአገልግሎት አድማሣቸውን በማስፋት ከአራት



የበረራ ሙያተኛ ከማሠመረቅ ተነስተው እስከ አሁን ከ150 በላይ ፕሮፌሽናል ፓይለቶችን አሥመርቀዋል። አብዛኞቹ ተመራቂዎች ኢትዮጵያውያን ይሁኑ እንጂ የውጭ አገር ዜግነት ያላቸውን ባለሙያዎች አሠልጥነው አሥመርቀዋል።የሱዳን፣ የሩዋንዳ፣ የየመን፣ የዩክሬን፣ የደቡብ ሱዳን፣ የአሜሪካ እና የሌሎች አገራት ዜግነት ያላቸውን ተማሪዎች አሠልጥነዋል። በአሁኑ ወቅት ወደ ሃምሣ የሚጠጉ ተማሪዎችን በአብራሪነት ሙያ እያሠለጠኑ ይገኛሉ፡፡

ከጉልበት ሥራ ተነስተው የ17 አውሮፕን ባለቤት መሆን ትልቅ ሥኬት መሆኑ አያጠራጥርም።እሣቸው ግን በዚህ አይረኩም።አሁን ላይ ሆነው የደረሱበትን ደረጃ ሲመለከቱ ሊያደርጉት ከሚያስቡትና መድረስ ከሚገባቸው ጋር ሲያወዳድሩ 20 በመቶ ወይም 25 በመቶ እንኳን አልሠራሁም ባይ ናቸው።በአሁን ጊዜ አሥር፣ አሥራ ሁለት እና አሥራ አራት ሰዎች የሚይዙ አውሮፕላኖች ብቻ ሣይሆን ቦይንግ አውሮፕላኖች ሊኖሩን ይገባ እንደነበር ያስባሉ።ካለው ገበያ፣ ካለው የሰው ኃይል፣ ሀገራችን ካላት መልክዓ ምድር አንጻር

ትልቅ ነገር መሥራት ይቻል እንደነበር ይቆጫሉ።

በሚገባቸው ልክ እንዳይሠሩ እጅና እግራቸውን አሥሮ የያዘው የጣሪያ መከለያ ያለው የአውሮፕላን መጠገኛ ቦታ (ሐንገር) አለማግኘታቸው ነው።ይህንን ለማግኘት ከአሥራ ስምንት ዓመት በላይ ጥረት አድርገው ሊያገኙ አልቻሉም።ጥገና ለማድረግ መካኒክ፣ መፍቻና ሌሎች ዕቃዎችን ይዘው የጣሪያ መከለያ ያለው ቦታ ለማግኘት ብቻ ኬንያ ድረስ ይሄዳሉ።ይህንን አገልግሎት ለማግኘት ብቻ አውሮፕላን ይዞ ሲኬድና ሲመጣ የነዳጅ ወጪ፣ የሠራተኞች አበል፣ የጣሪያ አገልግሎት(ሐንገር) ክፍያ ወዘተ... የአቢሲኒያ ኪሣራ ብቻ ሣይሆን የሀገርም ኪሣራ ነው።ለአንድ አውሮፕላን ሀገር ውስጥ ቢሆን በሁለት ሺህ ዶላር መጠገን የሚቻለውን ናይሮቢ በመሄድ እስከ 20 ሺህ ዶላር ያወጣሉ።ለ17 አውሮፕላኖች በተለያዩ ጊዜያት የወጡ ወጪዎች ሌሎች አውሮፕላኖችን አስመጥቶ ቢያንስ ከ50 እስከ 80 ለሚደርሱ ፕሮፌሽናል ኢትዮጵያዊ ሠራተኞች የሥራ ዕድል መክፈት ይቻል ነበር።ለመንግሥትም ተጨማሪ ታክስ በመክፈል ሀገር ትጠቀም ነበር።አሁን ካሉበት ደረጃ ከፍ ባለ መልኩ ወጣቶች በዚህ ዘርፍ ቢሰለጥኑ ፕሮፌሽናሎች ሆነው ሀገር ውስጥም ሆነ በሌላው ሀገር በመሄድ ሠርተው ራሳቸውን የመጥቀም ዕድል ይፈጠርላቸዋል።ከስድስት ወር ወዲህ በትራንስፖርት ሚንስትሯ በኩል እየተሠሩ ያሉ አበረታች የሆኑ ጅምሮች እንዳሉ ካፒቴን ሰለሞን ይገልፃሉ።እነዚህ ጅምሮች ተጠናክረው ተግባራዊ ውጤት እንደሚያሣዩ ትልቅ ተሥፋ ሠንቀዋል፡፡

«መንግሥት አሁን በያዘው አቅጣጫ የሚቀጥል ከሆነ ከግሉ የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ጋር ቀርቦ ዘርፉ የበለጠ የሚያድግበትን ሁኔታ የሚመካከርና ስለ ሀገር ጥቅም የሚወያይ ከሆነ ብዙ ሥራ መሥራት ይቻላል።በእኛም ሆነ በሌሎች ድርጅቶች አራትና አምስት ትምህርት ቤቶች ተከፍተው በፋብሪካ ደረጃ የአቪዬሽን ባለሙያዎች ማሠልጠን ይቻላል።ከአብራሪዎች በተጨማሪ የአቪዬሽን አስተናጋጅ፣ መካኒክ፣ አካውንታት፣ የሕግ ባለሙያ፣ ወዘተ... በሚል ወጣቶችን ብናሰለጥን ፕሮፌሽናሎች ስለሆኑ ሀገር ውስጥም ሆነ በመላው ዓለም ተለምነው የሚሠሩበት ሁኔታ መፍጠር ይቻላል።እኛ በአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ ተግዳሮቶችን ተቋቁመን 21 ዓመት በመቀጠል "ይቻላል!" የሚለውን መንፈስ በተግባር ለማሣየት ሞክረናል።ቢዝነሱን በማየት ሠፊቱን ብቻ ልብላ ከተባለ አቪዬሽን በጣም አስቸጋሪ ነው።በፍቅርና በፍላጎት ተነሣስቶ መሥራት ያስፈልጋል።ልክ ልጅ እንደማሣደግ ዓይነት ሁኔታ ይፈልጋል።ያለበለዚያ በአቪዬሽን ሥራ መዝለቅ አዳጋች ይሆናል።በመንግሥት በኩል ወይዘሮ ዳግማዊት ሞገስ የትራንስፖርት ሚኒስትር ከሆኑ በኋላ ለአቪዬሽን ኢንዱስትሪው ትኩረት ተሠጥቶት እየታሠበ ያለውና ወደ ተግባር ለመግባት ያለው ተነሣሽነትና እንቅስቃሴ

> **ኬንያ ከትናንሽ አውሮፕላን ጀምሮ እስከ ትላልቅ ያላቸው ከ80 በላይ ድርጅቶች አሉ። እኛ ከዚያ በላይ ሊኖረን የሚችልበት ሁኔታ አለ። ይህ ምኞት ሣይሆን አስቻይ ሁኔታዎች ስላሉ ነው**

እጅግ የሚበረታታ ነው።ሠፋ ባለ መልኩ ለሀገር ጠቀሜታ እንዲኖረው በጠቅላይ ሚኒስትር ደረጃ የአቪዬሽን አማካሪ ያስፈልጋል፤ ምክር ቤት ያስፈልጋል።በአፍሪካ ደረጃ ብቻ ሣይሆን በዓለም ደረጃ ከፍተኛውን ሥፍራ ለመያዝ የሚያስችል ቁመና አለን።ያለን ብቃት እዚያ ድረስ ነው» በማለት መንግሥት ቀረብ ብሎ በመነጋገርና በመመካከር የግል አቪዬሽን ዘርፉን ከፍተት የመደገፍ ሚናውን ሊወጣ እንደሚገባ አሣስበዋል።

## አቢሲኒያ

ካፒቴን ሰለሞን አቢሲኒያ በረራ አገልግሎትና አቪዬሽን አካዳሚን ከሌሎች አገራት መሠል ተቋማት ጋር ሲያወዳድሩት አቢሲኒያ በጣም በሚያሣፍር ደረጃ ላይ እንዳለ ይገልፃሉ።ይህንንም ለማለት ያስደፈራቸው ምክንያት አላቸው።የዛሬ አሥራ ሁለት ዓመት ገደማ አንድ ትንሽ አውሮፕላን ገዝቶ ታንዛንያ ውስጥ የበረራ አገልግሎት ይሰጥ የነበረ ታንዛንያዊ ጓደኛቸው ትንንሹን ትተን አሁን 30 እና 40 ሰዎች የሚይዙ ትላልቅ አውሮፕላኖች አሉት።«21 ዓመት ሠርቼ፣ ትናንሽ አውሮፕላኖች በመያዜ ትልቅ ነገር እንደሠራ ሰው ቃለ መጠይቅ እየተደረጉኝ ነው።እንደ አቢሲኒያ ብቻ ሣይሆን እንደ ሀገር ሊያሣፍረን ይገባል።ኢትዮጵያውያን ነበርን አፍሪካ ውስጥ የበላይነቱን መውሰድ የነበረብን።ከፈረንጆቹ ጋር ብዙም አንራራቅም 80 ዓመት የሚጠጋ የአቪዬሽን ልምድ አለን» በማለት እንደ ግል የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ መድረስ የሚገባን ደረጃ አለመድረሣችን ግን ያስቆጫቸዋል።

## የአመራር ሥልት

ካፒቴን ሰለሞን አቢሲኒያ ውስጥ የሥራ ባልደረባ እንጂ ሠራተኛ የለም የሚል እምነት አላቸው።ለእሣቸው ከሥራ ኃላፊና ፓይለት፣ ከፓይለትና መካኒክ እንዲሁም ከቢሮና ከጽዳት ሠራተኛ መካከል ልዩነት የለም።ሁሉም እንደ አንድ ሠንሠለት ተያይዞ ካልሄደ የሆነ ቦታ ላይ ችግር ካለ ድርጅቱ ሊቀጥል ስለማይችልና ጉዳት ስለሚኖረው የሥራ ባልደረብነት እንጂ የአለቃና ምንዝር ሥርዓት የለም ባይ ናቸው።ይህም ውጤት እንዳመጣላቸው ያስረዳሉ።

## ማህበራዊ ተሣትፎ

ስለማህበራዊ ተሣትፏቸው ተጠይቀው ሲመልሱ፤ «ታዋቂ የሆኑ ሰዎች ማህበራዊ ተሣትፏቸውን ለማሣየት ለተቸገሩ ልብስም ሆነ ገንዘብ ሲሰጡ የሚያሣይ በፌስ ቡክ (በማህበራዊ መገናኛ ብዙሃን) ላይ ሲለቁ በማይበት ጊዜ አዝናለሁ።ይህን የሚመስል ተግባር ማድረግ አልፈልግም፤ የምችለውን በአቅሜ ደረጃ አደርጋለሁ።አፌን ሞልቼ የምናገረው ግን በታላቁ ሕዳሴ ግድብ ዙሪያ ማድረግ የምችለውን ነገር ሁሉ በተሣትፎም ይሁን በገንዘብ አደርጋለሁ።ከጊዜ ማነስና ከሌሎች ሁኔታዎች አንጻር በምችለው ሙያ በሹፌርነት አንድ ሁለት ሣምንት ግድቡ የሚገነባበት ቦታ ቆይቼ ገልባጭ መኪና በመንዳት መርዳት አለመቻሌና በዚህ መስክ አለመሣተፌ ይቆጨኛል» በማለት ስለማህበራዊ

ተሣትፏቸው ብዙ ማውራት እንደማይፈልጉ ገልፀዋል።ስለ ማህበራዊ ተሣትፏቸው ለመግለጽ ፍቃደኛ ባይሆኑም በግልጽ ከሚታዩት ውስጥ ለመጥቀስ ያህል በሀይማኖት ሥም የሚነግዱና የሚያጭበረብሩ የሐሰተኛ አገልጋዮችን የአመጽ አካሄድ የሚያመላክትና የሚኮንን መዝሙር ደርሰው በምሥል በማስደገፍ ሠሚ ጆሮና ተመልካች ዓይን ላላቸው አገልጋዮችና ምዕመናን አበርክተዋል፡፡

የሕይወት ፍልሥፍናቸው "የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው" የሚለው እንደሆነ የሚያስረዱት እንግዳችን በጣም የምወዳትና ጓደኛ የሆነችኝ ባለቤት አለችኝ ይላሉ።የአራት ወንድና የሁለት ሴት ልጆች አባት ናቸው። ለሰው እንዲገባው ነው እንጂ ልጆቼ ጓደኞቼ ናቸው ይላሉ። ልጆቼ እግዚአብሔርን ፈርተው ሰውን አክብረው እንዲኖሩ ነው የምፈልገው፤ ይህንን በተግባር እንዲያሣዩ እያደረኩ ነው የማሣድጋቸው በማለት ስለአስተዳደግ ሥልታቸው ይገልጻሉ።

### ምሥክርነት

ካፒቴን አማረ ገብረሃና የአቢሲኒያ በረራ አገልግሎትና አቪዬሽን አካዳሚ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ናቸው።ቀደም ሲል የኢትዮጵያ አየር ኃይል ባልደረባ የነበሩና እስከ ሙሉ ኮሎኔል ማዕረግ የደረሱ ናቸው።ከአየር ኃይል በተጨማሪ በኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ አስተማሪ ሆነው ከመሥራታቸው ባሻገር በሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን መሥሪያ ቤትም ሠርተዋል።እስካሁን ወደ 60 ዓመት በአቪዬሽን ውስጥ የሥራ ልምድ አላቸው።ካፒቴን ሰለሞንን የሚያውቋቸው ከ21 ዓመት በፊት በኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የበረራ ደህንነት ኃላፊ ሆነው ሲሠሩ ነበር።ስለካፒቴን ሰለሞን የሚያውቁትን ሲናገሩ «ካፒቴን ሰለሞን ግዛውን ሣውቀው የግሉ የአቪዬሽን ዘርፍ ተሣትፎ ለብዙ ጊዜ ደካማ ሆኖ የቆየበት ሁኔታ ነበር።ሥራውን ለመጀመር ሲነሳ ምንም ዓይነት የግሉ ዘርፍ ተሣትፎ አልነበረም።የግሉን ዘርፍ እንደገና ለማበረታታት አንዳንድ እንቅስቃሴዎች በሚደረጉበት ወቅት ካፒቴን ሰለሞን ግንባር ቀደም ሆኖ መጣ።መጠነኛ መበረታታት ተደርጎለት ፍቃድ አግኝቶ አንድ አውሮፕላን ይዞ መጥቶ ራሱ እያበረረ አንድ ቴክኒሻንና አንድ የቢሮ ሠራተኛ ይዞ በመጀመር በሂደት የ17 አውሮፕላን ባለቤት እንዲሁም ከ100 በላይ ሠራተኞች የሚሠሩበት ድርጅት አድርጓል።ለአቪዬሽን ባለው ቅርበትና ፍላጎት በየጊዜው የተፈጠሩትን ተግዳሮቶች እየተቋቋመ በእሱ ከፍተኛ ጥረት በግሉ ዘርፍ የተለያዩ አስተዋጽኦ ማድረጉና ምሣሌ ሆኖ የሚታይ ድርጅት በመያዝ እዚህ ደረጃ መድረሱ ቀላል አይደለም።ካሉ ተግዳሮቶች የተነሣ ማደግ የሚገባውን ያህል ደረጃ ግን አላደገም።የአመራር ሥልቱን በተመለከተ በአለቃና በሠራተኛ መካከል እንዳለ ግንኙነት ሣይሆን እንደቤተሠብ ነው የሚይዘው፤ አሣታፊ የሆነ የአመራር ሥልት ይከተላል።ውጤት የሚገኘው በሠራተኛው ነው ብሎ ስለሚያምን ሠራተኞችን ማዕከል አድርጎ ሁሉንም በእኩል ዓይን በማየት ያከብራል።በኮቪድ 19 በሽታ ምክንያት ድርጅቱ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ሲገባ ሠራተኛው ሣይፈናቀል እንዴት መቀጠል ይችላል? የሚለውን ለመመለስ በከፍተኛ ሁኔታ ይዞ ሲንቀሳቀስ ሁላችንም በተግባር የምናየው ነው።ፈሪሐ እግዚአብሔር የሆነ ባህሪ ስላለው ሰው በጣም መርዳት ይፈልጋል።ስፖንሰር እየሆነ በነጻ ያሥተምራል፤ እኛ ክርክር የምንፈጥርበት ጊዜ አለ።እሱ ግን ‹በጎነት ይከፍላል› በሚል የሚያደርጋቸው ብዙ ነገሮች አሉ።በተለያየ ምክንያት ከበረራ ሙያቸውም ሆነ ከቴክኒሻንነት የተገለሉትን መልሶ አሠልጥኖ ወደነበሩበት ደረጃ አድርሶ በድርጅቱ ተቀጥረው ሙያቸውን የቀጠሉበት ሁኔታ አለ» በማለት ምሥክርነታቸውን ሠጥተዋል።

> **ፍላጎቱና ዓላማው ያላቸው የተለያዩ ተግዳሮቶች ቢገጥማቸውም ተሥፋ እንዳይቆርጡ፤ ነገ የተሻለ ጊዜና ዕድል ስለሚመጣ ዓላማቸውን ማሣካት እንደሚችሉ ተሥፋ እንዲያደርጉ ነው**

### ምክር ለወጣቶች

ለወጣቶች ይበጃል የሚሉትን ምክር አጽንኦት ሠጥተው ሲለግሱ፤ ለማብረር ፍላጎቱ ያላቸውን ወጣቶች የምመክረው ከፍላጎት በተጨማሪ ዓላማ ሊኖራቸው ይገባል። ፍላጎቱና ዓላማው ያላቸው የተለያዩ ተግዳሮቶች ቢገጥማቸውም ተሥፋ እንዳይቆርጡ፤ ነገ የተሻለ ጊዜና ዕድል ስለሚመጣ ዓላማቸውን ማሣካት እንደሚችሉ ተሥፋ እንዲያደርጉ ነው። ኬንያ ከትናንሽ አውሮፕላን ጀምሮ እስከ ትላልቅ ያላቸው ከ80 በላይ ድርጅቶች አሉ።እኛ ከዚያ በላይ ሊኖረን የሚችልበት ሁኔታ አለ።ይህ ምኞት ሣይሆን አስቻይ ሁኔታዎች ስላሉ ነው።በማብረር ሙያ ላይ ለሚገኙ ወጣቶች ደግሞ ሙያው አለሁ - አለሁ፣ ልታይ...ልታይ የሚባልበት ሣይሆን አብራሪነት የአገልግሎት መሥጫ መሣሪያ መሆኑን ተገንዝበው ሙያቸውን አክብረውና አስከብረው እንዲይዙ እመክራለሁ።ለኢትዮጵያ ወጣቶች አሁን ባለው ሁኔታ ምክር መስጠት በጣም ከባድ ነው።ወጣቶች በሙሉ ዘመኑን መዋጀት አለባቸው፤ ጊዜውን ማገናዘብ ይገባቸዋል።የራሣቸውን ሞሠብ ጠራርገው በልተው ጨርሰው የዚህን ዘመን ወጣት ትውልድ ሞሠብ ለራሣቸው የፓለቲካ ጥቅም ሲሉ የወጣቱን ደም እያጣቀሱ ለመብላት የሚፈልጉ ሰዎች አሉ።ወጣቱ ቆም ብሎ ማሠብና ለምን? ብሎ መጠየቅ እንዲሁም ነቅቶ ራሱን መጠበቅ ይኖርበታል።ከዚህ በተጨማሪ ወጣቱ ሀይማኖትን ሽፋን አድርገው ሀይማኖቱ ከሚፈቅደው ሥርዓት ውጭ ለግላቸው ጥቅም ብለው ከሚያጭበረብሩ፣ ከሚነግዱ፣ ከሚሠርቁ እንዲሁም ወጣቱ ሥራ እንዳይሠራና እንዲሠንፍ ብሎም የሀገር ፍቅር እንዳይኖረው ከሚያደርጉ አካላት አርቆ ራሱን መጠበቅ አለበት።በቲቮዞና በቡድን ማሠብን ማቆም አለበት።ወጣቱ በነገሮች ሁሉ ማማረር ሣይሆን በሚችለው አስተዋጽኦ አድርጎ ራሱንና ሀገርንም ሊጠቅም የሚችል ተግባር መፈፀም ይጠበቅበታል› በማለት አሣስበዋል፡፡

## ናፖሊዮን ሂል ዲያቢሎስን ማታለል (Outwitting the Devil) በሚለው መፅሃፉ

ከዲያቢሎስ ጋር ምናባዊ ቃለ ምልልስ አድርጎ ዲያቢሎስ የሚጠቀማቸውን ስልቶች እና እነሱን ለማሸነፍ መፍትሄዎቹን ከራሱ ከዲያቢሎስ አግኝቷል። እንዳናደርግ፣ እንዳንደሰት እና እንዳይሳካልን ዲያቢሎስ የሚያደርጋቸውን ድርጊቶች ለማግታት ብዙ መፍትሄ ጠይቆ ተረድቷል። ከመፍትሄዎቹ መካከልም ሰባቱ መንፈሳዊ፣ አዕምሯዊ እና አካላዊ ነጻነትን የምንቀዳጅባቸው ህግጋቶች:-

1) አላማዊ ፅናት
2) እራስን መግዛት
3) ከችግሮች መማር
4) በዙሪያችን ያሉ ተፅዕኖ ፈጣሪ ነገሮች መቆጣጠር
5) ጊዜን ለአወንታዊ ነገሮች እንጅ ለአሉታዊ ነገሮች አለመጠቀም
6) ከእሳቤዎቻችን ጋር ስምምነት የሚፈጥር ሁኔታዎችን ማመቻቸት
7) ለማድረግ ከመወሰናችን ቀድመን ስለ እቅዶቻችን ማሰብ

**ሳከማርያም (ዶ/ር)**

# ፈገግታ የሚያጭር ቃለ መጠይቅ
## (ከብቅየ የኢቲቪ ፕሮግራም ላይ የተወሰደ)

ገጠር ላይ ነውና ላንዱ ገበሬ ቃለ መጠይቅ እየተደረገለት ነው.......

ጋዜጠኛ፡- ከብቶቹ ስንት ሊትር ይታለባሉ?
ገበሬ፡- የትኛዋ ጥቁሯ? ወይስ ነጯ?
ጋዜጠኛ፡- ነጯ
ገበሬ፡- በቀን 2 ሊትር
ጋዜጠኛ፥ ጥቁሯስ?
ገበሬ፡- በቀን 2 ሊትር
ጋዜጠኛ፡- ( ትንሽ ግራ ገባውና ) እእእ የምታበላቸው ምንድነው?
ገበሬ፡- ነጯን? ወይስ ጥቁሯን?
ጋዜጠኛ፡- ጥቁሯን
ገበሬ፡- ሳር ነው የማበላት
ጋዜጠኛ፡- ነጯንስ
ገበሬ፡- ሳር
ጋዜጠኛ፡- በጣም ተናደደና ለተመሳሳይ መልስ ለምንድነው? "የትኛዋን" እያልክ ተመሳሳይ መልስ የምትሰጠኝ?
ገበሬ፡- ምክንያቱም ጥቁሯ የኔ ስለሆነች፡፡
ጋዜጠኛ፡- Oh! ነጯስ?
ገበሬ፡- እሷም የኔው ናት።

"የሰው ልጅ የሚፈልገውን ማድረግ ይችላል ነገር ግን የሚፈልገውን መፈለግ አይችልም።

" ጋብቻ ማለት የራስን መብት መግመስና ግዴታን በሁለት እጥፍ ማሳደግ ነው።

" የሰው ልጅ ደስታ ሁለት ጠላቶች አሉት እነሱም ህመምና ድብርት።

"ችሎታ ማንም ሰው መምታት ያቃተውን ኢላማ ይመታል ፤ጥበብ ግን ማንም ሰው ያላየውን ኢላማ ይመታል።

**ከሾፐናወር**

## ህልፈታቸው በወርሃ የካቲት የሆነ አንጋፋ የሀገራችን የሥነ-ፅሑፍ ሰዎች

1, የካቲት 2 ቀን 1972 ዓ.ም ደራሲ አቤ ጉበኛ በወል ባልታወቀ ምክንያት አስፓልት ላይ ወድቆ ተገኘ። ሕይወቱ አለፈ። "ከመቅሰፍት ሠራዊት ይጠንቀቅ ሰውነት" እና "መስኮት" የተባሉ የግጥም መጻሕፍት፤ "ቂመኛው ባህታዊ"፣ "የራሄል ዕንባ" እና "ፖለቲካና ፖለቲከኞች" የተሰኙ ተውኔቶች፤ "የአመፅ ኑዛዜ"፣ "አልወለድም"፣ "አንድ ለናቱ"፣ "ጎብላንድ አጭበርባሪዋ ጦጣ"፣ "መልክአም ሰይፈ ነበልባል"፣ "ዕድል? ነው በደል?"፣ "የፍጡራን ኑሮ" የተባሉ ልቦለዶችና አስተኔ-ልቦለዶች፤ እንዲሁም በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በእንግሊዝኛ ተጽፎ የታተመው "The Savage girl" ደራሲ ነው - አቤ ጉበኛ።

2, የካቲት 11 ቀን 2004 ዓ.ም ስብሐት ገብረእግዚአብሔር ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። ከ"ሰባተኛው መልአክ" አንድ መንክር አንቀጽ እንቆንጥር፡

"ብስጭትጭት ብለህ ተስፋ ቆርጠህ አጥንትህ ሁሉ በድካም ድቅቅ ብሎ ይታይሀ። ይኼኔ አንድ ንፁህ ክፍል ውስጥ በጣም ንፁህ ሆኖ የተነጠፈ፣ ምቹ አልጋ አጠገብህ አለ። ለመተኛት ትችላለህ፣ የአባትህ ቤት ነው፣ መተኛት ማንም አይከለክልህም። አትተኛም? ልብስህን አውልቀህ አትተኛም? ይኸውልህ ሞት እንደዚህ አልጋ ሆኖ ነው የሚታየኝ . . ."

3, የካቲት 18 ቀን 1998 ዓ.ም ባለቅኔ ሎሬት ጸጋዬ ገብረመድኅን በሞት የተለየበት ወር ነበር።

4, የካቲት 23 ቀን 2004 ዓ.ም በኢትዮጵያ የጽሑፍ ታሪክ በርካታ መጻሕፍትን በማሳተም የመጀመሪያው ደራሲ ማሞ ውድነህ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።


5, የካቲት 24 ቀን 1976 ዓ.ም አመሻሽ ላይ ደራሲና ጋዜጠኛ በዓሉ ግርማ ከቤቱ እንደወጣ ቀረ።

እንዲጋጣሚ ሆኖ በተቃራኒው በወርሃ የካቲት 16 ቀን 1928 ዓ.ም የተወለዱት ደራሲ ዳኛቸው ወርቁ ናቸው።

# 10 ሳይንስና ታሪክ ነክ
## የዓለማችን አስደናቂ እውነታዎች

1. ረዘም ያለ የምግብ አብሳዮች ወይም ሼፎች ኮፍያ በጎኑ በኩል 100 እጥፋቶች ያሉት ሲሆን ይህም እንቁላልን ማዘጋጀት የሚቻልባቸውን 100 መንገዶች ያመለክታል፡፡
2. ከዓለማችን ቢራ አምራቾች መካከል የሆነው ጊነስ በእንግሊዝ ብቻ 93,000 ሊትር ቢራ ባለ ረጃጅም ጺም ሰዎች በሚጠጡበት ጊዜ ወደ ጺማቸው ገብቶ እንደሚባክን ግምቱን አስቀምጧል፡፡
3. የእንግሊዟ ንግሥት ኤልሳቤት ሁለተኛ የተዋጣላት መካኒክ ነበረች
4. በሲውዲን ሃገር የሚገኙ ደም ለጋሾች የለገሱት ደም ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ የምስጋና መልእክት ይደርሳቸዋል፡፡
5. የዓለማችን እውቁ ጠፈርተኛ ኒል አርምስትሮንግ የሥራ ማመልከቻ ያስገባው ለማመልከት ከተሰጠው ቀን አንድ ሳምንት ዘግይቶ ነበር፡
6. ውሻዎች እስከ 250 ቃላትንና ምልክቶችን የመረዳት ብቃት አላቸው፡፡ የውሾች አማካኝ የአእምሮ አቅም ከሁለት ዓመት ህጻን ልጅ ጋር ይወዳደራል፡፡
7. የሳሙና አረፋ የመታጠቢያ ውሃ ለረጅም ጊዜ ሳይቀዘቅዝ እንዲቆይ ማድረግ ያስችላል
8. ረጅም እግር ባላቸው ፍላሚንጎ በሚባሉ የወፍ ዝርያዎች እግር መካከል ያለው እጥፋት ጉልበት ሳይሆን እንደ አልቦ አይነት ጌጥ ነው
9. በ1967 በናይጄሪያ የርስበርስ ጦርነት ወቅት በተዋጊዎቹ መካከል ለሁለት ቀናት የተኩስ አቁም ስምምነት ተደርጎ ነበር፡፡ ለዚህም ምክንያቱ እውቁ የእግር ኳስ ኮከብ የሚያደርገውን ጨዋታ ለመመልከት ነበር፡፡
10. የንግል መስራች በ1999 ድርጅቱን ከ1ሚሊዮን ዶላር በታች በሆነ ዋጋ ለመሸጥ ተስማምቶ የነበረ ቢሆንም ገዥ የሆነው ድርጅት አያዋጣኝም ብሎ ትቶታል፡፡

**ምንጭ Mental fioss**



# የምድራችን የአእምሮ ምጡቅ የአልበርት አነስታይን 20 ምርጥ አይታዎችና ምልከታዎች

1. ‹‹ሠላምን በጉልበት ማስጠበቅ አይቻልም፡፡ ሠላምን ማስጠበቅ የሚቻለው በመግባባት ብቻ ነው››
2. ‹‹ስህተት ሠርቶ የማያውቅ ሠው ምንም ነገር ሞክሮ አያውቅም ማለት ነው››
3. ‹‹ ሁሉም ሠው ብሩህ ጭንቅላት አለው፡፡ ነገር ግን አሣን ዛፍ መዝለል አይችልም ብለህ ችሎታውን ካጣጣልከው በህይወትህ ሙሉ አሣ ደደብ እንደሆነ ታስባለህ››
4. ‹‹ዓይነ ሕሊና ከዕውቀት የላቀ አስፈላጊ ነው››
5. ‹‹ ትምህርት አዕምሯችን የበለጠ እንዲያስብ እንጂ ጥሬ ሃቆችን ለመለማመድ አይደለም ››
6. ‹‹ሙከራህን እስከምታቆም ድረስ በህይወት አትሸነፍም››
7. ‹‹አንድን ነገር በቀላል ቋንቋ መግለፅ ካልቻልክ ነገሩን አልተረዳኸውም ማለት ነው ››
8. ‹‹እብደት ማለት አንድን ነገር በተመሳሳይ ዘዴ ደግሞ ደጋግሞ በመስራት የተለየ ውጤት መጠበቅ ነው››
9. ‹‹ ደስተኛ ሕይወት ለመኖር ከፈለግክ አንተነትህን ከሠዎች ወይም ከነገሮች ጋር ከማወዳደር ይልቅ ከግብህ ወይም ከዓላማህ ጋር ራስህን እሠር››
10. ‹‹ ስኬታማ ለመሆን ከፈለግክ የስኬት ፍላጎትህ እወድቃለሁ ብለህ ከምትፈራው ፍርሃትህ በእጅጉ የበለጠ መሆን አለበት››
11. ‹‹መቀራረብ በፍቅር ለመውደቅ ዋስትና አይሆንም››
12. ‹‹ ዋጋ ያለህ ሠው ለመሆን ሞክር እንጂ ስኬታማ ብቻ ለመሆን አትሞክር ››
13. ‹‹ ምክንያታዊነት ከአንድ ቦታ አንስቶ ወደሌላ ቦታ ሊወስድህ ይችላል፡፡ ዓይነ ሕሊና ግን የትም ይወስድሃል››
14. ‹‹ ጎበዝ ሠው ችግሮችን ይፈታል፡፡ ብልህ ሠው ግን ችግሮቹ መልሠው እንዳይፈጠሩ ያስወግዳቸዋል ››
15. ‹‹ ተፈጥሮን በጥልቀት ተመልከት፡፡ ያን ጊዜ ሁሉንም ነገሮች በተሻለ ትረዳለህ ››
16. ‹‹ ሴቶች ብዙ ጊዜ የሚጨነቁበት ወንዶች ጨርሠው በረሳቸው ነገሮች ላይ ነው ወንዶችም ብዙ ጊዜ የሚጨነቁበት ጉዳይ ሴቶቹ በማያስታውሷቸው ነገሮች ላይ ነው ››
17. ‹‹ቅዱሱን ጉጉትህን አትጣለው››
18. ‹‹ የአመለካከት ድክመት እየቆየ ሲሄድ የባህሪ ድክመት ይሆናል ››
19. ‹‹ ሞትን መፍራት ማለት ተገቢ ባልሆኑ ፍርሃቶች መንቦቅቦቅ ነው፡፡ ምንም ስጋት የሌለበት ሠው ቢኖር የሞተ ሠው ብቻ ነው››
20. ‹‹ፍፁም የማይመስለውን የሚሞክሩ የማይቻለውን የሚችሉ ናቸው››

# የአባትና ልጅ አስገራሚ የፉክክር ታሪክ

በባሌ ጎባ ከተማ ነዋሪ የሆኑት ሼክ ካሚል አልዩ የ6 ልጆች አባት ናቸው፡፡ የመጀመሪያ ልጃቸውን ረመዳን ካሚል ወደ ትምህርት ቤት ለማስመዝገብ ሲሄዱ ‹‹እኔስ ለምን አልማርም›› በማለት ትምህርታቸውን ይጀምራሉ፡፡

አባትና ልጅ በጋራ ትምህርታቸውን መማር ይጀምራሉ፡፡ መጀመርም ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ተፎካካሪ ይሆናሉ፡፡ እርስ በእርስ ያላቸው ፉክክርን ተከትሎ ከ1ኛ እስከ 10ኛ ክፍል አባት አንደኛ ሲወጡ ልጅ ሁለተኛ፤ ልጅ አንደኛ ሲወጣ አባት ሁለተኛ ሆነው ይቀጥላሉ፡፡

በ10ኛ ክፍል ማትሪክ አባት 3.6 ሲያመጡ ልጅ 3.8 ያመጣል፡፡ በ12ኛ ክፍል የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ልጅ 500 ሲያመጣ፣ አባት 490 ውጤት ያመጡና ወደ ዩኒቨርሲቲ ይገባሉ፡፡

አባት ከመዳ ወላቡ ዩኒቨርሲቲ በማኔጅመንት ሲመረቁ፣ ልጅ ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ በሀይድሮሊክ ኢንጅነሪንግ ተመርቀዋል፡፡ በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የልጃቸው ሰቅሎ መቅረት የከነከናቸው አባት በመዳወላቡ ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስ አድሚንስትሬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ሲይዙ ልጅም ሁለተኛ ዲግሪውን አጠናቋል፡፡

ሁለቱም በዩኒቨርሲቲ መምህርነት በመሥራት ላይ የሚገኙ ሲሆን ፉክክሩ አላበቃም፡፡ ፉክክሩ ጤናማ ሲሆን አንዳቸው ሌላኛውን ለመብለጥ ዘወትር አያንቀላፉም ነበር።

**ምንጭ- ብስራት ሬዲዮ**

# የኢትዮጵያ አየር መንገድ

የኢትዮጵያ አየር መንገድ መስከረም 1 ቀን 1939 ዓ.ም. ባለቤትነቱ ሙሉ ለሙሉ የኢትዮጵያ በመሆን ቲ ደብሊው ኤ ከተባለው የአሜሪካ የአየር መንገድ ኩባንያ ጋር በውል በመፈራረም ጠቅላላ አስተዳደሩን ቲ ደብሊው ኤ እንዲመራው በማድረግ 1,000,000 ዶላር (በወቅቱ ምንዛሪ 2,500,000 ሺህ ብር) ካፒታል ተመሠረተ። መጋቢት 30 ቀን 1939 ዓ.ም. ሥራውን በይፋ ጀመረ። ሥራውን የጀመረባቸው አውሮፕላኖች ዲሲ- 3 የተባሉት ሲሆኑ ብዛታቸውም ስድስት ነበሩ። የመጀመሪያው የሀገር ውስጥ በረራ ከአዲስ አበባ በመነሳት ጎንደር፣ ደብረ ማርቆስ፣ ድሬዳዋ፣ ጅማና ጎሬ የተባሉ ከተሞችን ያካተተ ነበር። የኢትዮጵያ አየር መንገድ የመጀመሪያውን የውጭ ሀገር በረራ ያካሄደው በ1949 ዓ.ም. ወደ ካይሮ(ግብጽ) በዲሲ- 3 አውሮፕላን ነበር። የመጀመሪያውን የአውሮፓ ጉዞ ያደረገው ደግሞ ሲቪ 240 በተባለ አውሮፕላን ሚያዝያ 3 ቀን 1954 ዓ.ም. ወደ አቴንስ ነበር።

**ምንጭ- (ዳንኤል ዓስሙ፣‹‹ይህን ያውቁ ኖሯል? ቁ 1››፣ 2007 ዓ.ም. )**